ከህወሓት በኋላስ?
አዲሱ የትግራይ ፖለቲካ ፍኖት!

ከጄነራሎቹ በሥተጀርባ

"ሀገር እና መንግሥት
ግራ የሚገባን ሕዝቦች አይደለንም"
ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ቅጽ 2 ቁጥር 111 ህዳር 2013 ዓ.ም ዋጋ 20.00



የመጨረሻው የመቀሌ ከበባ

የትግራይ አርነት እወጃ

የአዲሱ አስተዳደር የመዋቅር ዝርጋታ

## የዘመቻው መቋጫ ምዕራፍ



"በኢትዮ-ኢራን መካከል ያለውን
ሁለንተናዊ ግንኙነት ማሳደግ ተችሏል"

ዶ/ር ሳልማን ሩስታሚ (የኢራን የባህል ማእከል ኃላፊ)



"ወጣቱ የእኛ ትውልድ የሰራውን
ሕገመንግሥት ቀድዶ መጣል ይኖርበታል"

"የኔ ትውልድ ኢትዮጵያን ያየበት መንገድ መጨረሻ ክሽፈት ነው"

ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም

ቅፅ 2 ቁጥር 111 ህዳር 26 ቀን 2013 ዓ.ም

# ግዮን ክፍል

ክፍል ሁለት 23-28

## ግዮን
## ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ ታህሳስ 3/2013 ዓ.ም
## ይጠብቁን




ቁጥር 110


ዜናዎች
ገፅ 3

አዲስ የአስተሳሰብ መንገድ ለመከተል ወሳኙ ወቅት አሁን ነው! 2

ማህበራዊ ሚዲያ 13

ሐሙስ ቅዱስ ወይስ እርኩስ? 7

አንደበት 16

ከህወሓት በኋላስ? አጼሱ የትግሬይ ፖለቲካ ፍኖት! 8


የዘመቻው መቋጫ ምዕራፍ 17

“ሀገር እና መንግሥት ግራ የሚገባን ሕዝቦች አይደለንም”
ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ 10

ከጄነራሎቹ በሥተጀርባ 21

የዶ/ር ዐቢይ እና የአፄ የኃይለሥላሴ የባሕሪ ምስስሎሽ
መታሰቢያ መልዓከሕይወት 12

“ሥራችን ሴቶችን ማብቃት ነው”
ወ/ሮ ሮማን ደቅሲዎስ 14


“ወጣቱ የእኛ ትውልድ የሰራውን ሕገመንግሥት ቀድዶ መጣል ይኖርበታል”
“የኔ ትውልድ ኢትዮጵያን ያየበት መንገድ መጨረሻ ክሽፈት ነው”
ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም 4

# አዲስ የአስተሳሰብ መንገድ ለመከተል ወሳኙ ወቅት አሁን ነው!

ያለፉት አርባ ዓመታት በጥቅል፣ ያሳለፍናቸውን ሠላሳ ዓመታት ደግሞ በተለይ፣ የማኅበረ ፖለቲካችን ምስቅልቅል መሠረት የኾነው ህወሓት መራሹ ኃይል ግብዓተ መሬቱ እየተፈጸመ ነው፡፡ ይኽ ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ኀላዌ በተለያየ መንገድ ሲታገልና ዋጋ ሲከፍል ለቆየ ወገን ሁሉ ትልቅ ብሥራት ነው፡፡ የጊዜ ጉዳይ እንጂ ኢትዮጵያ ተሸንፋና ተዋርዳ እንደማትቀር፣ ለጥቂቶች ጠባብ ሕልምና ፍላጎት የደከመች ብትመስል እንኳን ተረትታ እንደማትቀይ ያሳየ አጋጣሚ ነውና ድሉ ትልቅ ነው፡፡

በዚህ ብቻ አያበቃም፡፡ ኢትዮጵያችን "ቀበርናት፣ ሰበርነባት" ያሏትን አንገት የምታስደፋ ሀገር መኾኗን ያሳየችበት ታሪካዊ አጋጣሚ ኾኖ ያለፈ መኾኑም ዳግም ሕልውናዋን አስይዘው መቆመር ለሚፈልጉ ሁሉ ጥልቅ ትምህርት የሰጠ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በዚህም "እኛ ከሌለን የለችም" የሚለው ባዶ እብሪትና ከንቱ ፉከራ አፈር በልቷል፤ "ባልበላውም ጭሬ ልበትነው" የሚለው የስግብግቦች ተምኔት ቅዠት ኾኖ ቀርቷል፡፡ የኢትዮጵያና የዜጎቿ ሕልውና እንቅልፍ ነስቷቸው፣ እረፍት አሳጥቷቸው ወጣትነታቸውን፣ የከበረ ሙያቸውን፣ ሀብታቸውንና ኑሯቸውን ወደጎን ብለው ያለፉትን ሃያ ሰባት ዓመታት የታገሉ ሁሉ ክብር ይገባቸዋል፡፡

ገና ከጥንስሱና ከአበቃቀሉ የድርጅቱን ፖለቲካዊ ፍኖት ጠልቀው የተረዱ ህወሓት ሀገርን ወደመቀመቅ እንደሚከትት አልተጠራጠሩም፡፡ ይኽ በስሁት ርዕዮት-ዓለምና አስተሳሰብ የሚመራ ድርጅት ገና በለጋ ዕድሜው ወደሕሊናው ይመለስ ዘንድ የበዛ ዋጋ ከከፈሉ ዘርፎች አንዱ ደግሞ የነጻው ፕሬስ ነው፡፡ ህወሓት/ኢሕአዴግ የዴሞክራሲና ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ ነጻነት ጸር በመኾኑ ያለፉትን ኹለት ዐሠርቶች ከነጻው ፕሬስና ከጋዜጠኞች ጋር ዓይንና ናጫ ኾኖ ቆይቷል፡፡

በዚህም ሳቢያ ታሪክ በመፈጠረለት የአራት ኪሎን ደጆች የመቆጣጠር ዕድል መንግሥታዊ ምስፍናውን ጋዜጠኞችንና ልኂቃንን በማሳደድ ሲያባክነው ኖሯል፡፡ እንደ ኤሳው ብኩርናውን በምሥር የሸጠ ጥቂት አድርባይ መኖሩ ባይካድም፣ አብዛኃው የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኛ ግን የሀገር ፍቅር እና የኢትዮጵያ ሕልውና ከምንም በላይ ያንገበግበው ስለነበር የህወሓት ሕጋዊ ሞት እስከተበሰረበት የመጨረሻዋ ሰዓት ድረስ ከትግሉ አልነጠፈም፡፡ ይኽ የአይበገሬነትና የእምቢ ባይነት መንፈስ ቀጣዩ ትውልድ በእጅጉ ሊማርበት የሚገባ የጽናት ልክ ነው ብሎ መመስከር ይቻላል፡፡

ያለፉትን ዓመታት በኢትዮጵያ የተቃውሞ ፖለቲካ የተደረገው የጸረ ህወሓት ተጋድሎ ያስከፈላቸው ዋጋዎች በቀላሉ ተዘርዝረው የሚያልቁ አይደሉም፡፡ ገና የግንቦት 1983 አየር በዚህ ድርጅት ቁጥጥር ሥር የዋለ ከመሰለበት ጊዜ አንስቶ፣ እንደኤቢሳ አዱኛ ዐይነት ድምጻዊያን ተገድለው አስከሬናቸው መንገድ ለመንገድ ተጎትቷል፤ እንደፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ዐይነት ታላላቅ ዋርካዎች በእሥርና ሕክምና ዕጦት ማቅቀው እንዲሞቱ ተፈርዶባቸዋል፤ እንደአሰፋ ማሩ ያሉ ጉምቱ የመምህራን ማኅበር ተጠሪዎች በቤታቸው ደጃፍ የጥይት እራት ኾነው ቀርተዋል፡፡

የበደል ሂሳብ ውርርድ ውስጥ መግባት ለሀገራችን የነገ ፍኖት ጠብ የሚያደርገው አንዳች ነገር የለም በሚል ስሌት አልተነገረም እንጂ ስብስቡ በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያን ላይ አመለካከትን፣ ዘርንና ሃይማኖትን እየለየ ያልፈጸመው ወንጀል የለም፡፡ የህወሓት በኢትዮጵያ የነገ ፖለቲካ ውስጥ ታሪክ ኾኖ መቅረት ልዩ ትርጉም የሚኖረውም ድርጅቱ በዕድሜው ለፈጸማቸው ግፎች ዳፋውን ያልተሸከመ አንድም ኢትዮጵያዊ ስለማይገኝ ነው፡፡

ደጋግመን እንደምንለው ግን ህወሓት "ኖሮ በግፉ፣ ሞቶ በሰንኮፉ" የሚያጋድል ድርጅት ነው፡፡ "በቅሎ ገመዷን በጠሰች ቢሉ…" እንዲሉ ኾነና የማይነካ ነክቶ ሞቱን በራሱ ላይ ቢያውጅም ከሕጋዊ ሰውነቱ መደምሰስ በኂላም መሠል ኦሊጋርኪያዊ፣ ጠባብ ቡድናዊና ሴረኛ ድርጅት በኢትዮጵያ ማኅበረ ፖለቲካዊ መድረክ እንዳይፈጠር ጠንክሮ መሥራትና መታገል ይገባል፡፡

ህወሓት በውይይትና በንግግር ሊፈቱ የሚችሉ በርካታ ጥያቄዎችን ወደማይታረቅ የማኅበረሰብ ቅራኔ ከፍ አድርጎ ያለፈ ድርጅት ነው፡፡ ለዚህም ነው፣ መንግሥት የትኞዎቹም የግልም ይኹን የማኅበረሰብ ፍላጎቶች ከኢትዮጵያችን አንድነትና ሕልውና በታች መኾናቸውን ግልጽ በማድረግ መፍትሔ ለመስጠት መረባረብ አለበት የምንለው፡ ፡ በመኾኑም "አሉ" የሚባሉ ማኅበረ ፖለቲካዊ ችግሮቻችንን ለመፍታት ያልተሄደበትን አዲስ የአስተሳሰብ መንገድ የመከተያ ወሳኙ ወቅት አሁን በመኾኑ መንግሥት ለኢትዮጵያችን ሕልውና ጠንቅ የኾኑ ጉዳዮችን ለይቶ መልስ የመሥጠት እንቅስቃሴ መጀመር አለበት እንላለን፡፡


**ግዮን መጽሔት**

**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ዋና አዘጋጅ**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ
አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 1035

**ማኔጂንግ ኤዲተር**
ኄኖክ ገለታው

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ብሩክ መኮንን

**አዘጋጅ**
ቀጸላ ክፍሌ
ቢንያም አሊ

**አምደኞች**
አቦነህ አሻግሬ ዘ ኢየሱስ (ፒ/ር)
ሙስጠፋ ሓሚድ የሱፍ
ውብሸት ታዬ
ሁሴን ከድር
ዶ/ር ሃይደር አብደላ
ኢ/ር ወንድሙ ነጋሽ
በኃይሉ ገ/እግዚእሔር
ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ
ሠሎሞን ለማ ገመቹ

**ጸሐፊ**
ገነት ብርሃኑ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
እየሩሳሌም ወንድምነህ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011meg@gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ
0911223335/ 0911420506


በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም

## አቶ አገኘሁ ትህነግ በሽብርተኝነት እንዲፈረጅ ጠየቁ

ለዓመታት ህዝብን ሲያሰቃይና በቅርቡ ደግሞ በመንግሥት ላይ ጥቃት የፈፀመው የትህነግ ፓርቲ፣ በፈፀመው ግፍና የሀገር ክህደት ወንጀል ምክንያት በአሸባሪነት እንዲፈረጅ ተጠይቋል። ይህ ጥያቄ ለኦነግ ሸኔ ቡድንም የቀረበ ሲሆን፣ በኦሮሚያ ክልል እየፈፀመ በሚገኘው ዘግናኝ ወንጀል ሳቢያ እርምጃ ሲወስድበት እንደቆየ ይነገራል። ሁለቱ የፖለቲካና ወታደራዊ ቡድኖች በአሸባሪነት እንዲፈረጁ የጠየቁት የህዝብ ተወካዩች ምክር ቤት አባላት በያዝነው ሳምንት መጀመሪያ ላይ በነበረውና ጠ/ሚ/ሩ በተገኙበት ስብሰባ ላይ ነው። በተመሳሳይ፣ የአማራ ክልል ርዕስ መስተዳድር አገኘሁ ተሻገር የትህነግ ታጣቂ ቡድን በአሸባሪነት እንድፈረጅ እንረባረብ የሚል ጥሪ ለህዝቡ አቅርበዋል።

በትዊተር ገፃቸው ላይ ባሰፈሩት ጥሪ መሠረት፣ ፓርቲው በሽብርተኝነት እንዲፈረጅና አባላቱ በህግ እንዲጠየቁ ለማድረግ ዘመቻ መጀመሩን አሳውቀዋል። “የአገራችን ህዝቦች፣ ማይካድራ ዜጎቻችን ላይ የተፈፀመው የዘር ጭፍጨፋ ህወሓት የሚባል ድርጅትን ሽብርተኛ ካላስባለ ምን ሊሆን ይችላል? ወያኔን በሽብርተኝነት ለመፈረጅ በሚደረገው ዘመቻ ተባብረን እንድንነሳ በአማራ ህዝብ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ” በማለትም ህዝቡ የተጀመረው ዘመቻ ላይ እንዲሳተፍ ጠይቀዋል።

## ለቁጥር የሚታክት የጦር መሣሪያ መቀሌ ተገኘ

መቀሌ ከተማ በመከላከያ ቁጥጥር ስር መዋሏን ተከትሎ ከተማዋን በመፈተሸ ላይ የሚገኘው የፀጥታ ሀይል በመጋዘን የተከማቸ ለመቁጠር የሚያዳግት የጦር መሣሪያ ማግኘቱ ይፋ ተደርጓል። በፎቶግራፍ ተደግፎ የወጣው ይህ መረጃ እንደሚያሳየው፣ በሳጥን የተቀመጡ በርካታ ቁጥር ያላቸው የጦር መሳሪዎችና አንደ ደመራ የተቆለለ የነፍስ ወከፍ ጠብመንጃ ነው። በረድፍ አግድም የተረበረበው የተለያየ አይነት ጠመንጃ አቧራ ቅሞ ከሰው ቁመት በላይ ተደርድሯል። ቁጥሩን ለመገመት የሚያስቸግር ከመሆኑ በተጨማሪ ለመቁጠር በርካታ ሰዎችን ለቀናት ሊያውል እንደሚችል ይገመታል። በዚህ መልክ ይህን ያህል የጦር መሣሪያ ትህነግ አከማችቶ ያስቀመጠበት ምክንያት በግልጽ አይታወቅም። ከየት ያገኙት የህዝብ ወይም የመንግሥት ሀብት እንደሆነ በግልጽ አልተነገረም።

## የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከኢትዮጵያ ጋር መስማማቱን ተናገረ

በሰሜን ኢትዮጵያ እየተወሰደ ባለው ህግን የማስከበር ዘመቻ ጉዳት ለደረሰባቸው ንፁሐን ዜጎች እርዳታ ማስገባት እንዲቻል የሚያደርግ የስምምነት ፊርማ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ማድረጉን የተባበሩት መንግሥት ድርጅት ኃላፊ አሳውቀዋል። በትግራይ ክልል እርዳታ ለማስገባት ፈቃድ መገኘቱን ተከትሎ ሁኔታውን የሚገመግም የልዑካን ቡድን ወደ ኢትዮጵያ መግባቱን የተባበሩት መንግሥታት ቃል አቀባይ ተናግረዋል፡ ፡ በክልሉ አጋጥሟል የተባለ የመድኃኒትና ምግብ አቅርቦት በመከሰቱ በርካታዎች ችግር ላይ ናቸው ተብሏል። የመቀሌው አቅርቦት በመከሰቱ በርካታዎች ችግር ላይ ናቸው ተብሏል።

የመቀሌው አይደር ሆስፒታል አስፈላጊ የህክምና መገልገያ ቁሳቁሶች አልቆበታል ሲል አለም አቀፏ ቀይ መስቀል ማህበር ማስታወቁን ተከትሎ ግፊት መበርታቱ ይነገራል። በሌላ በኩል፣ ዘመቻው በተካሄደባቸው አካባቢዎች በሚገኙ የስደተኛ ማቆያዎች ውስጥ የሚገኙ በሺዎች የሚቆጠሩ ኤርትራውያን ስደተኞች የምግብ እጥረት እያጋጠማቸው እንደሆነ የተመድ የስደተኞች ድርጅት የስደተኞች ተቋም UNHCR አሳውቋል። ከሠሞኑ ተመድ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በተፈራረመበት ስምምነት መሠረት፣ ያለ ምንም እክል በክልሉ እርዳታ ማቅረብ እንዲቻል ነው። የመጀመሪያው ተግባር ምን አይነት እርዳታ እንደሚያስፈልግ ማጣራት ነው የተባለ ሲሆን፣ ቀጥሎም እርዳታው ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ማቅረብ እንዲቻል የሎጂስቲክ ቡድን ማቋቋም ነው ተብሏል።

## በሕግ ማስከበር ዘመቻው ተገኝተው ሲዘግቡ ለነበሩ የሚዲያ ባለሙያዎች እውቅና ተሰጣቸው

በትግራይ ክልል በተካሄደው የሕግ ማስከበር ዘመቻ ላይ በምዕራብ ግንባር ተገኝተው በመዘገብ የተሰጣቸውን ሀገራዊ ተልዕኮ ለተወጡ የሚዲያ ባለሙያዎች የምስጋና መርሐ ግብር ተካሄደ:: የምስጋና መርሃ ግብሩ የተካሄደው በዘመቻው በምእራብ ግንባር ከዳንሻ፣ ሁመራ፣ ሽራሮ፣ በሽሬ አድርጎ እስከ አድዋና አክሱም የዘለቀ ስምሪት ለነበራቸው የሚዲያ ባለሙያዎች ነው። በምስጋና መርሐ ግብሩ ላይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመረጃ ፍሰት ቃል አቀባይ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴንን ጨምሮ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና የአገር መከላከያ ሠራዊት ተወካዮችና የተለያዩ የሚዲያ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

## የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ኹለተኛ መጽሐፍ ተመረቀ




“የታፋኙ ማስታወሻ” በሚል ርዕስ በ310 ገጾች የተዘጋጀው የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ መጽሐፍ ባሳለፍነው ቅዳሜ 19/2013 ዓ.ም በግዮን ሆቴል ታዋቂ ፖለቲከኞችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት ተመርቋል። መጽሐፉ አቶ አንዳርጋቸው የመን ላይ እንዴት፣ በማን እና በምን ሁኔታ አፈና እንደተፈጸመባቸው፤ ወደ አዲስ አበባ እንዴት እንደተወሰዱ፤ በአዲስ አበባ እንዴት እንደተጓዙና በድብቅ የአፈና ቤት እና በቃሊት እስር ቤት የነበራቸውን ሕይወት የሚተርክ ነው። በተጨማሪም ደራሲው ከእስር ከተፈቱ በኂላ ከጠ/ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ ጋር ያደረጉትን ውይይት እና እሱን ተከትሎ ስለተፈጸመው የኢትዮጵያ እና የኤርትራ ስምምነት ያስረዳል፡ ፡ መጽሐፉ ለገበያ የቀረበው በ280 ብር ነው።

## የኢትዮ ቴሌኮም ሰራተኞች ወደ መቐለ መጓዛቸው ታወቀ

የኢትዮ ቴሌኮም ሠራተኞች ወደ መቀሌ መጓዛቸውን ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ ወ/ሪት ፍሬሕይወት ታምሩ አሳወቁ። በመቀሌ ያሉት የኢትዮ ቴሌኮም አገልግሎት መስጫ እቃዎች ማከማቻ ላይ ጉዳት መድረሱንና በቅርቡ እንደሚጠገንም ገልጸዋል። ከቴሌ ታወሮች ጋር የሚያገናኙ በርካታ የፋይበር ኬብሎችም ተቆርጠዋል ይህም ይጠገናል ብለዋል ወ/ሪት ፍሬህይወት። የመቀሌ ከተማን ጨምሮ በመላው ትግራይ ክልል የቴሌኮም አገልግሎት ለማስጀመር በመቀሌ ያለው (core site) ጉዳት መጠን መለየት አለበት፤ ጉዳቱ ከፍተኛ ከኾነ አገልግሎቱን ለመመለስ ረጅም ጊዜ ሊወስድ እንደሚችል ተናግረዋል።

በሌላ በኩል ሽረ አካባቢ ያለ ፋይበር ኦብቲክ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል ያሉት ሥራ አስኪያጇ ጉዳቱ ረጅም ኪሎ ሜትር ስለኾነ ጥገናው እስካሁን እንዳልተጠናቀቀ ተናግረዋል። በተመሳሳይ ዜና በትግራይ ክልል የቴሌኮምንኬሽን አገልግሎት መስጠት መጀምሩን ሕዳር 23 ቀን ባሰራጨው መረጃ አስታውቋል። በአላማጣ ከተማ ሙሉ አገልግሎት መጀመሩን የገለጸው ኢትዮ ቴሌኮም፤ በማይጸብሪ፣ ማይካድራ፣ ዳንሻ፣ ሑመራ፣ ተርካ እና ሽራሮ ከተሞች ደሞ በከፊል አገልግሎት መስጠት እንደጀመረ ገልጿል።

## ሱዳን ሸሽተው ወደ ግዛቷ የገቡ 50 ወታደሮችን ለኢትዮጵያ አሳልፋ ሰጠች

ሱዳን ከትግራዩ ግጭት ሸሽተው ወደ ግዛቷ የገቡ 50 ወታደሮችን እና ፖሊሶችን ለኢትዮጵያ አሳልፋ እንደሰጠች ሱዳን ትሪቡን ዘግቧል፡ ፡ ከእነዚህ ውስጥ አንድ ኮሎኔልን ጨምሮ 31ዱ የጦር ሠራዊት አባላት ሲኾኑ፣ 13ቱ ፌደራል ፖሊሶች፣ 6ቱ ደግሞ የጉምሩክ ባልደረባዎች ናቸው ተብሏል። አባላቱ ተላልፈው የተሰጡት በመተማ በኩል መኾኑ ተገልጿል። በተያያዘ ዜና ወደ ሱዳን የሚሰደዱ ኢትዮጵያውያን ቁጥር በእጅጉ መቀነሱን የዓለም አቀፉ ስደተኞች ኮሚሽን ገለፀ። ዓለም አቀፉ የስደተኞች ኮሚሽን ኮሚሽነር ፍሊፖ ግራንዴ ለሲኤንኤን እንደገለፁት፣ በኢትዮጵያ አሁን ያለው ሁኔታ ወደ መደበኛ ሁኔታ በመመለሱ ወደ ሱዳን የሚሰደዱ ኢትዮጵያውያን ቁጥር በእጅጉ ቀንሷል።የሚሰደዱ ሰዎችን ለማቋቋምና ወደነበሩበት ለመመለስ የኢትዮጵያ መንግስት ዝግጁ መሆኑን የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ማረጋገጡ ተነግሯል።

## ቀጣዩን ምርጫ ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ መግባባት ላይ መደረሱ ተገለጸ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከፖለቲካ ፓርቲዎች አመራሮች እና ከሲቪክ ማኅበረሰብ ተወካዮች ጋር ሕዳር 23 ቀን በተካሄደው ውይይት፣ ቀጣዩ ምርጫ ዴሞክራሲያዊ በሚኾንበት መንገድ መግባባት ላይ መደረሱን አስታውቀዋል። የፌዴራል መንግሥት በኢትዮጵያ ነጻ እና ፍትሐዊ ምርጫ የሚካሄድበትን መሠረት ለመጣል በቁርጠኝነት መሥራቱን እንደሚቀጥል መግለፃቸውንም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልፀዋል። ውይይቱ ቀጣዩን ሀገር ዐቀፍ ምርጫ ነጻ እና ፍትሃዊ በማድረግ ላይ ያተኮረ እንደኾነም በማኅበራዊ የትስስር ገጻቸው አሳውቀዋል።

# “ወጣቱ የእኛ ትውልድ የሰራውን ሕገመንግሥት ቀድዶ መጣል ይኖርበታል”

## “የኔ ትውልድ ኢትዮጵያን ያየበት መንገድ መጨረሻ ክሽፈት ነው”

### ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም



በሃገረ-አሜሪካ ሳን ቤርናርዲኖ የካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር ከኾኑት ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም ጋር ከለውጡ በኋላ በሊቀመንበርነት ስለሚመሩትና የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ትረስት ፈንድ እንቅስቃሴ፣ ስለሕይወታቸውና በተለያዩ ሀገራዊ፣ ወቅታዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከጋዜጠኛ ፍቃዱ ማህተመወርቅ ጋር ያደረጉትን ክፍል ሁለት ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡ መልካም ንባብ !

ግዮን፡- ከሀገር ከወጡ ምን ያህል ጊዜ ኾኖት? በምን አጋጣሚስ ሊወጡ ቻሉ?

ፕ/ር አለማየሁ፡- ከሀገር የወጣሁት እ.ኤ.አ 1970 ነው፡፡ የወጣሁበት ምክንያት ደግሞ ለትምህርት ነው፡፡ በወቅቱ በ1960ዎቹና ሰባዎቹ ወደ አሜሪካ የምንሄድ ወጣቶች በጣት የምንቆጠር ስንኾን የምንወጣበት ዓላማም ለትምህርት ነበር፡፡ እኔም እድለኛ ስለነበርኩ ከሀገር ወጥቶ የመማር እድሉ ተካፋይ ኾንኩ፡፡ ያው በእኛ ትውልድ ጊዜ ልጆች ኾነን “አሜሪካ ሄደን፣ እንዲህ አድርገን፣ ይኽን ገዝተን” የሚል ምኞት ነበረን፡፡ እኔም ውስጥ ይኸ ሕልም ነበር፡፡ ምክንያቱም ብዙ የምናያቸው ብልልጭል ነገሮች ነበሩ፡፡

የመኪናው፣ የቤቱ፣ የመንገዱ፣ የልጆች የጨዋታው፣ ወጣቶቹ እንዴት በነጻነት እንደሚንቀሳቀሱ፣ የተለያዩ ሰልፎችን ሲያደርጉ ማየቱ ያስቀናንና ያጓጓን ነበር፡፡ ስለዚህም አሜሪካ መሄድ በጣም እንፈልግ ነበር፡፡ እኔ ደግሞ ቤተሰቦቼ ትንሽም ቢኾን ንብረት ያላቸው ስለነበሩ ለመውጣት ያን ያህል አልተቸገርኩም፡፡ በወቅቱ እማር የነበረውም ጆርጂያ በምትባለው የአሜሪካ ግዛት ውስጥ ሳንጆሴፍ በሚባል ትምህርት ቤት ነበር፡፡ ለአራት ዓመት ትምህርቴን ከተከታተልኩ በኋላ በአውሮፓውያኑ 1974 ለሦስት ወር ገደማ ወደሀገሬ ተመልሼ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ሀገሬን ላያት የቻልኩት ከ48 ዓመታት በኋላ ነሐሴ 2018 ዓ.ም ነው፡፡

ግዮን፡- 48 ዓመት አሜሪካ ከመቆየቶ አንጻር የትምህርትና የቤተሰብ ሕይወቶ ምን ይመስል እንደነበር ቢያጫውቱኝ?

ፕ/ር አለማየሁ፡- በጣም የቀለም ሰው ስለነበርኩ ከሀገሬ እንደወጣሁ ትኩረቴ ትምህርት ላይ ነበር፡፡ በተለይ በዚያን ጊዜ በአሜሪካ የሚገኙ ብዙ ወጣት ተማሪዎች የፖለቲካ አቀንቃኞች ነበሩ፡፡ እኔ ግን በወቅቱ ዝንባሌዬ ፖለቲካው ሳይኾን የመጣሁበትን ተልዕኮ ፈፅሞ ሀገርን ማገልገል ነበር፡፡ በዚህም በ1973 መጨረሻ ዲግሪዬን ከጆርጂያ ለመያዝ ችያለሁ፡፡ ወዲያውም ከፍ ሲል እንዳልኩት ለጥቂት ጊዜ ሀገሬ መጣሁና ማስተርስ ለመማር ወደ አይዋ በመሄድ አንድ ዓመት ተምሬ አጠናቀቅኩ፡፡

በመቀጠልም እ.ኤ.አ በ1976 ወደ ሚኒሶታ በመሄድ እስከ 1983 ድረስ ቆይቼ የዶክትሬት ዲግሪ (PHD) ይዤለሁ፡፡ ከዚያ በኋላ በ1984 ወደ ሜሪላንድ በመሄድ ሕግ ት/ቤት በመግባት በ1988 ማጠናቀቅ ችያለሁ፡፡ እንግዲህ አብዛኛውን ጊዜዬን ያጠፋሁት በትምህርት ላይ ነበር ማለት ነው፡፡ ነገር ግን በትምህርት ላይ እያለሁም ት/ቤት ውስጥ ሥራ እሠራ ነበር፡፡ ለምሳሌ ግራጁዌት ስኩል ረዳት መምህር በመኾን ጥናት(ሪሰርች) አሠራ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ወደ ሜሪላንድ ሄድኩና ሞደርን ስቴት የሚባል ት/ቤት ተቀጠርኩ፡፡ ኹለት ዓመት አካባቢ እንደሠራሁ የሪሰርች ሴንተሩ ሰውዬ ሲሄድ እኔ አክቲንግ ዳይሬክተር ኾኜ ተሰየምኩ፡፡ በዚህ መሐል ላይም ከባለቤቴ ከምሥራቅ ገሠሠ ጋር ተዋወቅን፡፡ ከዚያ በኋላ ተጋብተንና ▶

ልጃቻችንን ይዘን ወደ ካሊፎርኒያ በመሄድ በሕግ ፍቃድ አውጥቼ በአንድ በኩል ጥብቅና እየሠራሁ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ማስተማር ጀመርኩ ማለት ነው፡፡ በአጭሩ የቤተሰብ አመሠራረቴና የትምህርት ሕይወቴ ይኽን ይመስላል፡፡

*ግዮን፡- ወደ ኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ መቼ ገቡ? በተለይ ቀደም ሲል የነበሮት ሕልም ተምሮ ሀገርን ማገልገል ነበርና እንዴት የመመለስ ሀሳቦ ሊመክን ቻለ?*

ፕ/ር አለማየሁ፡- እኔ ከኢትዮጵያ እንደወጣሁ ደርግ መጥቶ ዜጎችን በደፈናው መጨፍጨፍ ሲጀምር በሁሉም ነገር ተስፋ ቆርጬ ነበር፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል እንዳልኩት ለሦስት ወር የመጣሁ ግዜ ለውጡን ሳይ መልካም ተስፋ ስለነበረኝ ማስተርሴን ተምሬ ተመልሼ የመምጣት ሃሳብ ነበረኝ፡፡ ወዲያው እንደተመለስኩ ግን የሕዳር ዐሥራ አራቱን ግድያ ስሰማ ተስፋ የጣልኩበት ለውጥ እንዳከተመ ገባኝ፡፡ እና በዚህ ወቅት የተሰማኝ ስሜት ፍፁም በሀገሬ ተስፋ መቁረጥና ኑሮዬን ባለሁበት መቀጠል ነበር፡፡ በዚህም ሙሉ ትኩረቴን ባለሁበት ሀገር ኑሮዬን የሚያሻሽሉ ነገሮች ላይ አደረግሁ፡፡ ነገር ግን ስለሀገሬ መፃፌን አላቆምኩም ነበር፡፡ ለምሳሌ ስለረሀቡ፣ በወቅቱ ስለነበረው አንባገነን መንግሥትና ስለመሳሰሉት ነገሮች በጥናት መልክ አድርጌ ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ይፋ አደርግ ነበር፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች ስለ አፍሪካም ኾነ ስለኢትዮጵያ እጽፍ ነበር፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ ትምህርት ቤት ውስጥ ስለ አፍሪካ ወይም ስለ ኢትዮጵያ ክርክር ሲኖር ንግግር አደርጋለሁ ፤ እሳተፋለሁ፡፡

ያም ቢኾን ግን በሀገሬ ተስፋ ቆርጬ ነበር፡፡ በወቅቱ ወታደራዊው መንግሥት በሀገሪቱ የሚፈፅመው ነገር የሕዝቡን ደህንነት ያልጠበቀ ከመኾኑ አንፃር ሕልሜ ሁሉ ኮስምኖ ተስፋ የምለው ነገር አልነበረኝም፡፡ የደርግን አካሄድ ሳየው ከዚህ በኋላ ጦርነት ድርቅ ረሃብ ነው የሚኖረው ብየ ስላሰብኩ ለምን ብቻየን ለማልቀይረው ነገር እራሴን አሰቃያለሁ በሚል ራሴን እንዳገል አስገደደኝ፡፡ በኋላ ግን የህወሓት መንግሥት ሲገባ "አዲስ ሕገ መንግሥት ስለሚረቅ መጥተህ ተሳተፍ" የሚል ጥሪ ቀረበልኝ፡፡ እኔም ስለደረሰኝ ጥሪ ከቅርብ ጓዶቼ ጋር ከመከርኩ በኋላ አርቃቂው "አሽናፊው" ቡድን መኾኑን ስለተረዳሁ ጥያቄያቸውን ውድቅ አደረግኩት፡፡ በዚህ ሂደት ላይ እያለሁ ምርጫ 2005 (በእኛ 97) መጣ፡፡ በዚህ ወቅት እኔ ብቻ ሳልኾን ሁሉም ኢትዮጵያዊ አዲስ ተስፋ ሰንቆ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህ መነሳሳት ምንጩ ደግሞ በየሚዲያው የሚታየው የጋዜጠኛ ነፃነትና የፖለቲካ ክርክር ነበር፡፡

ወዲያው ግን በምርጫው ዕለት ምሽት የህወሓት መንግሥት አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥቶ በሕዝቡ ላይ ነፃ የግድያ እርምጃ ሲወሰድ እኔም መናወጥ ውስጥ ገባሁ፡፡ ማለትም ሞቶ የነበረው የፖለቲካ ስሜቴ ተቀስቅሶ ድጋሚ ሲወርድ ለራሴ የማልፈታው ውዥንብር ውስጥ ገባሁ፡፡ በኋላ ግን በተለይም መርማሪ ኮሚሽን የሚባለው አካል የተገደሉትን ሰዎች ምስልና የግድያውን ዝርዝር ሁኔታ ይፋ ሲያደርግ ዝምታዬ ወንጀል ሆኖ ስለታየኝ መቃወም አለብኝ ብዬ ወሰንኩ፡፡ ነገር ግን በመቃወሜ እነሱን ማሸነፍ ባልችልም ሰላማቸውን መንሳት እንደሚቻል እምነት ስለነበረኝ በተቻለኝ አቅም የእነርሱን ወንጀልና ጥፋት ለማጋለጥ ወሰንኩ፡፡ በተለይም እነርሱ ዓለም ላይ ካላቸው ተቀባይነት አንጻር እኔ በብዕሬ በራስ መተማመናቸው ለመሸርሸር ተነሳሁ፣ ተሳክቶልኛል ማለት እችላለሁ፡፡ በዚህም በአንድ ወቅት አቶ መለስ በእኔ ላይ ያደረሰብኝ የግል በደል እንዳለና እንደሌለ እስከመጠየቅ ደርሶ እንደነበር አንድ ወዳጄ ነግሮኛል፡፡ አልፎም በተደጋጋሚ በጓደኞቼና በማስተምርበት ተቋም በኩል የተለያዩ መልዕክቶችን ይልክብኝ ነበር፡፡ እንደውም አንድ ወቅት የአገዛዙ ሰዎች ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር የግል ስብሰባ እንድናደርግ ጠይቀውኝ ጭምር ነበር፡፡



በሰዓቱ የእኔ መልስ "እንደ ግለሰብ ሳይኾን እኔም መሰሎቼን ይዤ እርሳቸውም የሚመለከታቸውን የሥራ ባልደረቦች ይዘው በሀገሪቱ እያካሄዱት ያለውን የሰብዓዊ መብት ረገጣ የሚስተካከልበት ነገር ላይ እንወያይ" የሚል ነበር፡፡ ይኽ እንደማይኾን ሲነግሩኝ እኔም አቶ መለስን ማግኘት እንደማልሻ አሳወቅኳቸው፡፡ ነገር ግን አቶ መለስ 2010 ወደ አሜሪካ መጥቶ ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ ብዙዎች እዚህ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንዳይናገር ሲረብሹት ነበር፡፡ እኔ ደግሞ የመናገር ነፃነቱን ልጋፋው አልፈለግሁም፡፡ በዚህም አንዳንዶች ተከፍሎት ነው" የሚል አሉባልታ እስከማስነገር ደርሰው ነበር፡፡ ያም ኾነ ይኽ እኔ ያገዛዙን ሽፍጦች በጽሑፌ አጋልጥ ነበር፡፡

*ግዮን፡- የተለያዩ ጦማሮችን በተከታታይ መጻፍ የጀመሩት በዚህ ጊዜ ነበር ማለት ነው?*

ፕ/ር አለማየሁ፡- መጻፍ የጀመርኩት ህወሓት ሥልጣን እንደያዙ ከ1990ዎቹ አንስቼ ነው፡፡ በወቅቱ እንደውም "ሃሳብ ይቀይራሉ፣ ዕድል ይሰጣቸው" የሚል ዐይነት ይዘት ያለውን ሃሳብ አንፀባርቅ ነበር፡፡ "ከመፈረጅ እንውጣ፣ ሥራቸውን እንይ" የሚል እምነትም ነበረኝ፡፡ በኋላ ግን በተለይም ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ በጽኑ መቃወም ጀመርኩ፡፡ ያው እኔ ጦር እየመሩ ጫካ መግባት ስለማላውቅ ባለኝ እውቀት መሟገት አለብኝ የሚል ውሳኔ ላይ ደረስኩኝ፡፡ በዚህም እነዚህን ሰዎች "international court of public opinion" ፊት አቅርቤ በየሳምንቱ ክስ እመሰርትባቸዋለሁ የሚል እምነት በአዕምሮዬ ቀረጽኩ፡፡ በመኾኑም የእነዚህን ሰዎች አዕምሮ ለመግራትና ለማሸነፍ ዘመቻዬን ጀመርኩ፡፡ በዚህም በተለይም ጽሑፎቼ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ገፅታ ባላውቅም በውጭው ዓለም ግን ራሳቸውን የቻለ ሚና ነበራቸው፡፡ የምዕራባውያንን ትኩረት በመሳብና በዲፕሎማት ደረጃ ያሉትን ከማባነን አኳያ የነበራቸው ስፍራም ቀላል አልነበረም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ከገባሁ በኋላ ግን በተለያየ መልኩ ጽሑፎቼን በርካቶች እንዳነበቡት መታዘብ ችያለሁ፡፡

*ግዮን፡ ጽሑፎችዎ ዘወትር ቅዳሜ ነበር የሚወጡት?*

ፕ/ር አለማየሁ፡- አዎ በአሜሪካ ቅዳሜ፣ በኢትዮጵያ ደግሞ ሰኞ ጠዋት ነው፡፡

*ግዮን፡- ረጅም ዓመት በየሳምንቱ ጽፈዋልና መረጃዎቹን ከየት ነው የሚያመጧቸው? አሁንስ በዚያው መልኩ እየፃፉ ነው? አገኘሁበት የሚሉትስ ትርፍ አለ?*

ፕ/ር አለማየሁ፡- እንደሚታወቀው እኔ የሕግ ሰው ነኝ፡፡ እነዚህን ሰዎች ደግሞ ከፍ ሲል እንዳልኩት በየሳምንቱ በ "international court of public opinion" መክሰስ አለብኝ፡፡ በመኾኑም ለዚህ ሳምንታዊ ክስ ስል ማስረጃዎችን በየትኛውም መልኩ ማዘጋጀት አለብኝ፡፡ አንድ ጽሑፍ ከነማስረጃው ለማዘጋጀት ከ5 ሰዓት በላይ አይወስድብኝም፡፡ ማስረጃዎችን ከተለያየ ቦታ አገኛለሁ፡፡ የአገዛዙ ሰዎችም መረጃዎቹን ይልኩልኝ ነበር፡፡ ያገኘሁትን ውጤት በተመለከተ መለካት ባይቻልም በወቅቱ በነበረው መንግሥት ላይ ቀላል የማይባል ተጽዕኖ እንደሚያሳርፍ ግን የተለያዩ ዲፕሎማቶችና አካላት ነግረውኛል፡፡ በተለያየ አጋጣሚ ከአምባሳደሮች ጋር ስገናኝ የጽሑፌን በሳልነትና የሰላ ተችነት ይነግሩኝ ነበር፡፡ በተጨማሪነት ህወሓት ለእኔ ጽሑፍ አንዴም ምላሽ ሰጥቶ አያውቅም፡፡ ያ ደግሞ የሚያመለክተው ጽሑፌ በመረጃ የተደገፈ ስለኾነ እርሱን ለማስተባበልና ለማውገዝ የሚያስችል ሁኔታ ላይ አለመኾናቸውን ነው ማለት ይቻላል፡፡

በእርግጥ አንዳንድ የህወሓት/ኢሕአዴግ አፈቀላጤዎች የኔ ጽሑፍ ወጥቶ ሦስትና አራት ሳምንት ካለፈው በኋላ የተወላገዱ ማስተባበያዎችን ለመስጠት ሞክረው ነበር፡፡ ይኼ ደግሞ ወቅታዊነቱን ያልጠበቀና የተወናገረ ሃሳብ ከመሆን ያለፈ አልነበረም፡፡ እንደውም በህወሓቶች በኩል መጀመሪያ ጽሑፍ እንደጀመርኩ ሰልችቶት ይተዋል የሚል እምነት ነበራቸው፡፡ ኋላ ግን በቋሚነት ስቀጥል ከላይ እንዳልኩህ ከአፈቀላጤዎቻቸው በዘለለ ቀጥረው ምላሽ ለማጻፍ ቢሞክሩም አልተቻላቸውም፡፡ በዚህ መልኩ ትቀጥላለህ ወይ የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ አዎ እቀጥላለሁ፡፡ ለምሳሌ ባለፉት ሁለት ሳምንታት ከስድስት በላይ አርቲክሎችን አውጥቻለሁ፡፡ ስለዚህ እቀጥልበታለሁ፡፡ በሌላ በኩል ጽሑፎቼን በተመለከተ አንድ አሜሪካን ኤምባሲ የሚሰራ ሰው ነበር፡፡ ይኽ ሰው የእኔን ጽሑፍ በተመለከተ ስጠይቀው ሥራዎቼ ፋይል እየተደረጉ ወደ ስቴት ዲፓርትመንት መላካቸውን ነገረኝ፡፡

*ግዮን፡- HR 2003 ሎቢ በማድረግ በኩል ዲፕሎማቶችን ለማናገር ፕ/ር አለማየሁ ትልቅ*

**ኃላፊነት ተወጥተዋል የሚሉ ወገኖች አሉና እርሶ በዚህ ዙሪያ ምን ይላሉ?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- መጀመሪያ ጭፍጨፋው ከተፈጸመ በኋላ ሕዳር አካባቢ ክሪስ ሚት የሚባል የሪፐብሊካን ሴናተር ከኒውጀርሲ አዲስ አበባ መጥቶ አቶ መለስን ስለምርመራ ሁኔታው ያናግረውና መለስ "ውጣልኝ" ብሎ ያባርረዋል፡፡ ይኽ ሰውየ አሜሪካ ይሄድና ኢትዮጵያ ውስጥ ስለነበረው ጭፍጨፋና ሰብዓዊ መብት ረገጣ ረቂቅ ማውጣት ይጀምራል፡፡ ሪፐብሊካኖቹ ሥልጣን ሲያጡ እርሱ ቦታውን በመልቀቁ ጀንዋል ፔን የሚባል ግለሰብ ጉዳዩን ያዘው፡፡ የዚህ ረቂቅ ስያሜው "Ethiopia Democracy Accountability" ይባላል፡፡

በዚህ ላይ ያሉት ዋና ሃሳቦች በኢትዮጵያ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት መርምሮ ለፍርድ ማቅረብ፣ ትክክለኛ ምርጫ እንዲደረግ የምርጫ ሂደቱን ማከናወኛ የአሜሪካ መንግሥት በገንዘብ እርዳታ እንዲያደርግ ማስቻል፣ ሀገር ውስጥ ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲጠበቁ ማድረግ ወዘተ... የሚሉ ነበሩ፡፡ እንግዲህ እኔ በዚህ ላይ የተሳተፍኩት አንደኛው አሜሪካ ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያኖችን ስለሕጉ ማስተማርና የተለያዩ ተሳትፎዎችን እንዲያደርጉ መቀስቀስ ሲኾን፣ ኹለተኛው ደግሞ በኮንግረስ ውስጥ አማካሪዎችን፣ ሴናተሮችንና ስቴት ዲፓርትመንት ውስጥ ያሉ ሰዎችን ማናገርና በጽሑፍ መስጠት አልፎም በተለያየ አጋጣሚ መጎትጎትና ስለጉዳዩ ትኩረት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ በዘለለ ደግሞ ጉዳዩን በጋዜጦችና በተለያዩ ዐውዶች ላይ በመጻፍና በማስተጋባት ነው፡፡

በአጠቃላይ የጭፍጨፋ ሁኔታውን ሁልጊዜ በተገኘው አጋጣሚ ወደ አደባባይ ማውጣትና ሰው እሱን ብቻ እንዲያወራ ማድረግ ነበር፤ ዋናው ዓላማ፡ ፡ ምክንያቱም ይኽን በማድረግ የወያኔ መንግሥት ላይ ትልቅ ቀውስ መፍጠር ይቻላል፡፡ ቀደም ሲልም ያላቸው ተቀባይነት የወረደ ስለኾነ በዚያው ልክ ተሰሚነት እንዳይኖራቸው ያደርጋቸዋል፡፡ በሌላ በኩል የእኛ የቅስቀሳ ሂደት በዚህ ልክ እየገፋ እያለ የ2002(በኢትዮጵያ) ምርጫን አድርገው መቶ በመቶ አሸነፍን አሉ፡፡ ወዲያው የኦባማ መንግሥት አሜሪካ ላይ ተሰየመ፡፡ ይኽ መንግሥት ደግሞ ቅልጥ ያለ የወያኔ ደጋፊ ነበር፡፡ እናም በኦባማ ላይ ጫና እንዳናሳድር እርሱም ጥቁር ስለነበር በብዙ መልኩ ተወጥሮ ተይዞ ነበር፡፡ ወያኔዎችም የአልሻባብን መከሰት እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ከኦባማ መንግሥት ሚሊዮን ዶላሮችን መቀበል ቻሉ፡፡

በእኛ በኩልም ይኼን እንቅስቃሴ ይመሩት የነበሩ የተደራጁ ወገኖች ተስፋ በመቁረጥ መቀጠል ሳይቻላቸው እየተንጠባጠቡ ቀሩ፡፡ እኔም በግሌ በተለመደው መልኩ በጽሑፍ ቀጠልኩ፡፡ ምክንያቱም እኔ ያቅሜን ማድረግ ከቻልኩ ሌሎችም ፈለጌን ተከትለው የራሳቸውን አስተዋፅዖ ያደርጋሉ፡፡ ያን የማያደርጉ ከኾነም በራሳቸው ነፃነትና ሕልውና ላይ እየቀለዱ ይኖራሉ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ነፃነት ዝም ብሎ የሚገኝ ሳይኾን ሁሉም በየፊናው መራር ትግል አድርጎ የሚጎናፀፈው የሰብዓዊነት ጥግ በመኾኑ ነው፡፡

**ግዮን፡- እርሶ የህወሓትን መንግሥት እንዴት ይገልፁታል? በውድቀቱስ የተሰማዎት ስሜት እንዴት ይገለፃል?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- እኔ ወያኔ እንደሚወርድ ተንብዬ ነበር፡፡ ይኽን ትንቢት 2013 በፃፍኩት ጽሁፍ ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡ በታላቁ መጽሐፍ "የራሱን ቤት የበጠበጠ ግለሰብ ንፋስ ይዘግናል" የሚል ጥቅስ አለ፡፡ እኔም ህወሓቶችን ያልኳቸው "የኢትዮጵያን ቤት በጥብጣችኋልና መጨረሻችሁ ነፋስ ወይም ጉም መዝገን ነው የሚሆነው" ብዬ ተንብየላቸው ነበር፡፡ "ሁልጊዜ በጭፍጨፋና በዘረፋ እንኖራለሁ ብላችሁ አታስቡ በታሪክ ብዙ ጨፍጫፊና አንባገነኖች መጥተዋል፣ መጨረሻቸው ግን እጅግ አስከፊ አፈራረስ ነው፡፡ ስለዚህ ስህተታችሁን አርሙና ወደ ትክክለኛው መስመር ተመለሱ" የሚል ምክርም ለግሼ ነበር፡፡ ነገር ግን በታሪካቸው እድሉን አግኝተው ያልተጠቀሙ ብቸኞቹ አንባገነኖች ናቸው፡፡ በዚያ ጽሑፌ ስለኢትዮጵያ ትንሳኤ ሌላም የጠቀስኩት ነገር ነበር፡፡ "ለኢትዮጵያ ትንሳኤ የሚኾኑት ወጣቶች ናቸው" በማለት፡፡ የእኛ ትውልድ ከስሟል፣ ነገር ግን ወጣቶች ናቸው ኢትዮጵያን የሚድኗት፣ አንድ ወጣት ይመጣል ሀገሪቱን የሚታደጋት ብዬ ተናግሬም ነበር፡፡ እናም ከኹለት ዓመት በፊት ዶ/ር ዐቢይ ወደ ሥልጣን ሲመጣ እኔ ብዙ አልገረመኝም፡፡ ይኽ ማለት ደግሞ አውቃለሁ ማለቴ ሳይኾን ፖለቲካውን በአንክሮ ለተከታተለ ሰው ይኽ እንደሚኾን እንደማይጠፋው ለመግለጽ ነው፡፡

ዶ/ር ዐቢይ የተሾመና ቃለ-መሀላ የፈፀመ ዕለት ቪኦኤ ቃለ መጠይቅ አድርጎልኝ ነበር፡ ፡ እዚያ ቃለመጠይቅ ላይ የተናገርኩት ከፍ ሲል እንደጠቀስኩት "ይመጣል ያልኩት ሰው ይኼ ነው፣ የኢትዮጵያን ትንሳኤ የሚያሳየን እርሱ ነው" የሚል ነበር፡፡ ዶ/ር ዐቢይን ከዚያ በፊት በፍፁም አላውቀውም ነበር፡፡ በተጨማሪም በቃለ መጠይቁ ላይ ዐቢይን መቶ በመቶ እንደምደግፈው ተናግሬ ነበር፡፡ ዐቢይ በተሰየመ በስድስተኛው ቀን ላይም ይኽንኑ ድጋፌን የሚገልጽ ጽሑፍ አውጥቻለሁ፡፡

"በርታ፣ ወደፊት ሂድ፣ ቀጥልበት" የሚል ይዘት ያለው ጽሑፍ ነው፡፡ ስለዚህ የህወሓት ወያኔ መንግሥት ወደቀ የተባለ ግዜ በአዕምሮዬ በቂ ግንዛቤ ስለነበረኝ ብዙ አልደነቀኝም፡፡ ነገር ግን በወቅቱ የእነርሱ በሰላም መሰናበት በጣም ነበር ያስደሰተኝ፡፡ ትናንትም ኾነ በይበልጥ ደግሞ ዛሬ የህወሓት መንግሥትን የማየው በአሸባሪነት ነው፡ ፡ ይኼን ስል ዝም ብዬ ሳይሆን ድርጅቱ(ህወሓት) "Global Terrorism Data Base" በሚለው መዝገብ ላይ የተመዘገበ ስለሆነ ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ ድርጅቱ እኔ አሸባሪ ስለው እነርሱን ለማጥላላት ፈልጌ ሳይሆን መሠረታዊ መረጃን በመያዝ ነው፡ ፡ የህወሓትን ማንነት ሥራው ይገልጠዋል፡፡ አሁን እያደረጉ ያሉት ደግሞ ከአልሸባብ፣ ከቦኮሐራም፣ ከአይሲስ ወዘተ... የባሰ ድርጊት ነው፡፡ ስለዚህ ይኽ ድርጅት አሸባሪነት እውነተኛ መገለጫው ነው ማለት ነው፡፡

**ግዮን፡- እንደሚታወቀው ከለውጡ በኋላ በውጪ ያለው ኢትዮጵያዊን የሀገሩ ልማት ተሳታፊ ለማድረግ በማለም "የዳያስፖራ ትረስት ፈንድ" ተቋቁሞ እርሶ ትልቅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡ ፡ የትረስት ፈንዱ እንቅስቃሴ ምን ያህል ውጤታማ ነው ማለት ይቻላል? ከመንግሥትስ ጋር በምን ዓይነት መልኩ እየሰራችሁ ነው?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- እ.ኤ.አ ነሐሴ 2018 ጠ/ሚኒስትሩ አሜሪካ መጡ፣ መጥተውም ከማክያቶ ቀንሳችሁ 1 ዶላር ብትሰጡ ለሀገር ይረዳል አሉ፡ ፡ እኔ በወቅቱ እንደተረዳሁት ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕለታዊ ገቢው ከአንድ ዶላር በታች ነው፡፡ ስለዚህ እኛ በውጭ ያለነው ዜጎች ከማኪያቶ ቀንሰን አንድ ዶላር ከፈልን ማለት እያንዳንዳችን የአንድ ሰውን ሕይወት ቀየርን ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ሃሳቡ የሚደገፍ ነው፡፡ በሌላ በኩል ዳያስፖራው በፊት የሚታወቀው በመከፋፈልና በመናቆር ስለኾነ አንድ አሰባሳቢና አቃፊ ፕሮጀክት እንዲኖረን በማሰብ የተመሰረተ ነው፡፡ ምክንያቱም ለሀገር ልማት የራስን አስተዋፅኦ ለማበርከትም መሰባሰብ መልካም ስለኾነ ነው፡፡ ይኽ ፈንድ ውሃ ማስቆፈር ይችላል፣ ትምህርት ቤት መሥራት ይችላል፣ ወጣቶችን ሥራ ሊያስገባ ይችላል፣ ለሴቶች የሥራ ዕድል ሊፈጥር ይችላል... ብቻ በጥቅሉ ለበርካታ አገልግሎት ሊውል የሚችል ነው፡፡ ያው በዚህ መልኩ ቢጀመርም ጥሩ እየሄደ መጥቶ አሁን ላይ ወደ ሰባት ሚሊየን ብር አካባቢ ማሰባሰብ ችለናል፡፡ ባለፈው ለኮቪድም 1.2 ሚሊዮን ብር አካባቢ ሰጥተናል፡፡ አሁን በቅርቡ ደግሞ አምስት ፕሮጀክቶችን ፈንድ አድርገናል፡ ፡ ሌሎች ወደ 16 የሚጠጉ ፕሮጀክቶችን ደግሞ ወደፊት በሥራ ላይ እናውላለን የሚል እምነት አለኝ፡ ፡ እንደሚታወቀው ኮቪድ ከመጣ በኋላ ብዙ ነገር ተቀያይሯል፡፡ አገር ውስጥ ያለው ችግርም በዝቷል፡ ፡ ለምሳሌ ለተፈናቃይ አምጡ ይባላል፣ ለአንበጣ አምጡ ይባላል፣ ዜጎች ተጎዱ ሲባል አምጡ ይባላል፡ ፡ ችግሩ ከመብዛቱ አኳያ ትንሽ መዳከም አለ፡፡ አሁን ያለው ተግዳሮት ይኽ ብቻ ነው፡፡ በጥቅሉ ትረስት ፈንዱ በዚሁ ይቀጥላል፡፡ እዚህ ብቻ ሳይኾን አገር ቤትም ቦርድ አለን፡፡ በዚህም ተናብበን ለመሥራት እየጣርን ነው፡፡

**ግዮን፡- ቀረ የሚሉት ነገር ካለ ሃሳቦን አጠቃልለው እንዲነግሩኝ ዕድሉን ልስጦት?**


ፕ/ር አለማየሁ፡- በጥቅሉ እስካሁን በመንግሥት በኩል እየተካሄደ ያለው ነገር ይበል የሚያሰኝ ነው፡ ፡ መንግሥት ሕግን በማስከበር በኩል የሚያደርገው እንቅስቃሴ በሕዝቡ ዘንድ ሙሉ ድጋፍ እንዳለው ተገንዝቤያለሁ፡፡ ይኼ ደግሞ መቀጠል አለበት፡፡ በሌላ በኩል የመንግሥት ሕግ የማስከበር ዘመቻ በትግራይ ብቻ ሳይኾን በሌሎች አካባቢም ሊኾን እንደሚገባና ሕዝብም ድጋፍ ሊሰጠው እንደሚገባ ማስታወስ እፈልጋለሁ፡፡ ጥፋት በተፈጠረ ቁጥር ራስን ማስተማር መልካም ነው፡፡ ስለዚህ የኔ መልዕክት መንግሥት ከዚህ የተማረውን ነገር በተግባር መግለጥ አለበት የሚል ነው፡፡ እኔ የተማርኩት ለዚህ ሁሉ ጥፋት ሊያደርሰን የቻለው ከውጭ የመጣ ጦስ ሳይኾን ሀገር በቀል የጥላቻ በሽታ ነው፡፡ ለዚህ ያበቃን ከልባችን የሚመነጨው የጥላቻ መንፈስ ነው፡፡ ለዚህም መነሻው ሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚደርገው ጥረት ውጤት ነው፡፡

ይኽ ነገር ደግሞ የሀገር ጠንቅ ስለኾነ የሃይማኖት አባቶች፣ የፖለቲካ መሪዎች፣ የሲቪክ ማኅበራት ወዘተ... ከዚህ ትምህርት ወስደው ለትውልድ ትምህርት መስጠት መቻል አለባቸው፡ ፡ ከአሁን በኋላ መደረግ ያለበት በእኩልነት ላይ ተመስርተን ሀገራችንን መገንባት አለብን፡፡ ሕግም መከበር አለበት፡፡ የሕግ የበላይነትነም ሊጠበቅ ይገባል፡፡ የግለሰብ መብት ሊጠበቅ ይገባል፡፡ ሌላ ምርጫ የለም፡፡ ወጣቱ ላይ ያተኮረ ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ወጣቱ ከስድሳ በመቶ በላይ ስለኾነ የምትገነባው አዲሷ ኢትዮጵያ በወጣቶች ሊኾን ይገባል፡፡ የኔ ትውልድ ኢትዮጵያን ያየበት መንገድ መጨረሻ ክሽፈት ነው፡፡

ስለዚህ የምትገነባው ኢትዮጵያ ከዚያ ትውልድ የእሳቤ ቅንብብ ውጭ በኾን መልኩ በወጣቱ መኾን አለበት፡፡ የኢትዮጵያ የወደፊት እጣፈንታ ያለው በወጣቶቹ ላይ ነው፡፡ ሌሎቻችን ተሳፋሪዎች ነን፡፡ አሁን የተፈጠረውን ነገር ለማስወገድ በእኔ እምነት ወጣቱ የእኛ ትውልድ የሰራውን ሕገመንግሥት ቀድዶ መጣል ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በዘር ከተደራጀ ሕገመንግሥት የፀዳ አዲስ፣ አመቺና አካታች ሕግን ማርቀቅ ይኖርበታል፡፡ ለክልልና ለዘር እውቅና የነፈገ ሕግ ማርቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ይኽ ማለት ግን አዲሱ ሕግ ራስን ማስተዳደርን ያስቀራል ማለት አይደለም፡፡ በጥቅሉ ከልጊቁ ጀምሮ በዚህ ዙሪያ ጠንካራ ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡

ለምሳሌ የኢትዮጵያን ብልፅግና በተመለከተ እስካሁን ዳያስፖራው ያደረገው ነገር የለም፡፡ ዓለም ላይ ያሉ ትውልደ ኢትዮጵያውያን አንድ በመኾን የኢኮኖሚስቶች ማኅበር አላቸው፡፡ ማኅበሩ ግን ለኢትዮጵያ ብልፅግና የፈየደው አንዳች ነገር የለም፡ ፡ ስለዚህ ወደፊት ይኼ መቀየር አለበት፡፡ ሁሉም በየሙያው ለውጥ ማምጣት ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ በጥቅሉ የጥላቻ ነገሮች ሁሉ ተደምስሰው ሀገሪቱ በወጣቶች ወደፊት መራመድ ይኖርባታል የሚል መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ፡፡

**ግዮን፡- ለነበረን ቆይታ በአንባቢያን ስም ከልብ እናመሰግናለን፡፡**



# ሐሙስ ቅዱስ ወይስ እርኩስ?

ያዕቆብ ብርሃኑ

ከሠይፋችሁም፣ ከእግዜራችሁም በላይ ህሊናዬን እፈራዋለሁ:: አምነዋለሁም:: በጉዳዩ ላይ ከክርስቶስ ጋር እስከመሟገት ድረስ ንባቤን አልጠረጥረውም:: እኔ እውነቴን ለመተያያነት አላረክስም:: በስሌት መጻፍ አይሆንልኝም:: ይኸው እጽፋለሁ...

ይሄን መጽሐፍ(አፍ) እስካጋምሰው ድረስ ንባቡ አሰልቺ ሆኖብኝ ደጋግሜ ለማቋረጥ አመንትቼ ነበር:: በአስራ አምስት ዓመታት በላይ ንባቤ እንደዚህ መጽሐፍ ተራኪው፣ ደራሲው እና ገጸባህሪያቱ በአተራረክ ሂደት ቅጥ በሌለው ሁኔታ የተዘበራረቁበት ሌላ ልብወለድ አጋጥሞኝ አያውቅም:: ብዙ ገጾች ላይ በግርጌ ማስታወሻ መልክ የተሰነቀሩ ተቀጥላ ታሪኮች ከዋናው ታሪክ በምን ተለይተው የግርጌ ማስታወሻ ላይ እንደሰፈሩ እንኳን ግልጽ አይደለም::

በዐረፍተ ነገር አሰጋገሩ አዳም ከእኛ ዘመን ይልቅ ለእነከበደ ሚካኤል ዘመን የሚቀርብ ይመስላል:: ፍዝዝ ያለ፣ ነፍስን ለመንዘር ተናዳፊነት የሚጎድለው፣ ፈራ ተባ የሚል ጅል መካሪ የሰነዘራቸው የሚመስሉ ትርክቶች መጽሐፉን ገጽ እስከ ገጽ ሞልተውታል:: ገጸባህሪያቱ እንደ ትንኝ፣ እንደ ብናኝ የቀለሉ፣ የቀጠኑ ሆነው ለመለየት የሚፈታተን ትኩረት ይፈልጋሉ:: ምናልባት ከአንድ ሁለቱ በስተቀር...

እያንዳንዷ ታሪክ በቀጭን መስመር ላይ የተሰመረች ደብዛዛ ሀቲት ነች:: ቀጭኗ ድር ግን ትብታቧ ረጅም ነው:: ከጦስኝ እስከ ዝንጀሮ የሚያዛምድ፣ የሚያጋምድ ሰላላ ሀዲድ አስምራለች:: አዳም እንደ ተራኪ ያገኘውን ቅራቅቦ ሁሉ እያግበሰበሰ የሚነጉድ ለጋ እብድ ይመስላል:: ምንም ብጣሽ ታሪክ አይንቅም:: ለመጽሐፉ ትርክት ፋይዳ ያለውንም፣ የሌለውንም ሽርፍራፊ ትርክት ሁሉ እየለቃቀመ ይደርታል:: ድርሰት ግን ዘገባ አይደለም(writing isn't all about narrating the whole story)... የሚያጫውተው የሚያስቆዝመው ጠነን ያለው፣ የተተወው(void) የሆነው ነገር እኮ ነው::

የአዳም ረታ ልብወለዶችን ማንበብ ለሃያ ዓመታት የተረሳ ቤት ውስጥ የተዘረገፉ ኮተቶችን ቆጥሮ እንደመረከብ ያለ አታካችነት አለበት:: ሁሉንም መጻሕፍቱን ለማንበብ ደጋግሜ መሞከሬ ባይቀርም ተሳክቶልኝ ሁለቱ ያነበብኩለት ‹ግራጫ ቃጭሎችን› ብቻ ነው:: በዚህ በመጽሐፉ (አፍ) ውስጥ አዳም ከቁንጽል የህክምና ጽንሰሐሳቦች ጋር የመጣበቅ፣ ብዙ ጭብጦቹንም ከዚያው የመምዘዝ ችክታ አይበቼበታለሁ:: በበኩሌ አዳም እንደደራሲ ከማሳየት ይልቅ መንገር የሚቀናው ተራኪ ሆኖ ተሰምቶኛል:: በመጽሐፉ ውስጥ የሚጥም፣ የማይጥም፣ አስማት፣ ምትሃት፣ ድንበር ዘለልነት አበዛዙ ለጉድ ነው:: በስመ ድኅረ ዘመናዊ የፈጠራ ነጻነት እንዴት ድርሰት ፍጽም ገዥ መርኅ ያጣ መረን ይሁን? የአዳም ረታን ልብወለዶች አስቀድሞውኑ ታኝከው በተተፉት የኤዚስተንሻሊዝምና የአብዘርዲዝም መነጽሮች ለመተንተን የተሽቀዳደሙት ትንታጎች፣ ስለ ሥርዓተ ነጥብ ሲነሳባቸው ግን ሕጉ ምን ይሰራል? ይሉናል:: ህጉ የሚሰራው ለማድነቅ ብቻ ነው እንዴ?

ይሄንን ጨምሮ የአዳምን መጻሕፍት ሴቶቻችን ስለምን አብዝተው እንደሚወደዱለት የገባኝ እስኪመስለኝ ድረስ ነገርዬው ሀሜት መሳይ ቀለም አለው... ሥራ ፈት ጋለሞቶች ቡናቸውን እያንቃረሩ የሚያባዝቱት ዓይነት እትትት - ብትትት... በመሀል ከተደነቀረው የራሚሱ(አቡ) ትረካ በስተቀር የተቀረው ሁሉ በትክክል እንደዛ ነው:: (ሴቶቻችን፣ ስለስፖርት፣ ፖለቲካ፣ ጽንሰ ሀሳብ፣ ታሪክ፣ እንቶፈንቶ ከምታስለቻቸው ይልቅ ስለማያውቁት ታክሲ ላይ ያገኘሽው ልጅ ብታወራላቸው እንደሚመርጡ በማተት እንዳሰለችህ አትፈልግም መቼስ አይደል?) ይሄን ይሄን ሁሉ ሳስብ አዳም በፊሽካ እየተጠራራ ከሚያዳንቀው ይልቅ፣ ጠጣሩን እውነት እየጋተ የሚያነቃው፣ የሚያተጋው፣ ባስ ሲልም የሚያስደነግጠው ደፋር ሐያሲ ያስፈልገው ነበር ይሆን? እላለሁ:: ኸረ ከዚያም አልፌ የአብዛኞቹን አድናቂዎቹን ኪነ ንቃት(Artistic consciousness) እስከመጠራጠር ደርሻለሁ::

አዳም በመጽሐፉ የመውጫ ገጽ ላይ ‹የድርሰቱ ቅርጽ› በሚል ርዕስ ሥር ስለ መጽሐፉ ያሰፈረው ሀተታም አስገርሞኛል:: እንዴት በአንድ መጽሐፍ ላይ ራስህን ደራሲም ሀያሲም አድርገህ ትሾማለህ? በበኩሌ ይሄን ሌሎች መጻሕፍቱም ላይ ጭምር የሚከውነውን ድፍረቱን በአንባቢዎቹ በነጻነት የማሰብ መብት ላይ እንደተሰነዘረ መራር ንቀት እቆጥረዋለሁ:: ሲፈልግ አንባቢው ለዘለዓለም ሳይረዳው ይቅር እንጂ ደራሲው በድርሰቱ የቅርጽና ይዘት ነጥቦች ላይ ምንም የማለት መብት የለውም:: አንባቢው ሀሳቡን በመሰለው መልኩ እንዲያንሸራሽር ሊተውለት ይገባል::

አዳም ባህላዊ የልጅነት ጨዋታዎችን ለድርሰቱ ቅርፅ መጠቀሙን አደንቃለሁ:: ቅርጹ ግን ይሄን የሚያክል ጥልፍልፍ ታሪኮች ተደራርበው የሰሩትን ሙሉ የልብወለድ ታሪክ ለመሸከም የሚያስችል አልነበረም:: አዳም የድርሰቱን እንደ ሚካኤል አንጀሎ ‹Battle of centaurs› የጥበብ ሥራ በጭካኔ የተዛዘለ፣ ዝግ ያለና አማተሪሽ አጀማመር ሕጸጽ ለመሸፋፈን ይህችን የመውጫ ቃል እንደጻፈ ይገባኛል:: እንዲህ ያለ አደናጋሪ ነገር ገጥሞት ሳይሆን አይቀርም ያ ገመሬ ዝንጀሮ «የምናውቃትን ክምር ገለባ አለበሷት::» የምትል ሽንቋጭ ብኂል ያቀበለን:: ነገሩን በውግዘት ጀምሬ በውግዘት እንዳልጨርሰው በንባብ ሂደት ነፍሴን የመዘመዙ አንድ ሁለት ጥያቄዎች አንስቼ ጥቂት ልቆዝምባቸው...

## ሐሙስ ቅዱስ ወይስ እርኩስ?

ይሄንን መጽሐፍ የሚያነብ ሰው «አስቀድሞ ምንም አልነበረም:: ከቦዘነ ጭፍግግ አድማስ በታች ሥራ የፈቱ አራት ጎረምሶችና አንዲት ልጃገረድ ብቻ...» ቢለን ተሳስተሃል ልንለው አቅም ይኖረን ይሆን? ሲጀምር ቅዱሱና እርኩሱ ሐሙስ ተጋምደው የፈጠሩት የሚመስል ጎነ ሦስት ታሪክ አለ:: ነገርየው ሲራኖ በተሰኘውን ተውኔት ላይ የምንመለከተው በትዕንግርታዊ አፈጣጠሩ ተገፍቶ የተቃኘ ስል ደመነፍስ ባዳበረው ሲራኖ፣ እሱ በሚወዳት ሩክሳን እና እሷ በምትወደው ክርስቲያን መካከል የተፈጠረውን ሦስትዮሻዊ (triangular) ቅርጽ የሚመስል ነገር አለው:: ቢሆንም ትረካው አሁንም አሁንም ስለሚዋልል ቅርጹ አንድ ወጥ አይደለም:: ስብስባቸው በአንድ መግነጢስ የሚታዘዙ አራት ቅስቶችን የሚያቅፍበት አጋጣሚ ነበር::

«ይሄ የወጣቶቹ የስብስብ ቅርጽ ብዙ ጊዜ አይለወጥም:: አቅደውት ነው? አንዳንድ ጊዜም ለመሮጥና ወዲያ ወዲህ ለመበታተን ያቀዱ ይመስላሉ:: ምናልባት ወዳጅነታቸው ውስጥ የተገነባው ግን የተደበቀው ጊዜ የሚያወጣው የሕይወት ጉዞ በጨረፍታ እራሱን ሲያሳይ ይሆናል:: ሁሉም ነገር ተለዋጭ ከሆነ በረሃው ካበበ፣ የአበበው ከረገፈ፣ የረገፈው ከጸደቀ እንዲህ የተሰበሰቡት ወጣቶች የማይበታተኑበት [ምን] ምክንያት ይኖራል?» ገጽ 49

ተረት እስኪመስል ድረስ ሁሉም ነገር የተከናወነው በአንዲት ሴት ከንፈር ነበር:: ደጋግሞ አብቦ ደጋግሞ የሚጠወልግ የወጣት ትኩስ ፍላጎት እንደ ቢራቢሮ ይቅበዘበዛል:: ስሜቶቻቸው ከምራቅ የቀጠኑ፣ ከጥቅሻ የፈጠኑ ስስና ተለዋዋጭ ናቸው:: በዚህ ላይ እነዚህን ሽልምልም ስሜቶቻቸውን በነጻነት እንዳያስታሙ ከወዲያም ከወዲህም የሚያካልቡ አደናቃፊዎች ጥቂቶች አይደሉም::

ግዕዛዊያን አባቶች ሐሙስ የሳምንቱ አምስተኛ ዕለት መሆኑን ለማመልከት ‹ኀምስ› ከሚለው የግዕዝ ቃል ተወርሶ የተሰየመ ነው ይላሉ:: አበቃ:: ትንሽ የተለየ ዘርዘር ያለ ብያኔ የምናገኘው ፍለጋችንን ወደ ፀሎተ ሐሙስ ካዞርን ብቻ ነው:: እንግዲህ በውል ካልተገለጹልን ሐሙሲቶች(ይባል ይሆን?) በአንዷ ቅድስናና እርኩሰትን ደርባ በተከናነበችው በዚያች እለት ተራኪያችን ታሪኮቹን ማድራት ጀመረ:: ቢሆንም ይሄኛው ሐሙስ እንዲያው በረቡዑ እና አርብ መካከል የቆመ ዕለት ነበር ብለን ብቻ የምናልፈው አይሆንም:: ነገር ግን ካልጠፋ ቀን ተራኪያችን ስለምን ሐሙስን መረጠ? እንጃ!

ነገር ግን መሲሁ ‹እኔን ምሰሉ ብሏልና› በሁሉ ነገራችን ልንመስለው ግድ ይላል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪከች ላይ እንደምንረዳው ሐሙስ የመታጨት ዕለት ነው:: ‹የሰው ልጆች ከኃጥያት ቀንበር ነጻ ይወጡ ዘንድ› ለመከራ፣ ለግፍ ተላልፎ ለመሰጠት የመታጨት ዕለት... ታሪኮቹ ሲተረኩልን ሐሙስ ሰቅለተ አርብን ለመርገጥ ብዙ የሰኞና የማክሰኞ ሰልፈኛ ዕለታትን በትዕግስት ማሳለፍ ነበረበት:: ሲያልቅ ግን ሐሙስ እርኩስም ቅዱስም ለሆነባቸው ሁሉ ስቅለተ አርብ ነበር:: አቸነካከራቸው ቢለያይም ቅሉ ሁሉም ገጸባህሪያት የምኞታቸው ሰልፈኛ እያዳፋ ወስዶ የወሸቃቸው ቅርቃር ውስጥ ነበሩ:: የአበበው ጠውልጓል... ለማየት የሚያስጎመጀው ለማየት አጸይፏል... ሲያልቅ እርኩሱም ቅዱሱም ሐሙስ ተሸኝቶ አርብ ነበር:: ትንሣዔን የካደ ስቅለተ አርብ...

ሌላ... ደራሲው በኮለሴ ባርያው በኩል የማሰነበት ቅዠትን የሚያስከነዳ ሰውን ከዝንጀሮ የሚዳቀልበት ታሪክ አለው:: ኮላሴን አሳዳጊ አባቱ በአንድ አሳቻ ሌሊት እንቅልፍ አምቢ ስላለው ከቤት በወጣበት አፍታ ገደል ስር ከሚራኮቱ ዝንጀሮዎች መካከል አገኘው:: ነገሩን ደብቆ ከዘመድ እንዲያሳድግ እንደተቀበለው ለጎረቤት ለማሳመን አልተቸገረም:: ታሪኩ ሲጀምር ይሄን ያህል ልሙጥና ፍዝ ነበር:: ኮላሴ እያደገ ሲሄድ ግን ፊቱ በጸጉር ተሸፈነ:: በተለይ በልጁ ጌርሳሞት ሲመጡበት ከሰዋዊነት በተለየ ቁጡና ምህረትየለሽ ሆነ:: አዳም በቅጠላቅጠል ተመጋቢነቱ በኩል ኮላሴን ከዝንጀሮ እንድናዛምደው ያደረገው መታተር የሰራለት አልመሰለኝም:: ዝንጀሮዎች ከቅጠላቅጠል ይልቅ ፍራፍሬና ሥጋ መብላት እንደሚወዱ አያውቅም ነበር ይሆን? ደራሲው ይሄን ያህል ሰውን ከዝንጀሮ የሚያዋውል ጭብጥ ለመምዘዝ ሲደፍር ይህችን ትንሽ ዝግጂት ማድረግ ሊከብደው አይችልም::

ሌላው ጥያቄ የሚፈጥረው ጉዳይ ወድቆ የተገኘበት ሁኔታ ነው:: ከዓመታት በፊት በእንግሊዞ Royal society open science journal ላይ ታትሞ ባነበብኩት አንድ ጥናት መሰረት የዝንጀሮ እናቶች እንኳን በሕይወት ያሉ የሞቱ ልጆቻቸውን ከ10 ቀናት እስከ ወራት ተሸክመው ይዞራሉ:: በልጆቻቸው የመጣውን እስከሞት ይፋለሙታል እንጂ አይሸሹለትም:: እናስ የኮላሴ ባርያው ነገር እንዴት? በበኩሌ ከቀደመው ታሪክ ይልቅ በመጨረሻ ኮላሴ ወደ ጥንተ ፍጥረቱ ወደ ዝንጀሮዎቹ የተመለሰበትን ሁነት የተረከበት ጉልበት የበለጠ ትንፋሽ ያለውና ድራማቲክ እንደሆነ ተሰምቶኛል:: ይህ ሁሉ የሆነው ግን ሐሙስ ተጀምሮ እስከ አርብ ድረስ ነበር:: ነገር ግን ሐሙስ ቅዱስ ወይስ እርኩስ? እንጃ!

# ከህወሓት በኋላስ? አዲሱ የትግራይ ፖለቲካ ፍኖት!

በዝግጅት ክፍሉ

## መግቢያ

ትግራይ ልክ እንደሌላው የሀገራችን ክፍል፣ በኢትዮጵያ ጥንታዊም ኾነ ዘመናዊ የሃገረ መንግሥት ታሪክ ውስጥ ጉልህ ስፍራ አላት፡፡ በረዥሙ የታሪክ ባቡርም አንድ የግዛት አሃድ እና የፖለቲካ ተዋናይ ኾና ቆይታለች፡፡ ለኢትዮጵያ መልከ ብዙ ሥልጣኔ መሠረት መኾኗም ግልጽ ነው፡፡ የትግራይ ሕዝብም በዘመናት የአብሮነትና የአንድነት ታሪኩ ከወንድም ኢትዮጵያዊያን ጋር ተዋሕዶ ዛሬ ደርሷል፡፡ ኢትዮጵያዊያንም በየትኛዎቹም የታሪክ አጋጣሚዎች በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተቃጡ የሉዓላዊነት ፈተናዎችን በመቀልበስ ወንድምነታቸውን በተግባር አስመስክረዋል፡፡ በአጠቃላይ የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያን በደሙ ምሎ፣ በአጥንቱ ገዝቶ በማስከበር እዚህ ማደረሱ ነጋሪ የማያሻው ንጥረ ሀቅ ነው፡፡ ይኽ ትናንቷ በጽልመት ሲሞሸር ሩብ ክፍለ-ዘመን በባጀባት ሀገር የተሸፈነ የታሪክ ገጽ ቢኾንም ሳይታከት መነገር ያለበት ኢትዮጵያዊ እውነት መኾኑ ግን ጥርጥር የለውም፡፡

ህወሓት ሥነ-ፍጥረቱ "አሃዱ" ከተባለበት ቀን አንስቶ ግን እንዲህና እንዲህ ያሉ ደማቅ ታሪኮች በጥቁር መጋረጃ ይጋረዱ ዘንድ ግድ ኾኗል፡፡ በትግራይም እንግዳና ትንግርት የፖለቲካ ባሕል ተፈጥሯል፡፡ ዛሬ ህወሓት የአገልግሎት ዘመኑን ጨርሶ ወደታሪክ ገጽነት ተቀይሯል፡፡ መንፈሱ፣ ስሁት አስተሳሰቡና ፍኖቱ ግን ባሉበት ረግጠዋል፡፡ ይኽንን በወጉ ማረምና ማስተከከል ደግሞ የነገሮች መንደርደሪያ ነው፡፡


## ህወሓት እና ወያነ

ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ በእንግሊዝኛው `Tigray People Liberation Front` የሚል አቻ ሥያሜ ተሰጥቶታል፡፡ "ወያነ" የሚለው ቃል `Liberation` የሚለውን እንዲተካ ተፈልጎ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ትክክለኛ ፍቺው እንዳልኾነ ግን ግልጽ ነው፡፡ በትግራይ መሳፍንት ከተመራውና በቀዳማዊ ዐጼ ኃይለሥላሴ መንግሥት ላይ አመጽ በማድረግ ከሚታወቀው "ቀዳማይ ወያነ" እንደተወሰደ ይነገራል፡፡ ህወሓትም ይኽንን በኩራት ይናገራል፡፡ ብዙዎች ግን ሥሙን እንጂ ግብሩን አልወሰደም ሲሉ ይቆጨበታል፡፡ በዚህ ረገድ ነባሩ የህወሓት ታጋይ አቶ ሊላይ ኃይለማርያም ረዳ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ "ወያነ የተባለውን ቅዱስ ሥም አርክሶብናል" ሲሉ ድርጅቱን ይኮንኑታል፡፡

ጠ/ሚኒስትር ዐቢይም በአንድ መድረክ "ወያነ" የተባለው ቃል በድርጅቱ ስያሜ ውስጥ ሽብልቅ ኾኖ የገባበት አመክንዮን አንስተው አስተያየት ሰጥተው ነበር፡፡ "ህወሓት የሰፊውን የትግራይ ህዝብ ድጋፍ ለማግኘት ቃሉን ተጠቅሞበታል" ነበር ያሉት፡፡ ይኽ ዐይነቱ ታሪክን የመዝረፍ በሽታ ድርጅቱን የኋላ ኋላ የተለያዩ አካባቢዎችን በኃይል "የእኔ ናቸው" ብሎ እስከመንጠቅ አድርሶታል፡፡ በዚህ ብቻም አልተገደበም፡፡ ሥርዓተ ትምህርቱን ተጠቅሞ ተራራ እስከ መዝረፍ ወደ ደረሰ ውንብድናም ሄዷል፡፡ እነኚህ ሁሉ ሁነቶች ታዲያ የሚነግሩን አንድ እውነት አለ፡፡ ይኽም ህወሓት ከትግራይ ሕዝብ ነባር የባሕል አንብሮ ተቃራኒ የኾነ ዕሳቤ ይዞ መከሰቱን ነው፡፡ ይኽ አዲስ የፖለቲካ ባሕል ያለፉትን ዐርባ ስድስት ዓመታት በትግራይ ምድር "ገዢ" እንዲኾን መገደዱ አያሌ ተላውጦዎች(Factors) ክሱት እንዲኾኑ አድርጓል፡፡ ቀዳሚው ደግሞ የፖለቲካ ባሕል ብልሽት ነው፡፡

## የተበላሸው የትግራይ ፖለቲካ

አቶ ጌታቸው ረዳ የተባሉ "የኢትዮጵያ ሰማይ" ድረ-ገጽ አዘጋጅ ከዓመታት በፊት "ቀዳማይ ወያኔ፤ ዓድዋ እና የካቲት11" በሚል ርዕስ ዘለግ ያለ ጽሑፍ አስነብበው ነበር፡፡ ጽሑፉን በጥልቀት ለማንበብ የሞከረ ከሚዘግናቸው አያሌ ጭብጦች አንዱ ህወሓት ለማይጠረቃው የሥልጣንና የበቀል ጥሙ የትግራይን ፖለቲካ ምን ያህል እንዳበላሸው ነው፡፡ እብለት፣ ቅጥፈት፣ ስሁት ፕሮፓጋንዳ እና አልቦ እብሪተኝነት ትግራይን በዘላቂነት በተበላሸ ፍኖት ወደቁልቁለቱ እንድትገሰግስ ምን ያህል እንደጣረ መረዳት



ይቻላል፡፡ ከፋፋይነት፣ መንደሬነት፣ ጸረ አንድነትና ወንድማማችነት የት ድረስ የድርጅቱና አመራሮቹ ባህሪ እንደኾነ ለመታዘብ ዕድል ይሰጣል፡፡ "ለትግራይ ሕልውና ብቸኛው ጠበቃ እኔ ነኝ" የሚል መለከት እየነፋ ወደጥልቁ የወረደው ድርጅቱ ገና በጥንስሱ ትግራይን ሳይቀር በአውራጃ በመከፋፈል "ሀቀኛ" እና "ኣባይ" እያለ ሲያባድን ለመኖሩ ተከታዩ ሥነቃል ጥሩ አስረጂ ኾኖ ተገኝቷል፡፡

"ዓድዋ አኽሱም ሽረ ጹሩያት ተጋሩ

ራያ እንደርታ ተምቤን ጎረቤት አምሓሩ"

ማለትም፡-

"ዓድዋ አኽሱም እና ሽሬ የጠሩ ትግሬዎች

ራያ እንደርታ ተምቤን ያማራ ጎረቤቶች"

ህወሓት ገና በዘፍጥረቱ ትግራይን በመነጣጠልና በመከፋፈል ያራምድ የነበረው አቋም ከትግራይ አልፎ የድፍን ኢትዮጵያን ፖለቲካ በእጅጉ አበላሽቶታል፡፡ መንደርና አውራጃ ከመቁጠር የጀመረው ፍረጃ፣ አጥንትና ጉልጥምት በመመርመር ያለንበት ፍዳ ላይ አድርሶናል፡፡ ድርጅቱ ውርስ ያደረጋቸው የተሳሳቱ ዕሳቤዎች ፈተናነታቸው ዛሬም ያበቃ ባይኾም ኢትዮጵያዊያን የነበሩበትን እመቃና ፖለቲካዊ አፈና በጣጥሰው ድርጅቱን ከፈላጭ ቆራጭነት መመንገል ግን ችለዋል፡፡

ትግራይ በዚህ በኩል ህወሓት ያነበረውን ስሁት የፖለቲካ ባሕል ለማራገፍ ፈተናዋ እንደሚከብድ አያጠራጥርም፡፡ ድርጅቱ የትግራይን ሕዝብ በሰዋዊ ጋሻነት ተጠቅሞ በብዙኃኑ ኢትዮጵያዊ የተጠላ ሥርዓቱን መልሶ ለመጫን ባካሄደው ያለፉት ሳምንታት የክህደት ውጊያዎች ያስተጋባቸው የነበሩ ፕሮፓጋንዳዎችና በተጨባጭም ባሰማራው ሠራዊት በኩል ይደመጡ የነበሩ ምክንያቶች የትግራይ ፖለቲካ የት ድረስ እንደተበላሸ መታዘብ ይቻላል፡፡ ጥቂቶቹን መመልከት ለመፍትሔው እንድባጅ ይረዳናል፡-

## ሀ) ፖለቲካዊ እቡይነት (Political Ego trip)

ህወሓት የዛሬ ዐርባ ስድስት ዓመት ወደትግል ሲገባ ያቀነቅን የነበረው መዝሙር የቅርጽም ኾነ የይዘት ለውጥ ሳይደረግበት ወደመቃብር እስከወረደበት ሰዓት ድረስ ቀጥሏል፡፡ "ዘይንድይቦ ኀቦ ዘይንሰግር ሩባ ፍጹም ወይከንየለን…" እያለ በሚቀጥለው መዝመር ውስጥ ጎልቶ የሚደመጠው ይዘት "የሚያሸንፈን ምድራዊ ኃይል የለም" የሚል ፖለቲካዊ እቡይነት ነው፡፡ ይኽ እቡይነት በሃያ ሰባት ዓመቱ የአገዛዝ ዘመን ግንቦት ሃያን ጠብቆም ኾነ ሳይጠብቁ በሚነዙት የፕሮፓጋንዳ ደቦዎች እየታገዘ በትግራይ አሁናዊ የፖለቲካ ባሕል ውስጥ ቀላል የማይባል ስህተት ፈጥሯል፡፡ ይኽ ስህተት በክልሉም ኾነ በሀገር አቀፍ ፖለቲካ ተሳታፊ የኾኑ በርካታ የክልሉ ተወላጆችን ያልተገባ አመለካከት ሰለባ እንዲኾኑ አድርጓቸዋል፡፡ ራሳቸውን ከሁኔታዎችና ከእውነታው ጋር አስማምተው ዘመኑን የሚመጥን አዲስ የፖለቲካ መስመር ለመቀየስ ዳገት ሲኾንባቸውም በስፋት ታይቷል፡፡

አላስፈላጊና ያልተገባ የፖለቲካ እቡይነት መንፈስ ተጠቂ በመኾናቸው ሳቢያም ስለ ድል፣ አሸናፊነትና ሥልጡን ፖለቲካ ያላቸው አመለካከት የተዛነፈ ኾኖ የህወሓት አጫዋች ሲኾኑ ያለፉትን ዓመታት መመልከት ተችሏል፡፡ "የሚያሸንፈን ኃይል የለም" የሚል መሬት ካለው እውነታ ጋር አብሮ መሄድ በማይችል አስተሳሰብ የፊጥኝ ታስረው በመቆየታቸውም ያለፉትን አምስት ዓመታት በተደረጉ የወጣት ንቅናቄዎችም ኾነ ሕዝባዊ ትግሎች ዘመኑን የሚመጥን የአካሄድ ስልት ከመቀየስ ይልቅ ህወሓት ያስታጠቃቸውን የእቡይነት ስሜት እያስተጋቡ ተያይዘው መቀመቅ መውረድን መርጠዋል፡፡ ይኽ አልቦ ማናኽሎኝነት ችግሮችን ጊዜው በሚጠይቀው የሠለጠነ መንገድ ለመፍታት ቁርጠኝነትን ከማሳየት ይልቅ "ጦርነት ባሕላዊ ጨዋታችን ነው" ወደሚል ኋላቀርነት ሲያንደረድራቸውም አሳይቶናል፡፡ ይኽ ግን በብዙው የትግራይ የፖለቲካ ኃይልና ልኂቅ ዘንድ የሚታይ እውነታ ይኹን እንጂ ነገሮችን ከዘመንና ከሀገር ዐውድ አንጻር ተንትኖ ጊዜው የሚጠይቀውን ተገቢ አቋም ለመያዝ ያልተቸገሩ አንዳንድ ግለሰቦችና ፓርቲዎች መኖራቸውን አያደበዝዘውም፡፡

## ለ) የፓርቲና ሕዝብ ተመሳስሎሽ

የሩብ ክፍለ ዘመኑ የህወሓት አገዛዝ በትግራይ ላይ ከከቸቻቸው ክፉ የፖለቲካ ልማዶች ሌላኛው በፓርቲና በሕዝብ መካከል ወሰኑን ያለየ የተመሳስሎሽ ተረክ መንዛት ነው፡፡ ይኽ ልማድ ኦሕዴድ በኦሮሚያ ላይ፣ ብአዴን በአማራ ላይ፣ ደኢሕዴን በደቡብ ላይ፣ ሶሕዴፓ በሱማሌ ላይ፣ አብዴፓ በአፋር ላይ፣… ያልሰራና የከሸፈ(በመርኅም መክሸፍ የሚገባው) ቢኾንም በትግራይ ፖለቲካ ግን የድርጅትን ኀላዌ የሕዝብና የሕዝብ አድርጎ በመኳል በኩል የተሳካ ማደናገር ተፈጥሯል ማለት ይቻላል፡፡ እዚህ ጋር ህወሓት በክልሉ ያለፉትን ዐርባ ስድስት ዓመታት ብቸኛ የፖለቲካ ኃይል ኾኖ ለመውጣት ያደረጋቸውን በትጥቅና በሸፍጥ የታጀቡ ትግሎች መሠረት አድርገን ጉዳዩን "እውነት ላያጣ ይችላል" ብለን መቀበል እንችል ይኾናል፡፡

ነገር ግን በበርካታ የትግራይ ልኂቃን ፣ ምሁራን እና ልዩ ልዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዘንድ ሕዝብና ድርጅትን በእጅጉ የማጣበቅ ልማድ ተንሰራፍቶ ሲሰራበት እንመለከታለን፡፡ ይኽ አስተሳሰብ ጸረ ዴሞክራሲ መኾኑ አያጠያይቅም፡፡ የግለሰቦች በነጻነት የማሰብና የመወሰን መብትን በእጅጉ የሚጋፋ ጠንቀኛ አካሄድ መኾኑም ግልጽ ነው፡፡ ዜጎች የወደዱትን፣ የመሰላቸውንና ይበጃል ያሉትን ሃሳብ በመመርጥ ዴሞክራሲያዊ መብታቸው ላይ ትልቅ ጋሬጣ እንደሚዘነጥፍም አያጠራጥርም፡፡ የዘውግ ፖለቲካ በኢትዮጵያ ሰማይ ኩል መስሎ መታየት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በየክልሉ የሚገኙ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ራሳቸውን ብቸኛ የሕዝብ ጠበቃ አድርገው የመታየት አባዜ ቢኖርም በትግራይ በኩል ስንመለከተው ከኖርነው እውነታ አኳያ ከመዘንነው ግን እምብዛም ነው ማለት እንችላለን፡፡ ለዚህ ነው ህወሓት በቀየደው የትግራይ ፖለቲካ በስፋት የሚታየው ይኽ ዓይነቱ የሕዝብና የድርጅት ጥቅምን የማምታታት አካሄድ በብዙ መልኩ የክልሉን ፖለቲካ አበላሽቶት ቆይቷል ብሎ ለመናገር የሚያስደፍረው፡፡

## ሐ) ከእውነት የተጣላ ፕሮፓጋንዳ

ህወሓት በኢትዮጵያ የሥነመንግሥት ታሪክ ውስጥ ልክ አልባ ኩሸት በማስተጋባት ረገድ ተስተካካይ አይገኝለትም፡፡ ከእውነት የተጣሉ መረጃዎችን በመፈብረክ፣ ከሀቅ የሚቃረኑ ዘገባዎችን በማሰራጨት ወደር የሌለው ድርጅት ነው፡፡ ፕሮፓጋንዳ በየትኛው የመንግሥት ዓለም ያለና የኖረ የገዢዎች መሣሪያ መኾኑ አይታበልም፡፡ አንዳች ፖለቲካዊ ብልጫ(Advantage) ለመውሰድ ሲባል ጥቅም ላይ መዋሉም የተጠላ ስልት አያስብለውም፡፡ በኢትዮጵያ ሁናቴ ግን ውሸት መንግሥታዊ መገለጫ እስኪመስል ድረስ እውነትን አጋድሞ እስከመሰየፍ ጥግ የደረሰ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በመክፈት በኩል ህወሓትን የሚያህል አይገኝም፡፡ ይኽ የድርጅቱ ባህሪ ወትሮም ተገማችና የሚታወቅ ቢኾንም ታንኩንም ባንኩንም ነቅሎ በሸማቂነት መቀሌ ከገባ በኋላ ግን ፍንትው ብሎ ተገልጹዋል፡፡

ባለፉት ሦስት ሳምንታት መንግሥት ድርጅቱ የፈጸመውን ታሪክ የማይዘነጋው ነውር ተከትሎ በጀመረው የሕግ የማስከበር ኦፕሬሽን ይኽ ከእውነት ፍጹም የተፋታ ጭምብሉ በይፋ ተገልጧል፡፡ ተራራ ሳይዝ ያዝኩ ብሎ ማውራት፣ ከከተማ ተብርሮ ከተማ አስመለስኩ ብሎ መፎከር፣ ቀለበት ውስጥ ገብቶ የድል አጥቢያ ላይ ነኝ ብሎ ማወጅ፣ እስካንገቱ አፈር ገብቶ ባለድል ነኝ ብሎ መሸለል፣… ምን ያህል ለእውነት ቅንጣት ታህል ቦታ እንደሌለው ያሳያል፡፡ በሬ ወለደ ብሎ ለማውራት አፍታም የማሸክካቸው ጋዜጠኞች፣ ይኽንንም በሳይንስ ሥም ለመተንተን አንደበታቸውን የማያንቃቸው ምሁራን መኖራቸውን ስናስብ ደግሞ ምን ያህል ከእውነት የተጣላ ፕሮፓጋንዳን ማስተጋባትና ለዚህም ዓይንን ሳያሹ መተባበር በትግራይ ፖለቲካ ባሕል ላይ ክፉ ጥላውን እንዳጠላ እንድንገነዘብ ገፊ ምክንያት ይኾነናል፡፡

## አዲሱ ፍኖት ምን ይኹን?

የትግራይ ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ የኾኑት አቶ ነብዩ ስሑል ሚካኤል ከአንድ ሳምንት በፊት በፌስቡክ በይነ-መረባቸው ያስተላለፉት መልዕክት የትግራይ ፖለቲካ አዲስ የአስተሳሰብ መንገድ ሊቀየስለት እንደሚገባ በእጅጉ የተረዱ መኾናቸውን የሚያሳብቅ ነው፡፡ በእርግጥ እንደአቶ ነብዩ ሁሉ ሌሎች የትግራይ ፖለቲከኞችም ህወሓትን ከትግራይ ሕዝብ ነጥሎ ለመታገል አስቸጋሪ በመሠለቡት ጊዜያት ሳይቀር በአደባባይ ወጥተው ዘመኑን የሚዋጅ የፖለቲካ መስመር ለትግራይ ወጣት እንደሚያስፈልገው ከመናገር አልቦዘኑም፡፡

ይኽ በምናልማት የነገዋ ኢትዮጵያ ሥልጡን ፖለቲካ ውስጥ የሚኖረው ትርጉም ትልቅ ነው፡፡ አዲሱ የትግራይ የፖለቲካ ፍኖት ምን ይኹን የሚል ጥያቄ ሲነሳም በዋናነት ወደታሪክ መዝገብነት እየተቀየረ ያለው ህወሓት ያነበራቸውን ስሁት ዕሳቤዎች ከመመርመርና ከማረም የሚነሳ ስለሚኾን ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ድርጅቱ በዐርባ ስድስት ዓመት ዕድሜው በትግራይ ፖለቲካም ኾነ ማኅበረሰባዊ ጉድኝት ውስጥ የተከላቸውን አላስፈላጊ አረሞች ከመንቀል መጀመር ይገባዋል፡፡

## ሀ) የሀቀኛ ፓርቲዎች ውልጃ (The birth of honest parties)

አረሙን የመንቀያ የመጀመሪያው ተግባር፣ ሀቀኛ የፖለቲካ ድርጅቶችን ማዋለድ ወይም መፍጠር ነው፡፡ በእስካሁን ህወሓት መር የክልሉ ፖለቲካ ከ"ዓረና ትግራይ" እና "ከትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ" ውጪ ሀቀኛ ፖለቲካ ፓርቲዎች አልተወለዱም ማለት ይቻላል፡፡ ህወሓት መቀመጫውን ከአዲስ አበባ ወደ መቀሌ ካሸጋሸገ በኋላ አስገራሚ ሊባል በሚችል መልኩ ግን ሦስት ተጨማሪ ድርጅቶች ተመሥርተዋል፡፡ እነዚህም ፓርቲዎች "ባይቶና"፣ "ሳልሳይ ወያነ" እና "ሳወት" ይሰኛሉ፡፡ ድርጅቶቹ ካለፈው አንድ ዓመት አንስቶ "የጨረቃ" እስከተባለው ምርጫ ድረስ ተሳታፊ በመኾን ሕልማቸውንም ትልማቸውንም ይፋ አድርገዋል፡፡

በአጭሩ "እኛ ከህወሓት የባሰን አክራሪ ዘውጌዎች ነንና ከትግራይ ጋር አብሮ ለመቀጠል ለዘብተኛው ህወሓትን አታስኮርፉ" የሚል ምልክት(Signal) አስተላልፈዋል፡፡ ባይቶና የተባለው ፓርቲ በተደጋጋሚ "ፌዴሬሽኑን ወደኮንፌዴሬሽን ከፍ እናደርገዋለን" ብሎ ሲፎክር ተሰምቷል፡፡ "ሳወት" የተሰኘው ድርጅትም እንዲሁ "ትግራይ ራሷን የቻለች ሀገር ካልሆነች ጥቅሟ አይረጋገጥም" የሚል አቋሙን በይፋ በማስተጋባት የ"ነጻነት" ጥያቄ አንግቦ ወደተግባር መግባቱን አውጇል፡፡ "ሳልሳይ ወያነ" ስሙ ብቻውን ለግብሩ በቂ መልስ ነውና ብዙ መዘርዘር አይገባም፡፡ የትግራይ ሕዝብ ከአልቦ ጀብድ እና ፖለቲካዊ ፋከራ የተሻገረ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙን ሊያስጠብቁ የሚችሉ ሀቀኛ የፖለቲካ ቡድኖችን መፍጠር የሚገባውም በዚህና ተያያዥ ምክንያቶች ነው፡፡

## ለ) ብልሽቱን ማስተካከል

አዲሱን የትግራይ ፖለቲካ ፍኖት ለማበጃጀት በሚደረገው ጥረት ከፍ ሲል በትግራይ ፖለቲካ ብልሽቶች ውስጥ ያነሳናቸውን ችግሮች ማስተካከልም ሌላው አስፈላጊ ተግባር ነው፡፡ ሀ) ፖለቲካዊ እቡይነት (Political Ego trip) ፣ ለ) የፓርቲና ሕዝብ ተመሳስሎሽ እና ሐ) ከእውነት የተፋታ ፕሮፓጋንዳ ብለን የዘረዘርናቸው ብልሽቶች በቶሎ መታረም የሚገባቸው ናቸው፡፡ ህወሓት ኢትዮጵያን ቀፍድዶ ለሦስት ዐሠርታት ለሚጠጋ ጊዜ መግዛቱን ተከትሎ እነኚህ ፖለቲካዊ ብልሽቶች እንደሀገር የምንጋራቸው መኾናቸው ግልጽ ነው፡፡ ለዚህም እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ኃይል የራሱ ድርሻና ኃላፊነት እንዳለበት አሌ አይባልም፡፡ ነገር ግን ህወሓት ጥንስሱም ኾነ ውድቀቱ በትግራይ እንደመኾኑ መጠን በክልሉ ፖለቲካዊ ባሕል ላይ ከሌላው የከፋ ጉዳት ማድረሱ ግልጽ ነው፡፡ ለዚህ ነው እነዚህን ክፉ ውርሶች በማስተካከል በኩል፣ በመጪው የትግራይ ፖለቲካ ውስጥ የክልሉ በሳል ምሁራን፣ ልኂቃንና ፖለቲከኞች ኃላፊነት ግዘፍ ነስቶ መምጣት አለበት የሚባለው፡፡

## ማሳረጊያ

በአጠቃላይ ልክ እንደሰው ልጅ ሕይወት ሁሉ ፖለቲካም ከህወሓት ሞት በኋላ ይቀጥላል፡፡ የትግራይ ሕዝብም ይቀጥላል፡፡ ኢትዮጵያም ትቀጥላለች፡፡ ዘመንን፣ ዐውድንና ነባራዊ እውነታን ከግምት ያስገባ ለዘመኑ የሚመጥን ፖለቲካን ማራመድ የሚያስፈልገውም በነበረበት የሚቆም አንዳችም ነገር ባለመኖሩ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ትግራይ ካረጀና ካፈጀው የህወሓት ዘውግ ፖለቲካ ይልቅ አካታች የኾነ ሥርዓትና ሀገር ለመፍጠር በሚደረገው ትግል ውስጥ መሳተፍን መምረጧ ይበልጥ ይጠቅማታል ተብሎ ይገመታል፡፡ "ትግሉ ከከተማ ወደ ደደቢት ተመልሷል" የሚሉ የአሮጌው ዘመን ቁማርተኞች ያረጡ መኾናቸውን ሕዝቡ በተግባር ማረጋገጥም የሚጠበቅበትም ለዚህ ነው፡፡ ይኽ መኾኑ በኢትዮጵያችን ሠማይ ላይ ያንዣበበው አስፈሪ ደመና ገፍፎ ጸሐይ የመውጫ ዕድሜውን ያፈጥነዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ከህወሓት በኋላ አዲስ ፖለቲካ ፍኖት መከተል ወሳኝ ውሳኔ ኾኖ ይመጣል፡፡

# “ሀገር እና መንግሥት ግራ የሚገባን ሕዝቦች አይደለንም”

ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ



ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሕዳር 21 ቀን 2013 ዓ.ም ከፓርላማ የቀረቡላቸውን ጥያቄዎች ተንተርሰው የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ በዚህም ለውጡን በኹለት እግሩ ለማቆም የነበረውን ፈተና፣ ቅድመ ለውጡ በኢትዮጵያ የመከላከያና የደህንነት ተቋማት ላይ ነበረውን ኢ-ፍትሐዊ ስብጥር፣ ባለፉት ኹለት ዓመት ተኩል ጊዜያት በየክልሉ ስለተፈጠሩት ግጭቶች እንዲሁም በሰሜን ዕዝ ላይ የተፈጸመውን ጥቃት ተከትሎ መንግሥት ስለወሰደው ሕግ የማስከበር እርምጃ በዝርዝር አስረድተዋል፡፡

## የለውጡ ሰሞንና የቤተመንግሥቱ ግብግብ

ጠ/ሚኒስትሩ ለውጡ በመጣበት የመጀመሪያዎቹ ጊዜያት የነበሩ ሁኔታዎችን አስመልክተው ለፓርላማ በሰጡት ማብራሪያ በዓለ ሲመታቸውን ተከትሎ ለተወሰኑ ጊዜያት ቢሮ ከፍተው የሚያስገቧቸውና ቆልፈው የሚያወስወጧቸው ህወሓቶች እንደነበሩ ተናግረዋል፡፡ የቤታቸው ዋናው ቁልፍ እነዚህ ኃይሎች እጅ እንደነበር የገለጹት ዶ/ር ዐቢይ “ማታ አስገብተው የሚቆልፉብኝም እነሱ ነበሩ” ብለዋል፡፡ እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ሳይኾን በእሥር ቤት ውስጥ እንዳለ ግን ሚዲያ ላይ መቅረብ እንደሚችል ሰው ነው ነበርኩ ብለዋል፡፡

በእያንዳንዱ እንቅስቃሴያቸው ሁሉ ደህንነቶች ቁጥጥር ያደርጉባቸው እንደነበርም አልሸሸጉም፡፡ በዚህም ሱማሌ ክልል ለመሄድ ሲነሱ “አልሸባብ ሊገድልህ ስለሚችል መሄድ አትችልም”፣ አምቦ ለመሄድ ሲሞክሩ “አትሂድ ኦነግ ይገድለሃል” እየተባሉ ይከለከሉ እንደነበር አስረድተዋል፡፡ የሚገድላቸው ኦነግ እና አልሸባብ ሳይኾኑ ሊገድላቸው ያሰበው በጉያቸው ያለው ኃይል መኾኑን አውቀው ተጨማሪ ጥበቃ አድርገው አምቦ ኾነ ሌሎች አካባቢዎች ሄደው ማኅበረሰቡን ማወያየታቸውን ተናግረዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይኽን ያሉት ከምክር ቤቱ “ሕግ የማስከበር እርምጃው ዘግይቷል” የሚል ጥያቄ መነሳቱን ተከትሎ እንኳን የሀገር ሰላም ማስጠበቅ ይቅርና የራሳቸውንም ደሕንነት ማስጠበቅ አለመቻላቸውን ባብራሩበት ወቅት ነው፡፡

## በመላው ሀገሪቱ የተፈጠሩ ግጭቶች በአኃዝ

ከለውጡ ማግሥት ጀምሮ በእያንዳንዱ ሳምንት የጦርነት ድግስ ነበር ያሉት ዶ/ር ዐቢይ መንግሥት ሥራ እንዳይሠራ በየቦታው ችግር ይፈጠር እንደነበርም ገልጸዋል፡፡ እስካሁንም በመላው ሀገሪቱ 113 የሚኾኑ ግጭቶች መፈጠራቸውን አስረድተዋል፡፡ ለግጭቶቹ እርሾም የብሔርና የሃይማኖት ሁከት እንዲነሳ የጥፋት ኃይሎቹ ታትረው መሥራታቸውን ተናግረዋል፡፡ በዚህም ባለፈው ኹለት ዓመት ተኩል በኦሮሚያ ውስጥ 37 ግጭቶች፣ በአማራ ክልል 23 ግጭቶች፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ 15 ግጭቶች፣ አዲስ አበባ 14 ግጭቶች፣ በጋምቤላ 7 ግጭቶች በሌሎች አካባቢዎችም እንዲኹ በርካታ ግጭቶች መከሰታቸውን አሳውቀዋል፡፡ በተለይ በኦሮሚያ ክልል የሀጫሉ ሁንዴሳ ግድያን በተመለከተ ከሃጫሉ በተጨማሪ ሌሎች የኦሮሞና የአማራ አመራሮችን በመግደል ግጭቱን የኦሮሞና የአማራ ለማስመሰል ጥረት ተደርጎ እንደነበርም ገልጸዋል፡፡

ጉጂና ጌዲዮ እንደ አንድ ቤተሰብ የሚኖር ሕዝብ መኾኑን የገለጹት ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ እዚያ አካባቢ በርካታ ሰዎች እንዲፈናቀል መደረጉን ተናግረዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በአማራና በቅማንት መካከልም የተፈጠረው ችግር የማይነጣጠሉ ዜጎችን ለማባላት የጥፋት ኃይሉ የነደፈው ሴራ መኾኑን ተናግረዋል፡፡ በሌላ መልኩ አማራ ክልል፣ ከቤኒሻንጉል፣ ከኦሮሚያ፣ ከአፋር መዋሰኑን ገልጸው ከሁሉም ጋር ሲጋጭ ከትግራይ ጋር ተዋስኖ አለመጋጨቱ የሴረኛውን ማንነት አጉልቶ የሚያሳይ ነው ብለዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ሌሎች ክልሎችም ከጎረቤት ክልሎች ጋር እንዲጋጩ መደረጋቸውን የገለጹት ዶ/ር ዐቢይ ትግራይ ክልል ለአማራና ለአፋር ክልል ጎረቤት ቢኾንም እንደሌሎች ክልሎች ግጭት አለመፈጠሩ ግጭቱ ታስቦበት የሚሠራ በመኾኑ ነው ሲሉም አክለዋል፡፡

## ከለውጡ በፊት የመከላከያ ሠራዊት የተገነባበት አኃዛዊ መረጃ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የመከላከያ ሠራዊትን አገነባብ በለውጡ ማግሥት ምን ይመስል እንደነበር በዝርዝር ለፓርላማ የሚከተሉትን አኃዛዊ መረጃዎች አቅርበዋል፡፡ በዚህም “የመከላከያ ሠራዊት የተገነባበት ርዕዮት ከሕገ መንግሥቱ ጋር 100% የሚቃረን የአንድ ፓርቲን ርዕዮት ለማስጠብቅ ያለመ ነበር” ብለዋል፡፡ ለምሳሌ ባለ አራት ኮኮብ ጄነራል 60 በመቶው ከአንድ ቡድን፣ ሌተናንት ጄነራል 50 በሞቶ ከአንደ ቡድን፣ ሜጀር ጄነራል 45 በመቶ ከአንድ ቡድን፣ ብርጋዴር ጄነራል 40 በመቶ ከአንድ ቡድን፣ ኮሌኔል 58 በመቶ ከአንድ ቡድን፣ ሌተናል ኮሎኔል 66 በመቶ ከአንድ ቡድን፣ ሻለቃ 53 በመቶ ከአንድ ቡድን፣ በጥቅሉ ከጄነራል እስከ ሻለቃ ድረስ በአማካይ ሲታይ 55 በመቶው ከአንድ ክልል ብቻ እንደነበር አብራርተዋል፡፡

የመከላከያ ሠራዊትን ስብጥር ለማስጠበቅ በወቅቱ በነበረው ሁኔታ ማሰብ እንዳይቻል ተደርጎ የአንድ ቡድንን የበላይነት ለማረጋገጥ ታልሞ የተሠራ እንጂ ቢያንስ በታችኛው የወታደራዊ እርከኖች ከሌሎች አካባቢዎች የመጡ መኮንኖችን ማፍራት ይቻል እንደነበር አስርድተዋል፡፡ ኢትዮጵያ በነበሯት ሁሉም ዕዞች ይመሩ የነበሩት ዋና እና ምክትል አዛዦች ከአንድ ቡድን ወገን የፈለቁ መኾናቸውን ተናግረዋል፡፡ ከዚህ በተለየም በሰሜን ዕዝ ላይ ዋና እና ምክትል አዛዥ፣ ሎጂስቲክ፣ አስተዳደርን የሚመሩት ሁሉም ከህወሓት ቡድን የመጡ መኾናቸውን አሳውቀዋል፡፡

ከዕዝ በመለስ የመካናይዝድ ክፍለ ጦሮችን በሙሉ 100 በመቶ እና የእግረኛ ክፍለ ጦሮችን 80 በመቶ የሚመሩት በዚሁ በአንድ ቡድን እንደኾነና ከወታደራዊ መለዮ ለባሾች ባሻገር የመከላከያ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት 80 በመቶው ተይዞ የነበረው በህዋሓቶች ስለመኾኑም ገልጸዋል፡፡ ሁሉም ክልል በሚገባው የሕዝብ ቁጥር ልክ መወከል አለበት እንጂ ከሚገባው በላይ እንዲኖረው መደረጉ አሁን ላይ የደረስንበትን ችግር ሊፈጥር ይችላል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የመከላከያ ሠራዊት አዛዦች ከአንድ አከባቢ መኾን ለትግራይ ሕዝብም ኾነ ለመላ የአገሪቱ ሕዝቦች እንዳልጠቀመ ተናግረዋል፡፡

እነዚህን ነባራዊ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት በትንሹም ቢኾን ለመቀየር እና ኢትዮጵያን የሚመስል መከላከያ ሠራዊት ለማዋቀር ጅምር ሥራዎች መደረጋቸውን ገልጸው በተደረገው የመከላከያ ሪፎርም ▶

ከሻለቃ እስከ ጀነራል የነበረውን ወታደራዊ የሥልጣን እርከን በአማካይ ከነበረበት 55 በመቶ ወደ 26 በመቶ ዝቅ እንዲል መደረጉን አስረድተዋል፡፡ ቁጥሩ ከፍ ያለ ቢኾንም የትግራይ ክልል በመከላከያ ሠራዊት አባልነት ረገድ በቂ ድርሻ እንዲኖረው ፅኑ ፍላጎት ያለ በመኾኑ የሌሎችንም ድርሻ ያማከለ እንዲኾን የማድረግ ሥራ እየተሠራ መኾኑንም ተናግረዋል፡፡ አያይዘውም በሁሉም የአገሪቱ ዕዞች የነበረውን የ100 % ስብጥር በአማካይ ወደ 25 በመቶ ዝቅ እንዲል መደረጉንና ከደቡብ ሕዝቦች እስከለውጡ ድረስ የነበረው ወታደራዊ ማዕረግ ከፍተኛው የማዕረግ ጣራ ሜጀር ጀነራል እንደነበር ገልጸዋል፡፡ መካከለኛው የአመራር ስብጥርን ለማስተካከል ግን ሙያዊ ደረጃ ስለሚጠይቅ እና የመከላከያው መዋቅር ሙሉ ለሙሉ እንዳይጎዳ ከፍተኛ ወታደራዊ አመራሩ ላይ ሪፎርሙ እንደተደረገው አለመኾኑንና እንዲዘገይ መደረጉን አብራርተዋል፡፡

አገሪቱ ላይ የነበሩ ከባድ መሣሪያዎች ሁሉ በሰሜን ዕዝ ላይ ስለነበሩ ለማንቀሳቀስ ሲሞከር ሕዝብን በማወናበድ የወንበዴው ቡድን እንቅፋት ሲኾኑባቸው መክረሙን የገለጹት ጠቅላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ "የታችኛውን አመራር አሠልጥኖ ደረጃውን የጠበቀ መለዮ አልብሶ ለማብቃት ኹለት ዓመት በቂ ባለመኾኑ በመከላከያው ላይ ያለውን ክፍተት በሙሉ አቅም ለማሻሻል ጊዜ ጠይቆናል" ብለዋል፡፡

በምሥጢር የተቋቋመ የሪፐብሊካን ጋርድ መሥርተው ኢትዮጵያን የሚታደግ ልዩ ኃይል የለውጡ አካል ኾኖ ሥራውን እንዳከናወነ የጠቀሱት ዶ/ር ዐቢይ ከዚህ በኋላ የመከላከያ አባል እንደሚኾንም አሳውቀዋል፡፡ "የአየር ኃይሉን በሰው ኃይል እና በቴክኖሎጂ በማዘመን እስከ ሰው አልባ በራሪ ተዋጊ ድሮኖችን ጭምር እስከመታጠቅ ደርሰናል" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የህወሓት ቡድን የኢትዮጵያን ወታደራዊ አቅም በማናናቅ ጭምር መከላከያውን በመውጋት የኋላ ኋላ ወደጦርነት እንደገባ ተናግረዋል፡፡

## በሰሜን ዕዝ ላይ የተሰነዘረው ጥቃትና ሕግ የማስከበር ዘመቻው

በሰሜን ዕዝ የመከላከያ ሠራዊት ላይ በተደረገው ጥቃት ሳቢያ በትግራይ የተጀመረውን ሕግ የማስከበር ዘመቻን በተመለከተ ጦርነቱን ቀድሞ የጀመረው የህወሓት ቡድን መኾኑን ገልፀው ሰሜን ዕዝን በሙሉ አውድሜያለሁ ብሎ በማሰቡና ጠንካራ አየር ኃይል የለም በሚል ጦርነቱን በይፋ ህወሓት መጀመሩን ተናግረዋል፡፡ ከሰሜን ዕዝ አልፎም የህወሓት ኃይል ወደ አማራ ክልል ጭምር ጥቃት በመፈፀሙ ጦርነቱን በመጀመሪያ የመከላከል ሥራ በመሥራት ኋላ ላይ ወደ ማጥቃት መገባቱን አስረድተዋል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የሰሜን ዕዝ አባላት የኾኑ የመከላከያ አባሎች ማርከውም፣ ራቁታቸውንም ኾነው ወደ ኤርትራ የገቡ የጦሩ አባላትን በማደራጀት ጦሩ ወደ መልሶ ማጥቃት እንዲችል ማድረጋቸውን ገልጸዋል፡፡ የመከላከያ ኃይሉ አባላት ጥይት ጨርሰው እንኳን ከጠላት ቀምተው መስዋዕትነት ከፍለው እስከ መዋጋት ደርሰው ለድል መብቃታቸውን ተናግረዋል፡፡

በሰሜን ዕዝ ላይ የተከፈተውን ጥቃት መክተው በጁንታው ኃይል ላይ ጥቃት ከፍተው የከፋ ጉዳት እንዳይደርስ አድርገው የህወሓትን ኃይል የደመሰሱ ቆራጥ ልጆች ኢትዮጵያ ባይኖራት ኖሮ አሁናዊ ገፅታችን እንደሌሎች አገራት ይኾን እንደነበር የገለጹት ዶ/ር ዐቢይ የትግራይ ሕዝብ በሕግ ማስከበሩ ሂደት ከሠራዊቱ ጎን በመቆም የተደበቀ መሣሪያ አውጥቶ በመስጠትና ለምን መከላከያን አጠቃችሁ በሚል ከሠራዊቱ ጋር አብሮ ኤርትራ ድረስ የተሰደደ ወገን መኖሩም ጭምር ሊታወቅ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም "ጦርነቱን በኹለት ሳምንት ለማጠናቀቅ ታቅዶ የነበረ ቢኾንም፣ የንጹሃን ዜጎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በሚል በተረጋጋ ሁኔታ ለመፈፀም ተገደናል" ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የአገሪቱ አቅም ሰሜን ዕዝ ላይ እንዲኾን ኾን ተብሎ አስቀድሞ የህወሓት ቡድን መሥራቱን የጠቀሱት



ዶ/ር ዐቢይ ጥቅምት 24 ቀን የአዲስ አበባ ህወሓት ቡድን አባላት የሰሜን ዕዝ መብራት በጣጥሰው፣ ወታደሩ እንዳይገናኝ ኮሚዩኒኬሽን አቋርጠው፣ ብዙዎችን ገድለውና አፍነው፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ተግባር መፈጸማቸውን ገልጸዋል፡፡ በሰሜን ዕዝ ላይ በደረሰው ጥቃት ራቁታቸውን ወደ ኤርትራ የሄዱ ሰዎች በኤርትራውያን የሚለበስ ልብስ ማግኘታቸውንም ተናግረዋል፡፡ የክልሉ መሪዎች እየወጡ ሰሜን ዕዝ ከእኛ ጋር ነው ሲሉ መቆየታቸውን የገለጹት ዶ/ር ዐቢይ "ሰሜን እዝ ከእነሱ ጋር ከኾነ ምንም ንግግር አያስፈልግም ነበር" ብለዋል፡፡ ሽሬ አከባቢ በነበረው ካምፕም የሌሎች ብሔረሰብ አባላትን ወታደሮች አፍነው መውሰዳቸውን ጠቅሰዋል፡፡

ከጥቃቱ በፊት የሰሜን ዕዝ አዛዥ ጄኔራል ድሪባ ከእነሱ ጋር ምሳ ከበላ በኋላ ራሱን በመሳት እስከ ዛሬ ሥራ መሥራት የሚያስችል አቋም ላይ አለመኾኑን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላ የትግራይ ሕዝብ ለመከላከያ ከፍተኛ ድጋፍ ማድረጉን አስረድተዋል፡፡ ባለፉት ኹለት ሦስት ሳምንታት ውስጥ ከሕጋዊ የትግራይ አስተዳደሮች ጋር ድርድር ሲደረግ እንደነበርም ተናግረዋል፡፡ በአንጻሩ ከወንጀለኛ ጋር ግን ድርድር የሚባል ነገር አለመኖሩን አሳውቀዋል፡፡

በሌላ መልኩ የትግራይ ሕዝብ አሁን ካለበት ሁኔታ እንዲወጣ በመደገፍ የተሰደዱትን የመመለስና የማቋቋም ሥራ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራ ጠቁመው በህወሓት ቡድን ላይ የተደረገው ዘመቻ በሰላማዊ ዜጎች ላይ ጉዳት ሳይደርስ በሦስት ሳምንት ውስጥ በቁጥጥር ሥር መዋል መቻሉን ተናግረዋል፡፡ ይኽ የኾነውም የመከላከያ ሠራዊቱ በጣም ዲሲፕሊን ያለው ጀግና ወታደር በመኾኑ እንደኾነ ጠቅሰዋል፡፡ በርካታ ሮኬቶች ቢኖሩም በትግራይ አንድም ሮኬት አልተተኮሰም ያሉት ጠ/ሚኒስትሩ እንዲኽ ሊኾን የቻለውም ኦፕሬሽኑ በኃላፊነት ስሜት ስለተሠራ ነው ብለዋል፡፡ መቀሌን አፈረሱ ብለው ለሚከሱ አካላት "እኛ የራሳችን የኾነን ነገር እንደ ጁንታው አናወድምም" ሲሉ መልሰዋል፡፡


## የሕግ ማስከበር ዘመቻው ዝርዝር ሁኔታ

ከዘመቻው ጋር በተያያዘ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከዚህ ቀደም ብሎ የሰሜን ዕዝ አዛዥ የነበሩትን ጄኔራል ድሪባ ከህወሓት አመራሮች ጋር ምሳ ከበሉ በኋላ ራሳቸውን ስተው እስካሁን ሆስፒታል እንደሚገኙ ገልፀው የህወሓት አባላት በእርሳቸው ምትክ የተሾሙትን አልቀበልም ማለታቸውን እና የሰሜን ዕዝ ምክትል አዛዥን ማፈናቸውን አስታውሰዋል፡፡ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በመከላከያ ሠራዊት ላይ ጥቃት ካደረሱ በኋላ እቅዳቸው ወደ አማራ ክልል መግባት ነበር፤ የመጀመሪያው ሥራ የመከላከል ሥራ ነበር ብለዋል፡፡ በዚህም ጥቃት የተፈፀመባቸው የመከላከያ ሠራዊት አባላት ወደ ኤርትራ እንዲወጡ የማድረግ ሥራ መሠራቱን ጠቅሰው ሦስት ጀኔራሎችን ይዘው ወደ ስፍራው ማቅናታቸውን እና ከጥቃቱ ካመለጡ የሠራዊት አባላቱ ጋር መገናኘታቸውን ገልፀዋል፡፡

ከዚያ በኋላም ጄኔራሎች የጦር ግንባሮቹን እየመሩ በ15 ቀን ውስጥ በርካታ ድል ማስመዝገባቸውንም አንስተው "ኢትዮጵያ ለሕይወታቸው ቅንጣት የማይሳሱ ጀግኖችን ባትፈጥር ኖሮ አሁን ያለንበት ጊዜ ሌላ ይኾን ነበር" ብለዋል፡፡ በዚህ ውስጥ የትግራይ ሕዝብ የነበረው ሚና ከፍተኛ እንደነበር ገልጸው፤ ባንዳ ተብሎ የተመታ ትግራዋይም እንዳለና ገዳዩ የስግብግብ ጁንታ እንጂ የትግራይ ሕዝብ እንዳልኾነም ሕዝቡ በተግባር ማረጋገጡን ተናግረዋል፡፡

መቀሌ ላይ ሕዳር 20 ቀን ከሕዝቡ ጋር ውይይት እንደነበራቸው የገለፁት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ፤ "ሕዝቡ ዘገያችሁ እንኳን መጣችሁ፤ ውሃ፣ መብራትና ኔትዎርኩን ቶሎ አስተካክሉልን፣ ወንበዴው እንዳይደራጅ በፍጥነት መንግሥት ያደራጅልን" ማለታቸውንም ገልፀዋል፡፡ ቀጣይ ሥራ ትግራይን መገንባት እንደኾነና ከግጭቱ ጋር ተያይዞ 30 ሺህ የሚኾኑ ዜጎች መፈናቀላቸውን ተናግረዋል፡፡ የተፈናቀሉ ዜጎችም በሳምንት እድሜ ውስጥ ተመልሰው እንደሚቋቋሙ አውስተዋል፡፡

ወደ ሱዳን ከተሰደዱት ውስጥ ሕፃናትና ሴቶች እንደሌሉበት የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እዚያ የሠፈረው ወጣት ማይካድራ ላይ አርዶ የሄደ ከኾነ በሕግ ሊጠየቅ እንደሚችል ገልጸዋል፡፡ በዚህ ዙሪያ ለዓለም አቀፍ ተቋማትም የኢትዮጵያ በር ክፍት እንደኾነ ጠቅሰው በክልሉ እውቅና ካለው ፓርቲ ውጭ ክልሉ እንዲተዳደር እንደሚደረግና በአጭር ጊዜ ውስጥ የክልሉ ሕዝብ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድር መኾኑን ጠቁመዋል፡፡ በዚህ ሕግ የማስከበር ዘመቻ ሂደትም ትብብር ላደረጉ የጎረቤት ሀገሮችም ምስጋናቸውን ጠ/ሚኒስትሩ አቅርበዋል፡፡



መታሰቢያ መልዓከሕይወት

# የዶ/ር ዐቢይ እና የአፄ የኃይለሥላሴ የባሕሪ ምስስሎሽ

አፄ ኃይለ ሥላሴ በኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ጉልሕ ስፍራ ያላቸው መሪ እንደነበሩ ግልጽ ነው። ነገር ግን አብዛኛው ታሪካቸው የሚነሳው በመልካም ሳይኾን የግል ዝናቸውን ለመገንባትና የሥልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም የደከሙት ነው። አፄ ኃይለ ሥላሴ መጀመሪያ አልጋ ወራሽ ኾነው ኢትዮጵያን ሲያስተዳድሩ ገና 28 ዓመታቸው ነበር። በወቅቱ የነበሩት ያገር መሪ ንግሥት ዘውዲቱ ለሃይማኖት ልዩ ቦታ ይሰጡ የነበረ በመኾኑ አፄ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ ሁነው አብዛኛውን የንጉሥ ሥራ ይሠሩ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ።

በዓለማችን ያሉ መጥፎ የተባሉ መሪዎች እንደሚታወቁት መጥፎ ሥራ ብቻ ሠሩ ማለት አይቻልም የሠሯቸው መጥፎ ሥዎች ከጥሩ ሥራዎቻቸው ጋር ሲነፃጸር መጥፎው ሥራ እየበለጠ ለውግዘት ዳረጋቸው እንጂ ጥሩ ሥራ አልሠሩም ማለት አይቻልም። አፄ ኃይለ ሥላሴም በተለይ በነበራቸው የዲፕሎማሲ ክሕሎት በርካታ ሥራዎችን እንደሠሩ መካድ አይቻልም። ሥልጣን ላይ የነበሩበት ዘመን በርካታ አገሮች ከድሕነት ለመውጣት መሠረት የጣሉበት ዘመን የነበረ ከመኾኑ በተጨማሪ ነዳጅ እጅግ ርካሽ የነበረበት ጊዜ በመኾኑ ንጉሠ ነገሥቱ ይህን ወቅት በዋዛ ፈዛዛ ማሳለፋቸው አገራችንን በእጅጉ ጎድተዋታል። በወቅቱ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሚያሳስባቸው ችግሮችና ንጉሡን የሚያሳስባቸው ችግሮች እጅግ የተለያዩ በመኾናቸው አገራችን ማግኘት የሚገባትን አመራር ባለማግኘቷ ወርቃማ ጊዜ በከንቱ መክኗል።

አፄ ኃይለ ሥላሴ ምሁራንን ተገቢ ቦታ በመሥጠት አገራችን ያላትን የምሁራን ሀብት እንዳትጠቀም የሚያደርጉበት ባሕርያቸው ከዶ/ር ዐቢይ ጋር ተመሳሳይ ያደርጋቸዋል። ንጉሡ በዋናነት የሚሾሙት አድር ባዮችን በመኾን በጊዜው የነበሩ ምሁራን እንኳን እውቀታቸውን ተጠቅመው ለውጥ ሊያመጡ ይቅርና ሐሳባቸውን እንኳን ለመግለጽ የሚችሉበት መድረክ አልነበራቸውም። አፄ ኃይለ ሥላሴንና ዶ/ር ዐቢይን በዋናነት የሚያመሳስላቸው ባሕርያቸው ሁለቱም ለግል ዝናቸው ተግተው መሥራታቸው ነው። እንዲህ ዓይነት ሰዎች ካላቸው የበላይ የመኾን ሱስ የተነሳ ይህንን ስሜታቸው ለማርካት የሰው ሕይወት እስከ ማጥፋት ወንጀል ሊሠሩ ይችላሉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ በእኔ ዕድሜ የምናቃቸው መሪዎች ልክ እንደ አትሌቲክስ የተለያየ ዘዴን ተጠቅመው የፊተኛውን መሥመር የያዙ ሰዎች ናቸው የሐገር መሪ የሚሆኾኑት እንጂ በችሎታቸው ተመርጠው ምንም ወንጀል ሳይፈጽሙ መሪ ለመኾን የቻሉ የሉም ማለት እችላለሁ። አፄ ኃይለ ሥላሴ የግላቸውን ዝና ያጎድፈዋል ብለው በማመናቸው ከሥልጣን ሊወርዱ ጥቂት ጊዜ ሲቀራቸው በትግራይና በወሎ የተከሰተውን ድርቅ ለማፈን በመሞከራቸው የብዙ ዜጎች ሕይወት አልፏል። የረሐቡ ዜና በጊዜ ግልጽ ቢደረግ ኖሮ በአገር ውስጥ እርዳታ ብቻ የብዙ ሰው ሕይወት ማትረፍ በተቻለ ነበር። ይህንን ዓይነት የአፄ ኃይለ ሥላሴ ለግል ዝና ሲባል ሕዝባዊ ሰቆቃን የመደበቅ ተግባር በብዙ መልኩ በዶ/ር ዐቢይ ላይም ይታያል። ለምሳሌ ወለጋ ውስጥ የታገቱትን ሴት ተማሪዎች ጉዳይ እየተከታተሉ ለሕዝቡ ማሳወቅ ሲገባቸው በየስብሰባው ላይ ሰው ካልጠየቃቸው በቀር በራሳቸው ተነሳሽነት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው መረጃ ሲያቀብሉ ታይተው አይታወቁም።

በአንድ በኩል በየክልሉ ያሉ ባለሥልጣናት የክልል ሕዝቦችን እየዘረፉ አዲስ አበባ የሚይከራዩ ሕንፃዎች ይገነባሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ዶ/ር ዐቢይ እየለመኑም፣ እርዳታ ከአገር ውስጥና ከውጭ እየጠየቁ ብልጭልጭ ነገሮችን ይገነባሉ። እነዚህ ፕሮጀክቶች እንደተባለው የቱሪስት መሥህብ ሊኾኑ ይችላሉ። ነገር ግን በአንድ አገር ፖለቲካዊ ሰላም ከሌለ፣ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት በአግባቡ ከሌለ፣ ሕገ መንግሥታዊ የፌደራል አወቃቀሩ መልክ ካልያዘና በአጠቃላይ አስተማማኝ ሰላም ከሌለ የቱሪስት መስሕብ የሚባል ነገር አይኖርም። ዶ/ር ዐቢይ በቅድሚያ መሥራት የሚገባቸውን ተግባራት አከናውነው ቢኾን ኖሮ ዛሬ ቅንጦት ለኾኑ ጉዳዮች ትኩረት ለመሥጠት የሚኾን ጊዜ ይኖራቸው ነበር።

ሌላው ዶ/ር ዐቢይ ላይ የሚታየው ግልጽ የኾነ ባሕርይ ውጭ አገር ሂደው ያዩትን ነገር አገር ውስጥ ለመድገም የሚሚክሩት ነገር ሲኾን ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ጋር ያመሳስላቸዋል። ውጭ አገር የተገነቡ የቅንጦት ፕሮጀክቶች የተገነቡት እነዚህ አገሮች የሕዝባቸውን መሠረታዊ ፍላጎት ካረኩ በኋላና ቅድሚያ ተሰጥቶአቸው ሊሠሩ የሚገባቸውን ከሠሩ በኋላ ነው። ለምሳሌ አጨቃጫቂ ያልኾነ ሕገ መንግሥት አዘጋጅተው ጨርሰው ሌሎችንም ወሳኝ ተግባራትን ከፈፀሙ በኋላ ነው።

አፄ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያን ባስተዳደሩበት ዘመን አፄ ኃይለ ሥላሴን የሚመሥሉ በርካታ መሪዎች በዓለም ላይ ነበሩ። በአውሮፓም ጭምር በመኾኑም አፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመኑን ይመሥሉ ነበር ማለት ይቻላል። ዶ/ር ዐቢይ ግን በዚህ በሠልጣነና በኮምፒውተር፣ በኢንተርኔት ዘመን እንደ ኃይለ ሥላሴ መምሰላቸው በእጅጉ አሳፋሪ ነው። የሠው ልጆች ካሉን አንዱና ዋነኛው ባሕሪ አንዱ ዘመኑን መምሰል ነው። እጅግ አክራሪ የኾኑት አረቦች እንኳን አሁን ገብቶአቸው ዘመኑን ለመምሠል (ወግ አጥባዊ ከኾኑ ቡድኖች ጋር እየተላተሙ) ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉበት ዘመን ላይ ደርሰዋል። ዘመኑን መምሰል ደግሞ በአለባበስ በአኗኗር ብቻ ሳይኾን በዋናነት በአስተሳሰብ ጭምር ነው። ዛሬ የዓለም ሕዝብ ለረቀቁ ሳይንሶች ብቻ ቦታ በሚሠጥበት ዘመን እኛ ገና ያለንን መሬት እንኳን እንዴት ማስተዳደር እንዳለብን ግራ ገብቶችን በመደናበር ላይ እንገኛለን።


ቻይናውያን ከጥቂት ዐሥርት ዓመታት በፊት እጅግ በድሕነት ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ሁነው አሁን በሳይንስ በመምጠቃቸው የተነሳ የራሳቸው GPS system መገንባት ችለው ባለፈው ሐምሌ ወር አስመርቀዋል። የዚህ ቴክኖሎጂ ባለቤት የኾነ አገሮች አሜሪካ ራሺያና የአውሮፓ ሕብረት ናቸው። በተጨማሪ (የ5G) አምስተኛው ትውልድ የኔትወርክ ባለቤት በመኾናቸው ይኽንን ሲስተም የሚጠቀሙ ካምፓኒዎች እጅግ የተቀላጠፈና ፈጣን ሥራ መሥራት የሚያስችላቸው በመኾኑ ትርፋማነታቸው ጊዜ ቆጣቢነታቸው እና ሌሎችም በርካታ ጥቅሞችን ያስገኙላቸዋል።

በመጨረሻም ፉገራ አጉል ሙገሳ ዝና የሚወዱ መሪ ይህን የሚያደርጉለት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ማሰባሰብ ይችላል። መጨረሻው ግን አያምርም ብልህ መሪ በዋናነት ሊያማክሯቸው የሚገቡ ሰዎች የመሪውን ደካማ ጎን በድፍረት የመግልጽ ብቃት ያላቸውን ዜጎችን ነው። አንድን መሪ እየፎገሩ የሚጠጉ ሰዎች በእርግጠኝነት የሥራ ዕድልን የመሳሰሉ በርካታ ጥቅማ ጥቅሞችን ማግኘት እንደሚችሉ ሥለሚያውቁ ከአምባገነን ሥር ተፈልገው አይጠፉም። እነዚህ ሰዎች ግን እንኳን ለአገር ለራሳቸውም አይኾኑም።



“በሀገራችን ውስጥ በኪጥበብ ባለሞያዎች የሚደረጉ ማንኛውም አይነት ለሀገር የሚጠቅሙ ፕሮግራሞች ሲካሄዱ እንደማንኛውም ዜጋ በዜና ነው የማየው እንጂ ተሳታፊ እንድሆን ጥሪ ተደርጎልኝ አያውቅም። በትላንትናው "ጥበብ ለሀገር ክብር" የተባለ ፕሮግራም ላይ ግን በብሔራዊ ቴአትር እንድገኝ የቀድሞ መምህሬ ረ/ፕ ነብዩ ባዬ ጥሪ አቀረበልኝ። "ውይ ዛሬ እንዴት ትዝ አልኩህ ተቀይሜህ ነበረኮ" ብዬ ጥሪውን በማክበር በቦታው ተገኘሁ። ብዙ ጋዜጠኞችና ጥቂት በጣት የሚቆጠሩ አንጋፋ ከያኒያን በቦታው ተገኝተዋል። እንደደረስኩ የቲቪ ጋዜጠኞቹ ጥያቄ ሲያቀርቡልኝ "እኔ ስለ ፕሮግራሙ ምንም የማውቀው ነገር የለም። ጠይቄ ከተረዳሁ በኃላ ታናግሩኛላችሁ" ብዬ መለስኩ። ጋሽ ደቤ (የጥበብ ሰው ደበበ እሸቱ) አካሉ በእድሜ የደከመ ቢመስልም በከፍተኛ የሞራል ጥንካሬ የፕሮግራሙን ሀሳብ ከማመንጨት እስከማስፈጸም ሲጣጣር ሳየው አሳዘነኝ። ዘመኑን፣ እድሜውን፣ እውቀቱን ሁሉ እስከመጨረሻዋ እስትንፋሱ ለሀገሩ ኢትዮጵያ ለመስጠት የቆረጠ ሰው በመሆኑ ኮራሁበት።”

አስቴር በዳኔ፣ አርቲስት



“የአገሪቱ ችግር የሚፈታው የጎሳ ህገ መንግስቱ ሲቀየርና ያሉት የጎሳ የክልል አስተዳደሮች እንደገና ሲዋቀሩ ነው። ይህ ከተደረገ የወልቃይትም ጉዳይ በዚሁ ተገቢውን ውሳኔ ያገኛል። ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ከ40 አመት በሁዋላ ህዝቡ በትግሉ የያዘውን አካባቢ በወሰን አስተዳደርና ማንነት ኮሚሽን የሚባል ምን እንደሚሰራ የማይታወቅ ድርጅት ነገ ብቅ ብሎ በጥናቴ መሰረት አካባቢው ወደ ትግራይ መካለል አለበት ቢል ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። የወልቃይትም ሆነ የአገሪቱ ችግር የሚፈታው ህገ መንግስቱን በመቀየር እንጅ ይህን. ጦሰኛ ህገ መንግስት መሰረት አድርጎ በተዋቀረ ኮሚሽን አይደለም። ወልቃይት በኮሚሽን ጥናት አትወሰድም። ጊዜና ገንዘብ አታባክኑ። ጠ/ሚኒስትሩ እውነት የዚህችን አገር አንድነት የሚፈልጉ ከሆነ የኮሚሽን ጋጋታ የሚይሳስባቸው ከሆነ ይህን ህገ መንግስት መለወጡ ላይ ቢበረቱ ይሻላል።”

ዶ/ር ሰማኸኝ ጋሹ፣ የሕግ ባለሙያ



“ብረትን መቀጥቀጥ ቀጥቅጦም ሰይፍ መስራት እንደ ጋለ ነው። ሲቀዘቅዝ መልሶ ጥቅም አልባ ብረት ነው። እናም "የህወሓት ጁንታ" የሚለውን ነገር ወደ ጎን አድርገን ህወሓት እንደ ፓርቲ ነው ልንዘምትበት የሚገባን። ማደባበስ ይቅር! ህወሓት ሞላጫ ሌባ ገዳይ ሀገር ሻጭ ወንጀለኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የትውልዱን አስተሳሰብ በርዞ ሀገር አልባ አድርጎታል! ስለዚህ መንግስትም ይሁን ዜጎች የልጆቻችንን ኢትዮጵያ ለማዳን በህወሀት ላይ የተጀመረውን ዘመቻ ማስቀጠል ይኖርብናል! ቀጠሮ አያስፈልገውም! አንተም ጸጉርህን እያከክ በጥርጣሬ ዳር ቆመህ ከምታይ ትግሉን ራስህ ጀምረው! "ህገ መንግስቱ እስኪሻሻል በዘሬ ልሰፈር፣ ሲሻሻል ጥሩኝ" የሚለውን ውሀ የማያነሳ አስተሳሰብ እያራመድክ ያንኑ የወያኔን የጎሳ ጉዞ ከምታስቀጥል ቁም! አስብ! ፊትህን አዙር! ጎጠኝነት እና መከፋፈልን ተዋጋውና የተባበረች ኢትዮጵያ የዜጎች ሁሉ ሀገር ለመፍጠር ወስን - ብረቱ እንዳይቀዘቅዝ!!”

የትነበርክ ታደለ፣ ጋዜጠኛ



“የፈንቅል መሪ ነው የተባለው ሰው ስለ ፈንቅል ምንነት ሲያብራራ “ፈንቅል” የሕወሓት ታጋይ የነበረው የሓየሎም አርአያ መጠሪያ እንደነበር ሲናገሩ በሰማሁት ላይ አስተያይት ልስጥና ልሰናበት። ፈንቅል የሚለው ስም የጀግናው ጸረ ፋሽስት አርበኛና የቀዳማይ ወያኔን የሸፍትነት እንቅስቃሴ የደመሰሱት የደጃዝማች ገብረ ሕይዎት መሸሻ የፈረስ ስም እንጂ የቀዳማይ ወያኔ የመንፈስ ልጆች ነን ብለው ጫካ ከገቡት ዋነኞች መካከል ቀዳሚ ለሆነው ለሕወሓቱ ሓየሎም አርኣያ የወጣ ስም አይደለም። ሌላው ቀርቶ ሓየሎም አርአያ የፈንቅል ስም ታሪካዊ ወራሽ እንኳን ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም በፈረስ ስማቸው ፈንቅል በመባል የሚታወቁት የአድዋው አርበኛ ደጃዝማች ገብረ ሕይዎት መሸሻ የቀዳማይ ወያኔን እንቅስቃሴ ከደመሰሱት መካከል ሲሆኑ ሓየሎም አርአያ ደግሞ ጫካ የገባው ደጃዝማች ገብረ ሕይዎት መሸሻ የደመሰሱትን የቀዳማይ ወያኔን እንቅስቃሴ ወራሾት ነን ብለው "ካልአይ ወያኔ" ከሆኑት "ወንበዴዎች" መካከል አንዱ ብቻ ሳይሆን ትግራይን ሊያስገነጥልና ኤርትራን ለማስገንጠል የታገለ በመሆኑ ነው።”

አቻምየለህ ታምሩ፣ አክቲቪስት



“አብን አማራዊ ነው። አብን እልህ አስጨራሹን የአማራ ህዝብ የትግል ጉዞ በመንፈስና በተግባር አብሮ ሲጓዝ ቆይቷል። አብን ፍፁም አማራዊ መሆኑ ለበርካቶች ምቾት እንደማይሰጥ ይታወቃል። ከአማራ ህዝብ ቀንደኛ ጠላት–ትህነግና ሌሎች ፅንፈኛ ሀይሎች አንስቶ በአማራ መካከል የመሸጉ የጠላት አበልጆች አብንን ቢጠሉት የሚገርም አይሆንም። ከአብን ምስረታ ቀን ጀምሮ እስካሁን ድረስ አሉባልተኞችና ሴረኞች ካባ እየቀያየሩ ሲዘልፉንና ስማችንን ሲያጠፉ ቆይተዋል። ነገር ግን አማራነት በራሱ ለጅምላ ጭፍጨፋ የሚዳርግና ጅምላ መቃብር ውስጥ የሚያስገባ የፍረጃ ሰለባ የተደረገ ማንነት ሆኖ መቆየቱን ስለምናውቅ ለአራጆቻችን ደቀመዛሙርት የምንገብር አይደለንም። የአማራ ህዝብ በትህነግ ላይ ያለውን ጥላቻና አቋም የተገነዘቡ ርዝራዦቹ ለህዝብ የሚታገሉ ልጆችንና አታጋይ ድርጅቶቹን ከትህነግ ጋር የሚገናኝና የሚሰራ በማስመሰል የስም ማጥፋት ዘመቻ ከፍተው ሰንብተዋል። ትህነግ ራሱ "አብን ከእኔ(ከትህነግ) ጋር ይገናኛል ወይም ይሰራል የሚል ፕሮፖጋንዳ ስሩልኝ" የሚል መልእክት ከመታያ ጋር በፖስታ እንደሚልክላቸው እንገምታለን።”

የሱፍ ኢብራሂም፣ ፖለቲከኛ



“ለትግራይ ተወላጆች! በጀግናው መከላከያ ሰራዊታችን መስዋእትነት ያገኘነውን የለውጥ ና የዴሞክራሲ በር በተረጋጋና በመልካምነ በማየት ልንጠቀምበት ይገባል። እመነኝ የህወሓት ተረት ተረት ላይመለስ ተቀብሯል። የጎጥ አገዛዝ በትግራይ ሆነ በመላው ሀገራችን ኢትዮጵያ ቦታ የለውም። መንግስት ለውጥ እፈልጋለሁ ለሚል ወጣት በሩን ክፍት አድርጓል ሁላችንም ከመንግስት ጋር በመሆን ለውጡን በጋራ በምስራት ለህዝባችን እናገልግል። ወንጀለኞችን በጋራ ተደራጅተን ያለምንም ይሉኝታና ፍርሃት ወደ ህግ እናቅርባቸው። ወንጀለኛ መደበቅም ይሁን መተባበር ራሱን የቻለ ወንጀልና የሀገር ክህደት ነው። ስለዚህ ወንጀለኛን ፊት ለፊት መጋፈጥ ካስፈራህ በቀጥታ በውስጥ መስመር እኔን መጠቆም ይቻላል። በ24 ሰአት ውስጥ እመነኝ አንጠልጥየ በህግ እንዲያዝ አደርጋለሁ። መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከጎናችን በመሆን ይተባበረናል። የትግራይ ህዝብ በኢትዮጵያዊነታችን በፍጹም አንደራደርም!!!”

መለስ ብሥራት፣ አክቲቪስት



“ገና ወደ መንበረ ዳግማዊ ምኒሊክ ሲመጡ ነበር ሳልሳዊ ምኒሊክ የመሆን እድል እንዳለዎ ምልክቶችን ያየነው። በኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ላይ ዛሬ ያስመዘገቡት ታላቅ ድል እንዲገኝ 1ኛ ለወያኔ ፋታ ሳይሰጡ እርምጃዎን እጅግ በአስገራሚ ፍጥነት ማከናወንዎ፣ 2ኛ ብቃት ያላቸውን ከፍተኛ ጀነራሎች ከጡረታ መልሰው በፍጥነት ወደ ሰራዊቱ መቀላቀልዎ ተገቢውንም ስልጣንም መስጠትዎ፣ 3ኛ ወያኔን መግቢያ መውጫ እንድታጣ ከፕሬዘዳንት ኢሳያስና ከሱዳን መንግስት ጋር የመሰረቱት ፖለቲካዊና ወታደራዊ ዲፕሎማሲ፣ 4ኛ ከየዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ አንዴ ተደራደሩ፣አንዴ ተኩስ አቁሙ፣ አንዴ የእርዳታ ድርጅቶች ይግቡ ወዘተ በሚል የደረሰብዎትን ዲፕሎማሲያዊ ውርጅብኝ በተገቢው ኢትዮጵያዊ ኩራት "አፍንጫችሁን ላሱ" በማለት የሰጡት አኩሪ ምላሽ። የዛሬው ድል እንዲገኝ አስችለዋል! ስለ አስገኙት ድል እንኳን ደስ አለዎት! የዛሬው ድል በእርስዎ አመራር ላይ ያለን ተስፋ፣ ለእርስዎ ያለንም ሂሳዊ ድጋፍ ዳግም እንዲያንሰራራ ምክንያት ሆኗል። ድሉን በዘላቂነት እንድናጣጥምም ወደሚቀጥለው ኢትዮጵያዊ ፕሮጀክት በዚሁ ፍጥነት ይሻገራሉ ብለን እንጠብቃለን! እግዚአብሔር እርስዎንና መላ ቤተሰብዎን ይባርክ!!!”

ታምራት ነገራ፣ ጋዜጠኛ



# "ሥራችን ሴቶችን ማብቃት ነው"

**ወ/ሮ ሮማን ደቅሲዎስ**

ወ/ሮ ሮማን ደቅሲዎስ ይባላሉ፡፡ የኦሮሚያ ክልል ነጋዴ ሴቶች ማኅበር ፕሬዝዳንት ናቸው፡፡ ስለማኅበሩ አመሠራረት፣ ስላለፉባቸው ሂደቶች፣ ስላስመዘገባቸው ውጤቶችና ከሌሎች ማኅበራት ጋር ስላለው የሥራ ግንኙነት የሚከተለውን ቆይታ አድርገናል፡፡

**ድርጅቶንና የእርሶ የሥራ ኃላፊነት በመግለጽ ቢጀምሩልን?**

ወ/ሮ ሮማን፡- የድርጅቴ ስም ሮማን የሽመና ውጤት የሚል ነው፡፡ በተጨማሪነት ማርም አመርታለሁ፡፡ በኃላፊነት ደረጃ ደግሞ የኦሮሚያ ክልል ነጋዴ ሴቶች ማኅበር ፕሬዝዳንት ነኝ፡፡

**ድርጅታችሁ የተመሠረተው መቼነው? ምን ያህል አባላትስ አሉት?**

ወ/ሮ ሮማን፡- ድርጅታችን የተመሠረተው በ2003 ዓ.ም ነው፡፡ በሥራችን ያሉት አባላት ሳይኾኑ ማኅበራት ናቸው፡፡ ብዛታቸውም 35 አካባቢ ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥም እንቅስቃሴ የሚያደርጉና የማያደርጉ አሉ፡፡

**የተቋማችሁ ዓላማ ምንድነው?**

ወ/ሮ ሮማን፡- ዓላማችን ነጋዴ ሴቶች ራሳቸውን ችለው እንዲሠሩና የሥራ ሂደታቸውን እንዲያስፋፉ ማድረግና ማበረታታት ነው፡፡ በተጨማሪም በማኅበር በመቋቋማቸው የሚያገኙትን ጥቅም አውቀው ሥራቸውን እንዲሠሩ ማጠናከርና ማብቃት ነው፡፡

**ከኢንሼቲቭ አፍሪካ ጋር ያላችሁ የሥራ ግንኙነት ምንድነው ቢያብራሩልኝ?**

ወ/ሮ ሮማን፡- እኛ ከኢንሼቲቭ አፍሪካ ቀደም ሲልም በነበሩት በኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበር አማካኝነት ያገኘነው እድል አለ፡፡ ከ2010 ጀምሮ ከኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበር አቅማችንን የምናጎለብትበትን መጋዘን ሙሉ እቃ እንዲገዛልን አድርገናል፡፡ አሁንም ተወዳድረን የ2010 ዓይነቱን ዕድል አግኝተናል፡፡ በዚህም አቅማችንን ለማጎልበት ባስተላለፍነው መሠረት በቀጣይ አስፈላጊውን ነገር እናገኛለን ብዬ አምናለሁ፡፡

**በመጀመሪያ ዙር ያገኛችሁትን ስኬታማ በኾነ መልኩ በሥራ ላይ አውላችኹታል? የነበረው ሂደት ምን እንደሚመስል ቢያብራሩልን?**

ወ/ሮ ሮማን፡- የመጀመሪያ 2010 ላይ ያገኘነው በጣም ጥሩና ውጤታማ ነበር፡፡ ለአባሎቻችንና ለማኅበራቱ በሙሉ ራሳቸው የአቅማቸውን እየወሰዱ የሚያጎለብቱበትን ድንኳን፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ሞንታርቦ፣ ቴብ በድምሩ ስድስት ነገሮችን አግኝተናል፡፡ ያገኘነውም በጨረታና በሕጋዊ መንገድ ነው፡፡ አሁን ማኅበሩ እየተጠቀመበት ነው፡፡

**ለማኅበር አባሎቻችሁ ንቃተ ህሊና የሚጠቅም የምትሰጡት የምክር አገልግሎት ምንድነው?**

ወ/ሮ ሮማን፡- ማኅበራት ያሉት በየአገሩ ነው፡፡ ያንን ማኅበር እንየዞርን አንዳንድ ለእነሱ አስፈላጊ የኾኑ ነገሮችን ለማድረስና ለማሳወቅ ወይም ለመሞከር ትራንስፖርት የለንም፣ የፋይናንስ ችግርም አለብን፡፡ ሌላው ቀርቶ የቦርዱ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንኳን ሄደን በየቦታው ለመሥራት ችግሮች አሉብን፡፡ ስለዚህ ይህን የተባለውን ለማድረግ አቅማችን እየጎለበተ ካልሄደ የምንችለው ተግባር አይደለም፡፡ ያው እቅዳችን እንዳሰብነው ሊሄድልን አልቻለም፡፡

**በቅርቡ የኢትዮጵያ ነጋዴ ሴቶች ማኅበር ያዘጋጀው ፕሮግራም ላይ ሽልማቶች ነበሩና በዚያ ፕሮግራም ተገኝታችሁ ነበር? ከዚያ ሽልማትስ ተቋዳሽ ነበራችሁ?**

ወ/ሮ ሮማን፡- አዎ እዚያም በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውስጥ አለሁኝ፡፡ ተጠርቼም የጤና ጉዳይ ስለነበረብኝ አልሄድኩም፡፡ ነገር ግን ሰው ወክዬ ነበር፡፡

**በዕለቱ የነበረውን ሁኔታ እንዴት አዩት? ትልልቅ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችም በፕሮግራሙ ላይ ተገኝተዋልምና የነበረውን ሁኔታ ሲያዩ ምን ዓይነት መበረታታት ፈጠረሎት?**

ወ/ሮ ሮማን፡- አዎ የነበረውን ሁኔታ በተወካዬ አማካኝነት ሰምቻለሁ፡፡ ፕሮግራሙ በጣም ደስ የሚል ነበር፡፡ ወ/ሮ ግደይንም ደውዬ ጠይቂያታለሁ፡፡ የማበረታቻ ሰርተፍኬቶችና ዋንጫም ተሰጥቶ እንደነበር ነግራኛለች፡፡ ያ በመደረጉ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ የጤና ጉዳይ ►

ኾኖ እንጂ በቦታው ብገኝ በጣም ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ወደፊት ደግሞ ማኅበሩ በጥሩ ሁኔታ እንዲራመድ የሚመለከተው ክፍል ሁሉ በቦታው ላይ ተሰብስቦ ማበረታታት ይገባል፡፡ እንደዚህ ዓይነት የማበረታቻ ሀሳቦች ደግሞ ለማኅበሩ ሲሰጡ በበለጠ የሚነሳሳ ይኾናል፡፡

*በኦሮሚያ ነጋዴ ሴቶች ማኅበራት ወደ ሰላሳ አምስት እንደሚኾኑ ነግረውኛል፡፡ እንዴው በእያንዳንዱና በጠቅላላው ምንያህል እንዳለ መገመት ይቻላል?*

ወ/ሮ ሮማን፡- አዎ እንግዲህ ቅድም ስናገር እንደነበረው ማኅበሩ በበጎ ፈቃደኝነት የሚሠራ ነው፡፡ በጣም ሕዝባዊ ፍላጎት ኖሮት ጥሩ ስለየሚሠራ ማኅበር ይኖራል፡፡ ጥሩ ተነሳሽነት ኖሮት ጥሩ ሥራ እንዲሠራ ተደርጎ የሚሠራ ይኖራል፡፡ እንዲህ ዓይነት ነገር ደግሞ በሁሉም ላይታይ ይችላል፡፡ በጥቅሉ ይሄ ነው ያነው ብየ ባላብራራም ኅበዝ የኾኑ ማኅበራት በውስጣችን እንዳሉ መናገር እችላለሁ፡፡ እኛ ከቦታው ርቀት ለምሳሌ ከዚህ ጅማ አጋሮ ላይ ነው ያሉት፡፡ እዚያም በቦታው እንዴ ካቋቋምንና ካደራጀን በኋላ ተመልሶ ለመነጋገርና አንዳንድ ድጋፍ ለመስጠትም ችግሮች ይገጥሙናል፡፡ የትራንስፖርትና የፋይናንስ ችግሮች ስላሉብን እነዚህ የቋቋምናቸው ማኅበራት ቦታ ድረስ ሄደን ለመሥራት እንቸገራለን፡፡

*ይህን ችግር ለመፍታት ምን ያሰባችሁት ነገር አለ? የቀረጻችሁት ፕሮጀክትስ አለ?*

ወ/ሮ ሮማን፡- አዎ በየቦታው በሴቶች ዙሪያ የሚሠሩት የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ለማኅበሩ እገዛ እንዲያደርግ ለኦሮሚያው ነጋዴ ሴቶች ማኅበራት ባዛር የመሳሰሉ ነገሮችን አዘጋጅተን ለመርዳት እቅድ አለን፡፡ በተጨማሪም ሥልጠና ለመስጠትና በቂ ግንዛቤ እንዲኖቸው ለማድረግ ቢሮ ለሌላቸው የመንግሥት ተቋማትን ለማማከር ቢሮ የሚያገኙበትን መንገድ ለማመቻቸት እየጣርን ነው፡፡ ለምሳሌ የቢሮ ችግሮችን በተመለከተ ከተለያዩ የመንግሥት አካላት ጋር በመነጋገር በተወሰነ መልኩ ውጤታማ የኾንበት ሁኔታ አለ፡፡ እንደ ቡራዩ፣ ጅማ፣ ገላን ወዘተ ያሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ስለዚህ እኛ በታቻለን መጠን የአቅም ጉዳይ ነው እንጂ በእቅዳችን መሠረት ለመራመድ እየሞከርን ነው፡፡

*የኦሮሚያ ክልል መንግሥት ሴቶችን ለማበረታታትና እናንተን ለማገዝ ያደረገው ነገር አለ? እናንተስ ለክልሉ መንግሥት ያቀረባችሁት ጥያቄ ይኖራል?*

ወ/ሮ ሮማን፡- የኦሮሚያ ንግድና ልማት ቢሮ፣ ፕሬዝዳንቱ ቢሮ ድረስ ደብዳቤዎችን እየፃፍን ባዛሮች በየቦታው እንዲያዘጋጅና ምርታቸውን ወደገበያ አውጥተው የገበያ ትስስር እንደፈጠርላቸው ስንል ብዙ ጊዜ ትግል እናደርግ ነበር፡፡ በእርግጥ አንድ አምስት ቦታ ከፕሬዘዳንት ቢሮ ተፅፎልን ነበር፡፡ እነርሱንም ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ አስገብተናል፡፡ በአጋጣሚ አሁን ያለው የወቅቱ ጉዳይ ማለትም ኮሮና እንደልብ አላንቀሳቅስ ብሎን ነበር፡፡ ቀደም ሲል ግን በጣም እኛን እንዳንሠራ የሚጫኑን ድርጅቶ ነበሩ፡፡ ኾኖም ግን እኛ ከትግሉ ወደ ኋላ አላልንም፤ በተቻለን መጠን ሴቶች የሚበረታቱበትን መንገድ እየሞከርን ነው፡፡ ከእቅዳችን አንዱም ይሄ ነው፡፡ እቃም ልንገዛ የቻልነው እየሠሩ ምርታቸውን ገበያ ላይ የሚውሉበትንና የሚያሳዩበትን እንዲኹም ሴቶች የሚበረታቱበትን አሠራር ለማምጣት



አቅደን የነበረውም ለዚህ ነው፡፡ በተለይ ባዛር በተመጣጠነ ዋጋ ነው ገበያ ላይ የሚያወጣው፡፡ ነገር ግን ይሄንም ለማድረግ ጫናዎች ነበሩብን፡፡ ያንንም መንግሥት ያውቃል፡፡ ወደፊት ሀገር ሰላም ከኾነ ወደኋላ የምንልበት ነገር አይኖርም፡፡

*ኮቪድ መፈጠሩን ተከትሎ እናንተ ግንዛቤ በማስጨበጥና እገዛ በማድረግ ዙሪያ ለማኅበራቱ ምን ያደረጋችሁት ነገር አለ፡፡*

ወ/ሮ ሮማን፡- የእኛ ማኅበር የበጎ ፈቃደኞች ማኅበር ነው፡፡ አትራፊ ድርጅት አይደለም፡፡ እኛ ሥራችን ሴቶችን ማብቃት ነው፡፡ በተቻለን መጠን ግን ሴቶቻችን ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ ራሳቸውን እንዲጠብቁ፣ ቤተሰቦቻቸውን፣ ጎረቤተቻቸውን እንዲጠብቁና ትምህርት እንዲያስተላልፉ እየተደዋወልን አንቅተናል፡፡ አቅም ያለው ማኅበር በሚኖርበት አካባቢ ደግሞ ከኅብረተሰቡ ጋር እየተነጋገረ የሚጠነቀቁበትን መንገድ አሳውቀናል፡፡ ሥልጠናም ለመስጠት እንደሚታወቀው መሰብሰብ ስለማይቻል ባለሉን አማራጮች ሁሉ ተጠቅመን ለማስተማር ሞክረናል፡፡

*ከማኅበራቶቻችሁ ጋር ዘመናዊ በኾን ዘዴ ማለትም በኢንተርኔትና መሰል ነገሮች ለመገናኘት አልሞከራችሁም? ለንቃተ ህሊና የሚኾኑ ወረቀቶችን በመበተን? ነጋዴ አባላት ሲኾኑ የሚያገኙትን ጥቅም ለማሳወቅ አልጣራችኹም?*

ወ/ሮ ሮማን፡- የአቅም ጉዳይም ስላለብን እንደ ልባችን የተባለውን ለማድረግ አልቻልንም፡፡ ነገር ግን ባለን አቅም በየወቅቱ እየተደዋወልን ከኅብረተሰቡ ጋር እየተነጋገርን ነው፡፡ ኅብረተሰቡን ምን ያህል ሊጎዳ እንደሚችል በተገኘው አጋጣሚ በቻልነው ሁሉ እየተነጋገርን ነው፡፡

*ከማኅበራቱ ለእናንተ የሚደርሳችኹ ነገር አለ? መልካም ይሁን ጥሩ የሚነግሯችኹ ጉዳዮች አሉ?*

ወ/ሮ ሮማን፡- ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ኾኖ ስለማይገኝ የሚነግሩን አንዳንድ ነገሮች አሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከተለያዩ ቦታ ይደውሉና ባለው ሁኔታ ደግሞ ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ችግሮችን ለመፍታት እንጥራለን፡፡ ለምሳሌ ከገላን ከተማ አሳተዳደር ጋር የተፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት ሞክረናል፡፡ ቡራዩም እንደዚሁ ቢሮ ሁሉ ተሰጥቷቸው እየተንቀሳቀሱ ነው፡፡ በጥቅሉ ከተለያዩ አካላት ጋር ተነጋግረን ችግሮችን ለመፍታት ጥረናል፡፡ በተጨማሪም በሴቶች ፌድሬሽን በኩልም ጥሩ አስተዋፅዖ እየተደረገልን ነው፡፡ በተለይ በማበረታታት በኩል ብዙ ነገሮችን እገዛ ያደርጉልናል፡፡ በማሰባሰብም ኾነ ግንዛቤ በማስጨበጥ እገዛዎችን ያደርጉልናል፡፡ ነገር ግን በሴቶች ዙሪያ መሥራት የሚገባው ማንኛውም አስፈላጊ ነገር ሙሉ በሙሉ ከመፍታት አንፃር ችግሮች አሉበት፡፡

*ከመንግሥት ፖሊሲዎች አንፃር ለእናንተ የሥራ ሂደት እንቅፋት የኾነና ቢሻሻል የምትሉት ይኖራል?*

ወ/ሮ ሮማን፡- እኛ የኦሮሚያ ልክል የሴቶች ነጋዴ ማኅበር ሕጋዊ ፈቃድ አለን፡፡ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የሥራ ፈጠራቸውን ባዛር በማዘጋጀት በተለያየ መልኩ ራሳቸውን የሚስተዋውቁበት መንገድ አመቻችቶልናል፡፡ ያንን የተመቻቸውን ይዘን በእቅዳችን መሠረት ለመውጣት ደግሞ ባዛር ሠርታችሁ ልትዘልቁት አትችሉም የሚለን ክፍል አለ፡፡ ያም እንደ ኦሮሚያ እንደ ኢትዮጵያ የሴቶች ማኅበር ሁሉ ብዙ ችግሮች አጋጥመውን ነበር፡፡ ወ/ሮ ግደይም ታውቃለች፡፡ ብዙ ትግል አለ፡፡ አሁን ደግሞ ከቀድሞው የተሻለ ነው፡፡ አሁን እንደ ኦሮሚያ አዳማ ላይ በአዳማ ከተማ አስተዳደር አንዳንድ ቢሮዎ ተሰጥተውን እየሠራን ነው፡፡ ነገር ግን መፈታት ያለባቸው ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ አሁን ስድስት ቢሮ ነው ፈቃዳችን፡፡ ይሁን እንጂ እኛ የኦሮሚያ ነጋዴ ሴቶች የምናገኘው ነገር ምንም የለም፡፡

*እርሱን ለማግኘት ችግር አለው? ምንድነው ችግሩስ?*

ወ/ሮ ሮማን፡- አዎ ችግር አለው፡፡ እኛን የሚታገለን ንግድ ምክር ቤት ነው፡፡ የነጋዴ ሴቶች ንግድ ምክር ቤት ማቋቋም አትችሉም ይሉናል፡፡ ለምሳሌ በኬንያ የተለያዩ የነጋዴ ሴቶች ምክር ቤቶች አሉ፡፡ እኛም እንደ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ነጋዴ ሴቶች ማኅበር ይቋቋምልን፡፡ ይህን ከእኔ በፊትም ወ/ሮ እንግዳይ ገልፀውታል፡፡ ይሄ ቢደረግልን የራሳችንን ቁጠባዎች አቋቁመን ሴቶቻችን የሚበረታቱበትና የሚጠነክሩበት መንገድ ይከፍትልናል፡፡ ስለዚህ ይህ ቢሻሻልልን ደስ ይለናል፡፡

*በመጨረሻም ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ እደሉን ልስጦት፡፡ ወደፊትሥ ምን ለመሥራት እንዳሰቡ ቢገልፁልን?*

ወ/ሮ ሮማን፡- የማስተላልፈው ሀገራችን ኢትዮጵያ የነበረውን የጭንቀት ጊዜ አሳልፎት እዚህ በመድረዛችን ደስ ብሎኛል፡፡ ሌላው እኛ ነጋዴ ሴቶች ማኅበራችን የፆታ ማኅበር ነውና መንግሥት ይሄንን ትኩረት ሰጥቶ ሴቶችን ለሕዝባችንም ለሀገራችንም ቀኝ እጅ እስከኾኑ ድረስ ከኢኮኖሚ ጥገኝነት እንዲወጡ ሊረዱን ይገባል እላለሁ፡፡


ተጨማሪ ጥያቄዎች አለዎት?

በድህረ ገፃችን www.initiativeafrica.net በኩል በምንገልጸው ዕለታት በአንዱ በሚሰናዳው የመረጃ መቀያየሪያ ክፍለ ጊዜ ላይ ይታደሙ ወይም በ 011 662 26 40 41 ይደውሉ፡፡

Initiative Africa



“ይህ ቡድን ህዝቡን ቢያከብር ኖሮ አሁን ያደረገውን ነገር ባላደረገ ነበር፡፡ ለምሳሌ የአክሱም ኤርፖርትን ጨምሮ በመሰረተ ልማቶች ላይ እየፈጸመ ያለው ድርጊት የትግራይን ብቻም ሳይሆን የኢትዮጵያን ህዝብ ሀብት የማውደም ነው፡፡ የአክሱም ኤርፖርትን እና መሰል መሰረተ ልማቶችን ማፈራረስ ከትግራይና ከኢትዮጵያ አልፎ በአለም አቀፍ ደረጃ ቱሪዝሙንም መጉዳት ነው፡፡ ይህ ቡድን ህዝባዊነቱ ልሳኑ ላይ እንጂ ተግባሩ ላይ አለመሆኑን እያደረገው ያለው ጥፋት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው”

አበባው አያሌው፣ የታሪክ ምሁር ረዳት ፕሮፌሰር
አዲስ ልሳን ጋዜጣ፣ ህዳር 19 ቀን 2013 ዓ.ም



“በእውነቱ አገራችን በዚያ አካባቢ የከፈለችው የሰብአዊና የማቴሪያል ዋጋ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ የውጭ ኃይሎች ከፍተኛ ተሳትፎ ያለበት መሆኑ ባይካድም ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ጀምሮ የእኛም ድክመት ቀላል አይደለም፡፡ ብዙ ስህተቶች ተሠርተዋል፡፡ በዝርዝር ጽፌዋለሁ፡፡ ወዳጀና ወንድሜ አምባሳደር ዘውዴ ረታም በሚያረካ ሁኔታ አስቀምጦታል፡፡ ብዙ ተዋናዮች ነበሩ፡፡ በእኛም በኩል ብዙ ስህተቶች ተሠርተዋል፡፡ በተለይ ደግሞ በወታደራዊው የአገዛዝ ሥርዓት የተፈፀመው በጣም አሳዛኝ ነገር ነው፡፡ የሚያሳዝነው የኤርትራ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን የራሳቸውን አገር ከመሠረቱም በኋላ ጦርነቱ አልቀረልንም፡፡ በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ብዙ ኢትዮጵያዊያንም ኤርትዊያንም የሆኑ ወገኖቻችንን አጥተናል፡፡ በሺሕዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ረግፈዋል፡፡ አዝናለሁ”

ዘውዴ ገብረ ሥላሴ፣ ዶ/ር ደጃዝማች
ሲራራ ጋዜጣ፣ ሕዳር 18 ቀን 2013 ዓ.ም



“የሆነ ፌስቡክ ላይ ያየሁት ነገር ነበር ለካፍ ደብዳቤ ተልኮ አዲስ አበባ ያሉት ይጫወቱ ተብሎ ተጠይቋል ይሳካ አይሳካ ባላውቅም ይሄ ተስፋ ያለው ይመስለኛል... አዲስ አበባ ያለነው ከአማኑኤል ገ/ሚካኤል ጋር 12 ነን፡፡ ከተፈቀደ ጥሩ ይመስለኛል፡፡ ሁሉም በየራሱ ከልምምድ ስላልተስተጓጎለ መጫወት እንችላለን ብለን ስለምናስብ ባይሳካ ቅር ያሰኛል፡፡ ግን አገራዊ ችግር በመሆኑ ምን ማድረግ ይቻላል፡፡ አምናም ተሳትፈን ነበር፤ የዛን አመት ቁጭት ለማስተካከል አስበን የነበረ ቢሆንም ያው በሀገር የመጣ በመሆኑ መቀበል የግድ ይላል፡፡ በዚያ ላይ ግን ሊግ ካምፓኒው ምን አስቦ እንደነበር ባናውቅም አንፈልግም ማለቱ ይገርማል... ያ ሁሉ አልፎ አሁን ይሄ ችግር መከሰቱ ግን ቅር ያሰኛል፡፡ ብንሳተፍ ግን አሪፍ እድል መሆኑ ይሰማኛል፡፡ ከዚህ ቃለምልልስ በኋላ ግን ሲሞከር የነበረው ሙከራ ከሸፎ ካፍ ከ14 ተጨዋች በታች አልቀበልም በማለቱና ለጨዋታው ዝግጁ የሆኑት ተጫዋቾች 11 ብቻ በመሆናቸው የመቐለ 70 እንደርታ በሻምፒዮንስ ሊግ እንደማይሳተፍ ተረጋግጧል”

አሚን ነስሩ፣ መቐለ 70 እንደርታ እግር ኳስ ተጫዋች፣
ሀትሪክ ስፖርት ጋዜጣ፣ ህዳር 19 ቀን 2013 ዓ.ም



“ውጊያው እንዳለቀ ሳይሆን ታንኩ እስከመጣልን ጊዜ ድረስ ነበር፡፡ የተረፍን ትንሽ ነበርንና ወደ አዋሽ አርባ ሄደን ስልጠና ወሰድን፡፡ በወቅቱ ከፊል ምጽዋ ተይዞ ነበር፡፡ አንድ ታንከኛ ሻምበል በአስቸኳይ ምጽዋ መግባት ነበረበት፡፡ 29ኛ ሜካናይዝድ የሚባል ሚሊሽያ ስለነበር እሱንም እዚያው አሰብ ላይ አቋቋምነው፡፡ ግን ውጊያ መግባት የማይችል ስለነበር በመርከብ ተጓጉዘን አስሩ ታንክ ላይ የነበሩትን ልጆች ምጽዋ ላይ አራግፈን እኛ ደግሞ ዳህላክ ላይ ወረድን፡፡ ከዚያ ሦስት ወር ናሁራ ደሴት ላይ ስልጠና አደረግን፡፡ እኔ የሜካናይዝዱን ያዝኩ፣ ሌሎቹ የእግረኛውን ይዘን ሐምሌ 5 ቀን 1970 ምጽዋ ገባን፡፡ በቀጣዩ ቀን ሻዕቢን ሰብረነው ገባን፡፡ በወቅቱ ከአስመራ እስከ ምጽዋ የነበረውን ባቡር ሐዲድ ነቃቅሎ ምሽግ ሰርቶበት ነበር፡፡ ከዚያ ምሽግ ውስጥ ነው ሰብረን ያወጣነው”

ካሳዬ ጨመዳ፣ ሊቀሕሩያን ብ/ጄ/ል
አዲስ ምንጭ መጽሔት፣ ህዳር 2013 ዓ.ም



“ይህ የሽፍቶች ስብስብ በአገርና በህዝብ ላይ ለ27 ዓመታት ሲጫወት ኖሯል፡፡ አገር እንድትበተን፣ ታሪክ እንዲጠፋና ትውልድ እንዲመክት ተግቶ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ቡድኑ የአገር ፍቅር ክብር የሚያውቅ አይደለም፡፡ የጁንታው ቡድን የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ኮትኩተው ያሳደጉት ክፉ ውልድ ነው፡፡ ቡድኑ በሰሜን እዝ የመከላከያ ሰራዊትም ሆነ በማይካድራ በፈፀመው የጅምላ ጭፈጨፋ በአለም አቀፍ የጦር ፍርድ ቤት ሊጠየቅ ይገባል፡፡ በእነዚያ የሽፍታ ቡድኖች የተፈፀመው ወንጀል፣ በናዚ ወታደሮች ከተፈጸመው በምንም አያንስም፡፡”

ታደሰ ታምራት፣ ሌ/ጄ
አዲስ አድማስ ጋዜጣ፣ ህዳር 19 ቀን 2013 ዓ.ም



“የዓለም የንግድ ድርጅት ኢትዮጵያ በአባልነት እንድትገባ ያለው ፍላጎት ከፍተኛ ነው፡፡ በወረርሽኙ ምክንያት ያልተከናወኑ ሥራዎች እንዴት መቀጠልና መካካስ እንዳለባቸው፣ ከድርጅቱ ጋር ሥራ ከመጀመሩ በፊት በአገር ቤት በኩልም ማለቅ ያለባቸው ሥራዎች እየተጠናቀቁ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ በኩል አባልነቱን ለመቀላቀል ከሚደረጉ ሥራዎች አንዱ፣ ከአገራዊ ጥቅምና ፍላጎት አንፃር በተለይም ከሸቀጦች ዓይነትና ገበያው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ይከፈት የሚሉ ያላለቁ ተግባራት አሉ፡፡ ኢትዮጵያ መጀመርያ አባልነቱን ካገኘች በአንድ ጊዜ ሁሉም ነገር የማይከፈትና በሒደት እየታዩ ወደ ሥርዓቱ የሚገቡ ሸቀጦች የሚኖሩ ሲኾን ከአባልነቱ ተጠቃሚ ለመሆን በሁሉም ዘርፎች የማምረት አቅም ጠንካራ መሆን ይገባዋል፡፡”

አቶ መላኩ አለበል፣ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር
ሪፖርተር ጋዜጣ፣ ህዳር 20 ቀን 2013 ዓ.ም



“ህዝቡ እና እነርሱ ሆድና ጀርባ ናቸው፡፡ እነርሱ የሚነዙት የትግራይ ህዝብ እና ህወሃት አንድ ነው የሚል ፕሮፖጋንዳ ነው፡፡ ህወሓት ሲሉም አመራሩንና ተራውን አባል አይለዩም፡፡ ድርጅቱና ህዝቡ አንድ ነው፡፡ ድርጅትና ህዝብ አንድ ሊሆን አይችልም፡፡ ድርጅት እና ህዝብ አንድ ቢሆንማ ኢሰፓ እና ህዝብ አንድ ይሆኑ ነበር፤ ወይ ኢህአዴግ እና የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ ነው ማለት ነበር፡፡ ይህ የማይሆን ነገር ነው፡፡ ድርጅት አንድ ወቅት ተፈጥሮ ሊከስም የሚችል ነው፡፡ የሚተካካ የሚቀየር ነገር ነው፡፡ ህዝብ ግን የነበረ፣ ያለና ወደፊትም የሚኖር ቀጣይ ማህበረሰብ ነው፡፡ የህወሃት አመራሮች በህዝቡ ሊነግዱ ስለሚፈልጉ ሲነግዱም ነበር፡፡ አሁን ደግሞ እንዲከላከልላቸው ለማድረግ ያቀዱትን ነገር ነው”

ዶክተር አረጋዊ በርሄ፣
የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር
ዱም’ዲ ታይምስ ጋዜጣ፣ ህዳር 19 ቀን 2013 ዓ.ም



“እንግዲህ እነሱ ማንንም ህገወጥ ማለት አይችሉም፤ ምክንያቱም እነሱም ራሳቸው ህገወጥ ስለሆኑ፤ ህጋዊ መሰረት የላቸውም፤ ምርጫ የሚሉትም ህገመንግስታዊ አይደለም፡፡ ህገመንግስታዊ ባልሆነ መንገድ ህገመንግስታዊ ተቋም መመስረት አትችልም፤ ሂደቱ ህገመንግስታዊ ካልሆነ ውጤቱም ህገመንግስታዊ አይሆንም፡፡ ብዙ ጊዜ ከ2.7 ሚሊዮን ህዝብ በላይ የተሳተፈበት ምርጫ ሲሉ እሰማለሁ፤ የህዝብ መብዛት እና ማነስ አንድን ምርጫ ህጋዊ እና ህገወጥ አያደርገውም፡፡ አንድ ምርጫ ዲሞክራሲያዊ የሚባለው ሂደቱ ዲሞክራሲያዊ ሲሆን እንጂ ውጤቱ አይደለም፡፡ ስለዚህ ህገመንግስታዊ ድንጋጌው እስከተጣሰ ድረስ 10 ሚሊዮን ህዝብ ቢሳተፍበትም ህጋዊ አይሆንም፡፡ እናም በትግራይ ክልል መንግስት ነኝ ብሎ ያለው አካል ህገወጥ ስለሆነ ሌላን አካል ህገወጥ ማለት አይችልም፡፡ ምርጫውን ካደረጉበት ጊዜ ጀምሮ ዝብ ብሎ ስብሰብ፣ ጓደኛማቾች እንጂ ባለስልጣን አይደሉም”

አቶ አሮን ደጎል፣ ከህግ እና አስተዳደር መምህር
ወይ አዲስ አበባ መፅሔት፣ ህዳር 2013 ዓ.ም

# የዘመቻው መቋጫ ምዕራፍ

## የመጨረሻው የመቀሌ ከበባ

## የዲጂታል ወያኔዎች የእስር ትዕዛዝ

## የትግራይ አርነት እወጃ

## የአዲሱ አስተዳደር የመዋቅር ዝርጋታ

የተከበራችሁ አንባቢያን የሰሜኑ ወታደራዊ የሕግ ማስከበር ዘመቻ ለሦስት ሳምንታት ተካሄዶ ባሳለፍነው ቅዳሜ ሕዳር 19 ቀን 2013 ዓ.ም የትግራይ ክልል ርዕሰ ከተማ የኾነችው መቀሌ መያዟን ተከትሎ መጠናቀቁን መንግሥት አስታውቋል። ኾኖም መንግሥት በሁነቱ ተጠርጣሪዎች ናቸው ያላቸውን ግለሰቦች በሕግ ቁጥጥር ሥር የማዋሉን ተግባር አጠናክሮ ቀጥሏል። እኛም ከዘመቻው መጀመሪያ ሳምንት አንስቶ የየእለት ውሎውን ታሪካዊ ዳራ ቀን እየጠቀስን በቅደም ተከተል ስንዘግብላችሁ ቆይተናል። በዚህ ሳምንትም የመጨረሻውን የዘመቻ ሂደትና አጠቃላይ ሁኔታ በሚከተለው መልኩ አዘጋጅተንላችኋል።

### ሐሙስ ሕዳር 17/2013

ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ከ72 ሰዓታት የእፎይታ ጊዜ በኋላ የመጨረሻውና ሦስተኛው የዘመቻ ምዕራፍን መከላከያ ሠራዊት ተፈፃሚ እንዲያደርግ ትዕዛዝ መሠጠቱን አስታውቀዋል። በዘመቻው ለንፁሐን ሰዎች ከፍተኛ ጥንቃቄ ይደረጋል፣ በሕዝብ ላብ የተሰራችው መቀሌ ከተማ የከፋ ጉዳት እንዳያገኛት የሚቻለው ሁሉ እንደሚደረግ በመግለጫው ተጠቁሟል። የመጨረሻው ዘመቻ ከመጀመሩ በፊት በነበረው የእፎይታ ጊዜ በርካቶች እጃቸውን እንዲሰጡ መጠየቁና ብዙ የትግራይ ወጣቶችም የትህነግን እኩይ ዓላማ ተረድተው እጃቸውን መሠብሰባቸው ተነግሯል። በመግለጫው የእፎይታ ጊዜው ዓላማ ሁለት እንደነበርና የመንግሥት ዋና ፍላጎት ጦርነት ሳይሆን ሕግን ማስከበር እንደሆነ ተነግሯል። ወንጀለኛው ቡድን በሠላም እጁን ከሠጠ ዘመቻውን በአነስተኛ ዋጋ ለማከናወን የነበረው ዓላማ አንዱ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የትህነግ የጥፋት ዓላማ ዘግይቶም ቢሆን የገባው አንድ ሰው ከተገኘ ያንን ሰው ለማትረፍ እንዲቻል ነው ተብሏል። እነዚህን ዓላማዎች የያዘው የእፎይታ ጊዜ በትህነግ እብሪት ምክንያት መዘጋቱ በመግለጫው ተጠቅሷል። በእለቱ በተጀመረው ሦስተኛው የዘመቻ ስልት ቅርሶች፣ ቤተእምነቶች፣ የሕዝብ መገልገያዎች፣ የልማት ተቋማትና የሕዝብ መኖሪያዎች የጥቃት ዒላማ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ ይደረጋል ተብሏል። የመቀሌና የአካባቢው ሕዝብ ትጥቅ ፈትቶ በቤቱ እንዲቀመጥና ከወታደራዊ ዒላማዎች ርቆ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ጥሪ ቀርቦ ነበር።

በሌላ በኩል፣ ምክትል ጠ/ሚ እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ዘመቻውን በማስመልከት ወደ እንግሊዝ አቅንተው ነበር። ከእንግሊዝ ጠ/ሚ ዓለም አቀፍ ጉዳዮችና ምክትል ብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ሚኒስትር ዴቪድ ኩኣሪ ጋር መመካከራቸው ተነግሯል። ምክትል ጠ/ሚሩ የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ ለአውሮፓ ሀገራት ግልጽ ለማድረግ በጀመሩት ዓለም አቀፍ ተልእኮ ለንደን መግባታቸው ታውቋል። ከእንግሊዝ ባለሥልጣናት ጋር በነበራቸው ቆይታ መንግሥት ሕግ የማስከበር እርምጃ ለመውሰድ መገደዱን፣ እንዲሁም ጥፋተኞችን ለሕግ የማቅረብ ጠንካራ እንቅስቃሴ ውስጥ መግባቱን አስረድተዋል። በትህነግ ሴራ በሕዝብና በመንግሥት ላይ በርካታ ጥፋቶች መፈፀማቸውን ማሳወቃቸው ተነግሯል። የእንግሊዝ ባለሥልጣናት በበኩላቸው፣ ሕግ የማስከበሩ እርምጃ ንፁሐን ዜጎችን ከማንኛውም አደጋ የመጠበቅ እና የመከላከል ዓላማ በማስቀመጥ፣ በኃላፊነት ስሜት እንዲያስፈጽሙና የሰብአዊ ድጋፍ መስጫ መንገዶች ማመቻቸት እንደሚገባ ጠቁመዋል::

በሌላ በኩል፣ በእለቱ ጋምቤላ ክልል ውስጥ በትህነግ ታቅዶ የነበረ የጥፋት ሴራ መክሸፉ ተነግሯል። የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኡሞድ ኡጁሉ እንደተናገሩት፣ በክልሉ ታቅዶ የነበረው የጥፋት ሴራ በሕዝቡና በፀጥታ ኃይሉ ቅንጅት መክሸፉን ተናግረዋል። ሴራው በዝርዝር ባይገለፅም፣ ለወደፊት ትህነግ ዘርግቶት የነበረውን የጥፋት መረብ ለመበጣጠስ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን ገልፀዋል። የትህነግ ሴራ በብዛት በክልሉ ነበረ የተባለ ሲሆን፣ የጥፋት ሴራውን ሊፈፅሙ የነበሩት አብዛኞቹ በቁጥጥር ሥር ውለዋል ተብሏል። የተቀሩትን ለመያዝ እየተሞከረ ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ ክልሉን አልፎ ወደ ደቡብ ሱዳን በሚያስኬዱ ስምንት የመውጫ በሮች የጥፋት ቡድኑ አባላት ለመውጣት መሞከራቸውንም ጠቁመዋል። ክልሉ ከትህነግና ከኦነግ ሸኔ ጋር ግንኙነት አላቸው ብሎ የጠረጠራቸውን 65 ግለሰቦችን እንዳሰረ አስታውቋል።

በሌላ በኩል፣ በሰሜን ዕዝ ላይ ጥቃት እንዲፈፀም አድርገዋል ተብለው የተጠረጠሩ ከፍተኛ መኮንኖች ለሁለተኛ ጊዜ በእለቱ ፍርድ ቤት ቀርበዋል። የሰሜን ዕዝን የሬዲዮ ግንኙነት በማቋረጥ በጦሩ ላይ አሰቃቂ የግድያ ወንጀልና ዝርፊያ እንዲፈፀም አድርገዋል ተብለው የተጠረጠሩ፣ 7 ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖችና 5 ግለሰቦች ናቸው በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን በቁጥጥር ሥር ውለው የነበሩት። የመከላከያ ኮሚኒኬሽን ኃላፊ ሜጀር ጄነራል ገ/መድህን ፍቃዱ፣ የምዕራብ ዕዝ አዛዥ ሜ/ጄነራል ይርዳው ገ/መድህን፣ የደቡብ ዕዝ የሥራ ኃብት ልማት አዛዥ ብርጋዴል ጄነራል ገ/ህይወት ሲስኖስ፣ የሰሜን ዕዝ መረጃ ዘርፍ ኃላፊ ብርጋዴል ጄነራል ኢንሶ ኢጳጆ እራሾ፣ ብርጋዴል ጄነራል ፍስሃ ገ/ሥላሴ እንዲሁም ኮለኔል ደሳለኝ አበባና ኮሌኔል እያሱ ነባሽ የተጣለባቸውን ኃላፊነት ወደ ጎን በመተው ከትህነግ ተልዕኮ በመቀበል ሠራዊቱ እርስ በርሱ እንዳይገናኝ አድርገዋል ተብለዋል።

በተጠረጠሩበት ድርጊታቸው ሳቢያ የደረሰው ጉዳት እየተጣራ እንደሆነ ተነግሯል። ከውጭ ጠላቶችና ኦነግ ሸኔን ከመሳሰሉ ሕገ ወጥ ቡድኖች ጋር በማበር፣ የሃይማኖትና የብሔር ግጭት መማስነሳት ሀገር ለመበተን ሲሰሩ እንደነበረም መጠርጠራቸውና መርማሪ ፖሊስ ለችሎቱ አሳውቆ ነበር። ተጠርጣሪዎቹ ሀገርን በመክዳት ወንጀልና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለመናድ በሚል ወንጀል መጠርጠራቸው ተነግሯል። በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ 1ኛ የጊዜ ቀጠሮ በተሰጠው የ14 ቀን ጊዜ የተሰሩ ሥራዎችን 2 መርማሪዎች አቅርበዋል። የ6 ሰዎችን ምስክርነት ያቀረበው መርማሪ ፖሊስ ቤታቸው ሲፈተሽ ከወንጀሉ ጋር ግንኙነት ያላቸው የጦር መሳሪያዎች በኤግዚቢትነት መያዛቸውን ተናግሯል። ተጨማሪ ምስክሮችን ለማቅረብ፣ ያልተያዙትን ለመያዝና አጠቃላይ የመረጃ ማሰባሰብ ሥራውን ለማከናወን ተጨማሪ ጊዜ እንደሚያስፈልግ ተጠይቋል። ተጠርጣሪዎች፣ “ጊዜ አያስፈልግም፣ ዋስትና ይፈቀድልን፣ ግንኙነት የለንም” እያሉም በአንባ ጭምር ለፍ/ቤቱ ክሳቸውን ያስተባበሉ ነበሩ። ግራቀኙን የሰማው ፍ/ቤቱ የ13 ቀን ጊዜ ሰጥቷል።

በእለቱ ይፋ ከተደረገ የዘመቻው አካል ውስጥ ሌላኛው 21ኛ ክፍለ ጦርን የተመለከተ ነው። ፅንፈኛው የትህነግ ቡድን ደምስሼዋለሁ ብሎ የውሸት ዜና ያሰራጨበት ይኸ ክፍለ ጦር፣ በከፍተኛ ጀግንነት በድል እየገሰገሰ መሆኑን የክፍለ ጦሩ ኦፕሬሽን ምክትል አዛዥ ኮሎኔል መንግሥቱ ደሴ ተናግረዋል። በራያ ግንባር ተልዕኮ ተሠጥቶት የነበረው ይኸ ክፍለ ጦር የጠላቱን ምሽግ እያስለቀቀ እንደሆነ ተገልጿል። በሰሜን ዕዝ ላይ የተፈፀመው የክህደት ተግባር ያስቆጨው ክፍለ ጦሩ በተመደበበት ግንባር በከፍተኛ ወኔና ቁጭት እየተዋጋ እንደሆነም አዛገፉ አሳውቀዋል። ክፍለ ጦሩ በፈፀመው ከባድ ጥቃት የትህነግ ታጣቂዎች መቋቋም አቅቷቸው እየተማረኩና እየሸሹ መሆኑም ተነግሯል። በከሀዲው ቡድን ተይዞ የነበረን የኮንክሪት ምሽግ በማፈራረስ አየር መቃወሚያውን ከጥቅም ውጭ ማድረጉን የክፍለ ጦሩ አዛዥ ተናግረዋል።

በሌላ በኩል፣ “ለሀገር ልጅ የማር እጅ” በሚል ለተፈናቃዮች የሚሆን ድጋፍ ለማሰባሰብ ተብሎ ለተጀመረው መርሃ ግብር የአዲስ አበባ አስተዳደር የፕላቲኒየም ድጋፍ ማድረጉ ተገልጿል። በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች በጀመሩት በዚሁ መርሃ ግብር በርካቶች በድጋፍ ማሰባሰቢያው ላይ መሳተፋቸው ተነግሯል። መርሃ ግብሩ የተጀመረ ሰሞን፣ “ለትግራይ ተፈናቃዮች ነው የታሰበው” በሚል ተቋውሞ ገጥሞት ነበር። በማይካድራ በተፈፀመው ዘግናኝ ጭፍጨፋ ለደረሰው እልቂት ተጠያቂ ናቸው የተባሉ፣ “ሳምሪ” የተሰኙ የወጣት አደረጃጀቶች ሱዳን ተሰደዋል፤ ለእነሱ እርዳታ አይገባም በሚል ብዙዎች በማኅበራዊ ትሥሥር መርሃ ግብሩን ሲቃወሙት ነበር። የሕዝቡን ብሶት የተመለከቱት አርቲስቶች በየግላቸው ይቅርታ የጠየቁ ሲሆን፣ አመራሮቹም እኛ ለሁሉም ተጎጂዎች ነው ያሰብነው በማለት እቅዳቸውን በማሳወቅ ስሞታውን አስተባብለዋል። የአዲስ አበባ አስተዳድርም ድጋፉን ስናደርግ የተጎዳው ወገን ከመላው ሀገር የተውጣጣ መሆኑን ተረድተን ነው ብሏል።

ሌላው በእለቱ ከመንግሥት በኩል የተገለፀው በትግራይ ክልል የሰብአዊ ድጋፍ ስለሚሹ ዜጎች ነው። በክልሉ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች መንግሥት የሰብአዊ ድጋፍ ከሚሰጡ አካላት ጋር በመሆን ድጋፍ ለማቅረብ እንደሚሠራ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት አሳውቋል። የተፈናቀሉ ዜጎችን ሁኔታ የሚያጣራ ኮሚቴ ተልኮ እያጣራ እንደሆነና ድጋፉ በሰላም ሚኒስቴርና በሌሎች የፌደራል ተቋማት ቅንጅት እንደሚደርስ ተነግሯል። ድጋፉ በመጀመሪያ የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የንፁህ ውሃና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች መሆናቸው ታውቋል። ድጋፉ ሁኔታዎች እስከሚረጋጉ ይቀጥላል የተባለ ሲሆን፣ ስደተኞች ወደ አካባቢያቸው እንዲመለሱ ለማድረግ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር አብሮ እንደሚሰራም መንግሥት ተናግሯል።

### አርብ ሕዳር 18/2013

ዘመቻው በተጀመረ በቀጣዩ ቀን ጠ/ሚ ዐቢይ ከአፍሪካ ኅብረት ልዑካን ጋር መወያየታቸው ተነግሯል። ጠ/ሚ ጽ/ቤት እንዳሳወቀው፣ ልዑካኑን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው በኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ተነጋግረዋል። የቀድሞ የላይቤሪያ ፕሬዝዳንት ኤለን ጆንሰን ሰርሊፍ፣ የቀድሞው የሞዛምቢክ ፕሬዝዳንት ጆአኪም ቺሳኖ እና የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት ኪጋማ ሞትላንቴ የመሩት ልዑክ


በትግራይ ክልል እየተካሄደ ባለው የሕግ ማስከበር ዘመቻ ዙሪያ መወያየቱ ታውቋል፡፡ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ ትህነግ ለ2 ዓመታት ያህል ሀገሪቱን ለማተራመስ የተጓዘችበትን ርቀትና መንግሥት ሲያሳየው የቆየውን ሆደሰፊነት ለልዑካኑ አብራርተዋል፡፡ ለዘመቻው መጀመር ምክንያት የሆነው የትህነግ ቡድን በሰሜን እዝ ላይ የወሰደው አሳፋሪ እርምጃ መሆኑን ጠ/ሚ/ሩ ለልዑካኑ አስረድተዋል፡፡ ለብዙዎች ስጋት የሆነው የንጹሃን ደህንነትን ትኩረት በመስጠት ዘመቻው በጥንቃቄ እየተከናወነ መሆኑንም፣ ለተፈናቀሉ ድጋፍ የሚያደርግ ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ተግባር መግባቱንም አሳውቀዋል፡፡ በማይካድራ የተፈፀመው ዘግናኝ ዘር ተኮር የግፍ ጭፍጨፋ በውይይቱ ላይ የተነሳ ሲሆን፣ ቡድኑ ወደ ሕግ እንደሚቀርብ በአጽንኦት ተነግሯል፡፡

ከመቀሌ በስተቀር በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ባሉና ከጥፋት ቡድኑ ነፃ በወጡ አካባቢዎች የመንግሥት ተቋማት መሠረታዊ አገልግሎት መጀመራቸው ተነግሯል፡፡ በጠገዴ ወረዳ ቀራቅር መስመር ከትህነግ ነፃ በተለቀቁት አካባቢዎች የመንግሥት ተቋማት አገልግሎት መጀመራቸው ብቻ ሳይሆን፣ ሕዝቡም ወደ እለት ተዕለት እንቅስቃሴው መመለሱ ተዘግቦ ነበር፡፡ የኮማንድ ፖስት አስተባባሪ የሆኑት አቶ ብርሃኑ ተድላ የማረጋጋት ሥራው መሠራቱን ተናግረዋል፡፡ ትህነግ በሰሜን ዕዝ ላይ ጥቃት በፈፀመችበት ዕለት ቅራቅር ከተማንም ለመያዝ ከፍተኛ ጥረት አድርጋ እንደነበር አስታውሰዋል፡፡ በእለቱ ያለ የሌለ ኃይል ተጠቅመው ጥቃት ቢሰነዝሩም፣ በወቅቱ የአማራ ልዩ ኃይልና ሚሊሻ ጥቃቱን መክቶ በመቆየት በመከላከያ ሠራዊት በመታገዝ ቀራቅርን ሙሉ በሙሉ አስለቅቆ ከተማ ንጉሥንም በመቆጣጠር እስከ ቃፍታ ሁመራ መዘለቁን አስታውሰዋል፡፡ አሁን ወደ ነበረበት የእለት ተዕለት ተግባር ሕዝቡ እንዲመለስ እየተሠራ እንደሆነ አሳውቀዋል፡፡ በየጫካው ተቆርጠው የቀሩ የትህነግ አባላት መኖራቸው እንደሚታወቅና ቦታቸውን ለይቶ ለመያዝ በፀጥታ ኃይል ክትትል እየተደረገ መሆኑን አስተባባሪው ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት መቀሌንና የወንጀለኛው ቡድን አባላትን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ስታራቴጂክ ቦታዎችን እንደያዘ አሳውቋል፡፡ ቦታዎቹን ለመቆጣጠር በተደረገው ዘመቻ ከአጀማመሩ ጀምሮ እንደነበረው የትግራይ ሕዝብ ለመከላከያ ሠራዊት ወገንተኝነት ማሳየት መቀጠሉም ተነግሯል፡፡ ሀውዜን፣ አልነጃሺ፣ አዲቀያህ፣ ማይመሳኖን እና ውቅሮ ከተማን ከታጠቀው የትህነግ ቡድን መሉ በሙሉ ነፃ ማውጣቱን አሳውቋል፡፡

ከ72 ሰዓታት እፎይታ በኋላ እጅን ያልሰጠውን ኃይል ለመደምሰስ ሦስተኛው ምዕራፍ ዘመቻ በተጀመረ በ2ኛው ቀን፣ መቀሌ ከተማ አቅራቢያ የሚገኙ ከተሞችን መከላከያ እንደተቆጣጠረ ተናግሯል፡፡ የመከላከያ ሠራዊት ኀብረት ሥልጠና ዋና መምሪያ ኃላፊ ሌተናል ጀነራል ሀሰን አብራሂም በሰጡት መግለጫ ከአድዋ ግንባር የተንቀሳቀሰው ሠራዊት ሀውዜንን አብርሃ ወአጽብሃንና ውቅሮን የተቆጣጠረ ሲሆን፣ አጉላንንም በግማሽ ቀን ተቆጣጥሯል ብለዋል፡፡ መሰቦ ተራራን ለመቆጣጠር ጦሩ እየገሰገሰ መሆኑን የተናገሩት እኚህ ወታደራዊ ኃላፊ ተራራውን መያዝ መቀሌን በቀናት ውስጥ ለመቆጣጠር ያስችላል ብለዋል፡፡ የአዲግራቱ 2ተኛ ግንባርም ሳንቀጣ እና አልነጃሺን በመቆጣጠር ውቅሮ ገብቷል ብለዋል፡፡

3ተኛው የራያ ግንባር አዲቀይኽን የተቆጣጠረ ሲሆን፣ ሒዋናን በመቆጣጠር ሁሉንም ምሽጎች ሰባብሮ ወደ መቀሌ እየተጠጋ መሆኑን አሳውቀዋል፡፡ መቀሌን በቀላሉ መቆጣጠር የሚያስችሉ ድሎች በወታደራዊው ግንባር ብቻ ሳይሆን፣ በፕሮፓጋንዳ ጭምር ቡድኑ እየተሸነፈ ማፈግፈግ መጀመሩ ተነግሯል፡፡ በአጠቃላይ፣ በውጊያው ከባድ የሚባል የመከላከል አቅም የነበረው ኃይል አለማጋጠሙና በጉላን በኩል መንገድ ለመዝጋት ቢሞክሩም እንዳልተሳካላቸው ታውቋል፡፡ በራያ በኩል ያለ የሌለ ኃይላቸውን ተጠቅመው መከላከያን ለመከላከል ቢሞክሩም



ቦታቸውን ለመልቀቅ ተገደዋል፡፡ በጦር ግንባር የደረሰበትን የሚያዋርድ ሽንፈት መቀበል ያቃተው የትህነግ ቡድን የውሸት ፕሮፖጋንዳ በማሰራጨት ሕዝብን ለማደናገር መጠመዱን ጦሩ አሳውቋል፡፡

በሌላ በኩል፣ የእለቱን የጦር ሜዳ ውሎ በተመለከተ መግለጫ የሰጡት ሌተናል ጄነራል ባጫ ደበሌ የመከላከያ ሠራዊት ሒዋና ከተማን ከጽንፈኛው ቡድን ማስለቀቁን ይፋ አድርገዋል፡፡ በአውደ ውጊያው ከባድ ሽንፈት የተከናነበው ቡድን ወደ አዲ ጉደም መሸሹን ተናግረዋል፡፡ መከላከያ ከተማዋን ሲቆጣጠር የትህነግ ታጣቂዎች ይጠቀሙባቸው የነበሩትን 6 ታንኮችና ሁለት ዙ-23 ን ጨምሮ በርካታ መሣሪያዎችን መደምሰሱን አሳውቀዋል፡፡ የጥፋት ኃይሉ ሲሸሽ ያወደማቸውን ድልድይ የመሳሰሉ መሠረተ ልማቶችን ሠራዊቱ እየጠገነ ማለፉንም በመግለጫው ጠቅሰዋል፡፡

በሌላ በኩል፣ የሀገራቱን ወቅታዊ ሁኔታ ለተለያዩ ሀገራት ለማሳወቅ አውሮፓ የገቡት ምክትል ጠ/ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን የእንግሊዝ ጉዟቸውን አጠናቀው አርብ ከጀርመን መራሂተ መንግሥት የውጭ ደህንነት ፖሊሲ አማካሪ ጋር ተወያይተዋል፡፡ በትግራይ ክልል እየተወሰደ ስላለው ሕግ የማስከበር ዘመቻ የመንግሥትን አቋም አሳውቀዋል ተብሏል፡፡

## ቅዳሜ ሕዳር 19/2013

በሦስተኛው የዘመቻ ምዕራፍ በሦስተኛው ቀን ከተከናወኑ ተግባራት መካከል በኢትዮጵያ ለተሰማሩ የሕንድና ባንግላዴሽ ባለሀብቶች የተደረገው ገለፃ አንዱ ነው፡፡ በትግራይ ክልል እየተወሰደ ስላለው ሕግ የማስከበር እርምጃ በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለተሰማሩት የሕንድና ባንግላዴሽ ባለሀብቶች ማብራሪያ መሰጠቱን በሕንድ የኢትዮጵያ አምባሳደር ዶክተር ትዝታ ሙሉጌታ ገልፀዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ፣ በትግራይ እየተካሄደ ስላለው ዘመቻ ለአትላንቲክ ካውንስል አባላት ገለፃ ተሰጥቷል፡፡ በአሜሪካ መቀመጫውን ላደረገው አትላንቲክ ካውንስል የምርምርና ጥናት ተቋም አባላት ገለፃውን የሰጡት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዶክተር ጌዲዮን ጢሞቲዮስ፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የኢኮኖሚና ፖሊሲ አማካሪ አቶ ማሞ ምህረቱ እና በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሳደር አቶ ፍፁም አረጋ ናቸው፡፡ እየተወሰደ ያለው እርምጃ የሚኖረውን ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ፣ ከሰብአዊ እርዳታ ድርጅቶች ጋር ስለሚደረገው ትብብር እንዲሁም ስደተኞች ወደ ሀገር ስለሚመለሱበት ሁኔታ ጥያቄ ተነስቶ ማብራሪያ መሰጠቱ ተነግሯል፡፡ በሌላ በኩል፣ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት ስሪል ራማፎሳ ለጠ/ሚ/ር ዐቢይ ምሥጋናቸውን ማቅረባቸው ታውቋል፡፡ የአፍሪካ ኅብረት ልዑካንን ተቀብለው ስላነጋገሩ ምሥጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

ዘመቻውን በተመለከተ በእለቱ ከወጡ መረጃዎች አንዱ፣ የትህነግ ቡድን ቤተክርስቲያን ውስጥ ከባድ መሳሪያ ጭምር አከማችቶ መገኘቱ ነው፡፡ በራያ በኩል የተሰለፈው መከላከያ ሰራዊት እንዳሳወቀው፣ በአዲምስኖ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ውስጥ ትህነግ ብዛት ያላቸው የከባድ መሣሪያ ጥይቶችን ጭምር አከማችቶ ተገኝቷል፡፡ የትህነግ ቡድን ቤተክርስቲያንን ለጦር መሣሪያ ማከማቻነት መጠቀሙ የአካባቢውን ሕብረተሰብ ጭምር ማስቆጣቱ ተዘግቧል፡፡ የመድፍና የቢኤም ጥይት ሲያመጡ፣ "ለምን?" ብለው የጠየቁት ነዋሪዎች፣ "ቤተክርስቲያኑ አይመታም ከተመታም ማስቀመጫውን ሸጣችሁ ታሰሩበታላችሁ" መባላቸውን ተናግረዋል፡፡ የእምነት ቦታችንን አርክሶብናል ያሉ አንድ ምዕመን፣ "ትህነጎች በሠሩት አረመኔያዊ ተግባር ቤተክርስቲያናችን ፈርሶብናል፣ ታቦቱ ይኑር አይኑርም የምናውቀው ነገር የለም" ማለታቸው ተሠምቷል፡፡

በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው የድል ዜና ቅዳሜ ማመሻሻው ላይ በሰበር መልክ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይፋ ተደርጓል፡፡ በማኅበራዊ ትሥሥር ገፃቸው እንዳሳወቁት መከላከያ መቀሌ ገብቷል፡፡ ንፁሀን ዜጎች ዒላማ ሳይሆኑ፣ ከተሞችና ቅርሶች ሳይጎዱ መቀሌ መግባት ተችሏል፡፡ መከላከያ ባለፈባቸው ከተሞች ሁሉ የትግራይ ሕዝብ ለሀገሩ ያለውን ፍቅርና ለመከላከያ ያለውን ክብር አሳይቷል ያሉት ጠ/ሚ/ሩ፣ ሕዝቡ ከትህነግ ቡድን ጋር አለመሆኑን በተግባር አሳይቷል ብለዋል፡፡ ስግብግቡ ቡድን ለትግራይ ሕዝብ በየትኛውም መመዘኛ አይመጥነውም ያሉ ሲሆን፣ የትግራይ ሕዝብ ከእውነት ጋር በመቆም የትህነግን እኩይ ዓላማ ለመፃረር ተመሳሳይ ድጋፍ ለሰራዊቱ ሰጥቷል ብለዋል፡፡ እኔ ከሞትኩ ብሎ ታጣቂው ቡድን ያፈረሳቸውን መሠረተ ልማት በመገንባት ሕዝቡ ወደ ሰላማዊ ኑሮው እንዲመለስ ለማድረግ የተቻለው ያደረጋል ተብሏል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ፣ መቀሌ ገብቷል የተባለው መከላከያ ሰራዊት ከተማዋን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር መቻሉ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ይፋ ተደርጓል፡፡ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ጀነራል ብርሃኑ ጁላ ማምሻውን በሰጡት መግለጫ፣ ከአንድ ቀን በፊት የከተማዋ ነዋሪ ላይ ጉዳት ሳይደርስ እንዴት መቆጣጠር ይቻላል በሚለው ላይ ዝግጅት ሲደረግ ቆይቶ፣ ቅዳሜ ከሰዓት ጀምሮ ከተማዋን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር መቻሉን አሳውቀዋል፡፡ ከተማዋን የተቆጣጠረው መከላከያ በየጎሬው የተደበቁ የትህነግ አባላትን እያሳደደና እያደነ ይገኛል ማለታቸው ተሠምቷል፡፡

የመቀሌ መያዝ ይፋ ከተደረገ በኋላ፣ የሀገር ክህደት ወንጀል በፈፀሙ የተለያዩ እርከን ላይ የነበሩ ወታደራዊ ሹማምንት በፈፀሙት የዘረፋ ወንጀል ንብረታቸው የሚፈለግ የትህነግ ቡድን አባላትና በሀገር ውስጥና ባህር ማዶ ሆነው የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም አገር አፍራሽ መረጃ በሚያሰራጩ ግለሰቦች ላይ የመያዣ ትዕዛዝ ወጥቷል፡፡ የፌደራል ፖሊስ ባወጣው መግለጫ ቀደም ሲል በፈፀሙት የሀገር ክህደት ወንጀል የመያዣ ትዕዛዝ ከወጣባቸው 117 ጄነራል መኮንኖች፣ ከፍተኛ መኮንኖችና የበታች ሹማምንቶች በተጨማሪ፣ 7 በተለያዩ እርከን ላይ

የሚገኙ ወታደራዊ ሹማምንቶች ላይ የመያዣ ትዕዛዝ ወጥቷል፡፡ እነርሱም፡-

1.ሜጀር ጄነራል ዘውዱ ኪሮስ ገብረኪዳን

2.ኮሎኔል ተወልደ ገብረትንሣይ

3.ኮሎኔል ገብረእግዚአብሔር ዓለምሰገድ

4.ኮሎኔል የማነ ገብረሚካኤል

5.ሻምበል ተወልደ ገብረመድህን

6.ኰሎኔል ጌትነት ግደይ

7.ኮሚሽነር ረታ ተስፋዬ ናቸው፡፡

በትህነግ የሥልጣን ዘመን የነበራቸውን ወታደራዊ ኃላፊነት እና ከትህነግ ቡድን ጋር ያላቸውን ጥብቅ ትስሥር ተጠቅመው፣ ከፍተኛ የዘረፋ ወንጀል በመንግሥት ላይ በመፈፀም ከፍተኛ ንብረት ማካበታቸው የተደረሰባቸው 20 ሰዎችም ተዘርዝረዋል፡፡

1.ሌተናል ጄነራል ታደሰ ወረደ- ሥልጠና ዋና መምሪያ ጡረተኛ

2.ሜጀር ጄነራል ገብረአድሃና ገብረዲላ- መረጃ ዋና መምሪያ ጡረተኛ

3.ሜጀር ጄነራል ተክለብርሃን ወልደአረጋይ / ሳንቲም/ — የኢንሳ ዳይሬክተር ጡረተኛ

4.ሜጀር ጄነራል ብርሃነ ነጋሽ /ወዲመድን/ — ሚንስትር ዴኤታ ጡረተኛ

5.ሜጀር ጄነራል ማዕሾ በየነ- ምሥራቅ ዕዝ አዛዥ ጡረተኛ

6.ሜጀር ጄነራል ኢብራሂም አብዱልጀሊል- ሎጀስቲክ ዋና መምሪያ ጡረተኛ

7.ሜጀር ጄነራል ዮሐንስ ወልደጊዮርጊስ — ማዕከላዊ ዕዝ አዛዥ የነበረ ጡረተኛ

8.ሜጀር ጄነራል ነጋሲ ትዕኩ- በሰላም ማስከበር ግዳጅ የከዳ

9.ብርጋዴር ጄነራል አባዲ ፍላንሳ- ምሥራቅ ዕዝ መረጃ ኃላፊ ጡረተኛ

10.ብርጋዴር ጄነራል ፀጋየ ተሰማ /ፓትሪስ/- ኢንስፔክሽን ዋና መምሪያ የነበረ ጡረተኛ

11. ብርጋዴር ጄነራል ምግበ ኃይለ- ሥልጠና ዋና መምሪያ ጡረተኛ

12.ብርጋዴር ጄነራል ተክላይ አሸብር /ወዲአሸብር/- የንዑስ ዕዝ አዛዥ የነበረ ጡረተኛ

13.ብርጋዴር ጄነራል ኃይለሥላሴ ግርማይ / ወዲዕበይተ/- ዘመቻ ዋና መምሪያ ጡረተኛ

14.ብርጋዴር ጄነራል ሙሉጌታ በርሔ- የአጋዚ ክፍለ ጦአዛዥ የነበረ ጡረተኛ

15.ኮሎኔል ተወልደ ገብረተንሳይ- መከላከያ መረጃ ጡረተኛ

16.ኮሎኔል ገብረእግዚአብሔር ዓለምሰገድ — መከላከያ መረጃ የነበረ ጡረተኛ

17.ኮሎኔል ደጀን ግርማይ- የዕዝ ስምሪት ኃላፊ ጡረተኛ

18.ኮሎኔል የማነ ገብረሚካኤል- የአጋዚ ክፍለ ጦር አዛዥ ጡረተኛ

19ኮሎኔል ገብረዮሀንስ አባተ /ወዲአባተ/- ምዕራብ ዕዝ 43ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ጡረተኛ

20ሻምበል ተወልደ ገብረመድህን /ወዲአድዋ/- ድሬዳዋ ያለ ቀደም ብሎ የወጣ

እነዚህ ግለሰቦች የዘረፉትን ንብረቶች ማስመለስ ይቻል ዘንድ ንብረቶች ያሉበትን ትክክለኛ አድራሻ የምታውቁ ለፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል መከላከል ቢሮ በ011-1-55-12-00 ወይም በ861 ነፃ መስመር አሳውቁ ተብሏል፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር ተቀምጠው የተለያዩ የሚዲያ አውታሮችን በመጠቀም ሀገር በማፍረስ ተግባር ላይ የተሰማሩት፡-

1.ዶክተር እዝቅኤል ገቢሳ

2.ዶክተር አወልአሎ ቃሲም

3.ዶክተር ኢታና ሀብቴ

4.ዶክተር ፀጋዬ አራርሳ

5.አቶ ዳንኤል ብርሃነ

6.አቶ ፍፁም ብርሃነ

7.አቶ አሉላ ሰለሞን

8.ሠናይት መብርሃቱ በሕግ እንደሚፈለጉ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን መግለጫ አሳውቋል፡፡

በሌላ በኩል፣ መከላከያ መቀሌን መቆጣጠሩን ተከትሎ በተለያዩ ከተሞች ከምሽቱ አንስቶ አውራ ጎዳናዎች ላይ በመውጣት ሕዝቡ ደስታውን ሲገልጽ ቆይቷል፡፡ ደስታውን ለመግለጽ አደባባይ ከወጣው የኅብረተሰብ ክፍል በተጨማሪ፣ የተለያዩ የመንግሥት አካላት የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡ የ9ኙ ክልሎች ርዕሰ መስተዳድሮችና የአዲስ አበባና የድሬደዋ አስተዳድር መከላከያ ሠራዊት በተቀዳጀው ድል የተሰማቸውን ደስታ በመግለጽ፣ ለሕዝቡ እንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

በሌላ በኩል፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም በተገኘው ድል የተሰማውን ደስታ ገልጿል፡፡ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ደስ ያላችሁ ከሚለው መልዕክት ባሻገር፣ በቀጣይ የትህነግን አባላት ለፍርድ ለማቅረብ በሚደረገው እርምጃ ከሰራዊቱ ጎን እንደሚቆም የተወካዮች ምክር ቤት ተናግሯል፡፡ ፕሬዝዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴም መከላከያን፣ "አኩርታችሁናል" በማለት የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡ ሕግ የማስከበሩ ምዕራፍ በድል ተጠናቋል ያሉት ፕሬዝዳንቷ፣ በመጪው ጊዜ ደግሞ ትልቅ ሥራ ስለሚጠብቀን ለአፍታ አንዘናጋ ብለዋል፡፡

## እሁድ ሕዳር 20/2013

ቅዳሜ ማምሻውን መቀሌ ተይዛለች መባሉን ተከትሎ ምሽቱን አደባባይ ወጥተው ደስታቸውን ከገለፁት ሌላ፣ እሁድ በጠዋት ጀምሮ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በየጎዳናው በመውጣት ደስታቸውን በተለያየ መንገድ ሲገልጹ አርፍደዋል፡፡ ከአዲስ አበባ በተጨማሪ የወልቃይት፣ የጠገዴና የዳንሻ ከተማ ነዋሪዎች የትህነግ ቡድን መደምሰሱን ተከትሎ አደባባይ ወጥተው ደስታቸውን ገልፀዋል፡፡ ድሉን ለተጎናፀፉት ለመከላከያ ሠራዊት፣ ለአማራ ልዩ ኃይልና ሚሊሻ የድጋፍ ሰልፍ መውጣታቸውም ታውቋል፡፡

በሌላ በኩል፣ የፌደሬሽን ምክር ቤት የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት አስተላልፏል፡፡ ለድሉ ያበቃን ሠራዊት ምሥጋና ይገባዋል ያለው የምክር ቤቱ መግለጫ፣ ጦሩ ለድል እንዲበቃ ላደረገው የሞራልና ሁለንተናዊ ድጋፍ ከጎኑ የሆኑ በሙሉ ከፍተኛ ደርሻ እንዳበረከቱ ገልጿል፡፡ የመከላከያ ሠራዊቱ ጀግንነት፣ ምሳሌነትና ቁርጠኝነት ለሀገራችን መፃኢ ጊዜያትም ትልቅ መሠረት የጣለ ነው ማለቱም ታውቋል፡፡

የትህነግ ቡድን ማርኬያቸዋለሁ ብሎ የውሸት ፕሮፖጋንዳ አውጥቶባቸው የነበሩት ሌተናል ጄነራል ባጫ ደበሌ መግለጫ ሠጥተዋል፡፡ ይኸው አልተማረኩም፣ በእናንተም ልማረክ አልችልም ባሉበት መግለጫቸው፣ "እኛ ከተማረክንም በትህነግ ሳይሆን በኢትዮጵያውያን እና በኢትዮጵያዊነት ነው" ማለታቸው ተሠምቷል፡፡

በመግለጫቸው ሠራዊቱ የጀመረውን ሕግ የማስከበር ዘመቻ አጠናቆ ሕዝቡን በማረጋጋት ወደ ቀየው መመለስ መጀመሩን አሳውቀዋል፡፡ የራያ ግንባር አዛዥ የሆኑት ሌተናል ጀነራል ባጫ ደበሌ፣ ሠራዊቱ ዋና ግዳጁን ቢያጠናቅቅም፣ በተለያዩ ከተሞች በትህነግ ቡድን ሊፈጸሙ የሚችሉ የአጥፍቶ መጥፋት ጥቃቶችን ለመከላከል ሠራዊቱ በተጠንቀቅ ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡ ቅዳሜ በነበረ ውጊያ ማርከነዋል ብለው የውሸት መረጃ ሲነዙ እንደነበር የተናገሩት ሌተናል ጀነራሉ፣ እየፈረጠጠ ያለው ቡድን ምንም ዓይነት የመማረክ አቅም የለውም ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል፣ የመቀሌን መያዝ በማስመልከት የትግራይ ብልጽግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት መግለጫ አውጥቷል፡፡ የትግራይ ሕዝብ በአንድ አጥፊና ከሀዲ ቡድን መገለጽና መወከል እንደማይፈልግ በተግባር አስመስክሯል የሚል ይዘት ያለው መግለጫው፣ ዘመቻው በድል በመጠናቀቁ ታላቅ ደስታ ተሰምቶናል ብሏል፡፡ እንዲሁም በመላ ሕዝባችን አስደናቂ ርብርብ የተገኘ በመሆኑ ድርብ ድል ሆኗል ተብሏል፡፡ የትግራይ ሕዝብ በከፋ አፈናና ጦርነት ውስጥም ሆኖ የነፃነት ቀኑን ሲጠባበቅ ቆይቶ፣ ከመንግሥት ይደርሰው የነበረውን መልዕክትና መመሪያ በአግባቡ በመተባበር አጥፊው ቡድንን ቀድሞ ከልቡ አውጥቶት እንደቆየው አሁን ደግሞ ከጉያው ገፍትሮ በመጣል፣ የትግራይ ሕዝብ በአንድ አጥፊና ከሀዲ ቡድን መገለጽና መወከል እንደማይፈልግ በተግባር ማስመስከሩ ተነግሯል፡፡ ዓለም አቀፍ ሕግጋትን ጥሰው በተከለከሉ ቦታዎች መሽገው የቆት የአጥፊው ቡድን አባላት፣ አንድ በአንድ ተለቅመው ለፍርድ የሚቀርቡበት የመጨረሻ ሥራ በአጭር ጊዜ እንደሚጠናቀቅ አሳውቀዋል፡፡ የቡድኑ ፍፃሜ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች በተለይም ለትግራይ ሕዝብ የትንሳኤና የአዲስ ዘመን ብሥራት ነው ብለዋል፡፡ የአጥፊ ቡድኑ ቅሪት አስተሳሰቦችና ተግባሮችን በቀጣይ የማፅዳት ሥራው ጠተናክሮ መቀጠሉ ወሳኝነት እንደሚኖረው መገንዘብ አስፈላጊ ነው ሲል መግለጫው ያሳስባል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ እዳ ሆኖ የቆየው ዘራፊና ገዳይ ቡድን፣ ራሱ በቆሰቆሰው እሳት ተለብልቦ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ግብአተ መሬቱ መፈፀሙም ተነግሯል፡፡

የትህነግ ቡድንን በተመለከተ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እንደተናገረው፣ ቡድኑ አስቦት የነበረው ሀገር የማፍረስ ሕልም ከሽፏል፡፡ በተገኘው ድል የተሰማውን ደስታ የገለፀው ተቋሙ፣ ከመረጃና ፀጥታ አካላት ጋር በመቀናጀት የትህነግን ድብቅ ሴራ በማጋለጥ ለሕግ ለማቅረብ በሚደረገው ጥረት ኃላፊነቱን ለመወጣት እየሠራ መሆኑን አሳውቋል፡፡ የትህነግ ቡድን በሰሜን ዕዝ የሠራዊቱ አባላትና የፌደራል ፖሊስ አባላት ላይ ጥቃት በመፈፀም፣ እንዲሁም በአማራ ክልል ሕዝቦች ላይ ግልጽ ጦርነት በማወጅ የሀገርን ብሔራዊ ደህንነትና ጥቅም የሚፃረር ከፍተኛ ክህደት መፈፀሙን የተቋሙ መግለጫ አመልክቷል፡፡ አጥፊው ቡድን አቅዶና ተዘጋጅቶ ጥቃት ቢፈፀምም ሕልሙ ከሽፎበታል፣ ያሳካው ነገር ቢኖር ትውልድ ይቅር የማይለው አሳፋሪና አስነዋሪ ታሪክ ማስመዝገብ ብቻ ነው ተብሏል፡፡

## ሰኞ ሕዳር 21/2013

በእለቱ የራያ ግንባር አዛዥ ሌተናል ጄኔራል ባጫ ደበሌ በትህነግ ታጣቂ ቡድን ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ንብረታቸው የተዘረፈና በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ተጎጂዎችን ጎብኝተዋል። ከተጎጂዎቹ በተጨማሪ፣ ቡድኑ ውድመት ባስከተለባቸው አካባቢዎች እያተዘዋወሩ ሕብረተሰቡን ማወያየታቸውም ታውቋል። ሕብረተሰቡ እንዳለው ታጣቂው ቡድን ሲሸሽ ንብረት በማውደምና በመዝረፍ ላይ ተጠምዶ እንደነበር ነው። በታጣቂ ቡድኑ ጉዳት ለደረሰባቸው ነዋሪዎች ድጋፍ ያደረጉት የጦር አዛዥ ቀዳሚው ተግባር ሕብረተሰቡን ማቋቋምና መደገፍ ነው ብለዋል። በተመሳሳይ መልኩ በግዳጅ ወቅት ጉዳት የደረሰባቸውን የመከላከያ፣ የአማራ ልዩ ኃይልና ሚሊሻ አባላትን ሆስፒታል ተገኝተው ጎብኝተዋል። በወልዲያ ሆስፒታል ተገኝተው ወታደሮቹን ከጠየቁ በኋላ የምሥጋናና የማነቃቂያ ንግግር አድርገዋል።

በሌላ በኩል፣ 5ኛው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት 6ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 2ኛ ልዩ ስብሰባውን ሰኞ ዕለት ያደረገ ሲሆን፣ በእለቱም ጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድ ተገኝተው የእንደራሴዎቹን ጥያቄ ተቀብለው ንግግር አድርገዋል። የምክር ቤቱ አባላት ትህነግና ኦነግ ሸኔ በሽብርተኝነት እንዲፈረጁ ጥያቄ አቅርበዋል። ጠ/ሚሩ ለሥልጣን ከበቁበት ጊዜ ጀምሮ ይደርስባቸው ስለነበረ ተጽእኖ በማስረዳት፣ ለውጥ ለማምጣት ከብዷቸው እንደነበር አብራርተዋል። አብዛኛው ሥልጣን በትህነግ ሰዎች በመያዙ ለድህንነታቸው ከመሥጋት ጀምሮ ራሳቸውንም ሆነ ሕዝቡን ከጥፋት ለመጠበቅ ሳይቻላች መቆየታቸውን ተናግረዋል። በየጊዜው ለተፈጠሩት ጥቃቶችና ግጭቶች ታጣቂውን ቡድን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተጠያቂ በማድረግ የጥቅምት 24 ጥቃት እስኪፈፀም ያለውን ሂደት ገልፀዋል። የሕግ ማስከበሩ ተግባር ከጅምሩ አንስቶ መቀሌ እስከተያዘች ድረስ ያለውን ያልተነገረ ታሪክ በዝርዝር በመተንተን ብዙ ያልወጣ የጀግኖች ታሪክ መኖሩን ጠቁመዋል።

በእለቱ ከተዘገቡ ክስተቶች ሌላው፣ በሀገር ክህደት ወንጀል የተጠረጠሩ የጦር መኮንኖች ቤት የተደረገው ፍተሻ ሲሆን፣ በተደረገው ብርበራ በግለሰቦች እጅ መያዝ የሌለባቸው የጦር መሣሪያዎች መያዛቸው ተነግሯል። የፌደራል ፖሊስ እንዳሳወቀው፣ ለረጅም ጊዜ ተቀምጠው የነበሩ ከፍተኛ ጉዳትና ኪሳራ ማድረስ የሚችሉ የጦር መሣሪዎች፣ የጦር ሜዳ ማጉሊያ መነጽሮች፣ ጂፒኤስ፣ በሳተላይት የሚሠሩ ስልኮች፣ ቦንቦች፣ ክላሽንኮቭ፣ ብሬንና የተቀየረው የሠራዊቱ የደንብ ልብስ፣ እንዲሁም በግለሰብ እጅ መያዝ የሌላባቸው ለእኩይ ዓላማ ማስፈፀሚያ የሚውሉ መሣሪያዎች መገኘታቸው ታውቋል። ፍተሻው በአዲስ አበባና ሌሎች ከተሞች የተከናወነ ሲሆን፣ ትህነግና ኦነግ ሸኔ ሊጠቀሙባቸው የነበሩና ባይያዙ ኑሮ ከፍተኛ ቀውስ ያስከትሉ ነበር ተብሏል።

በሌላ በኩል፣ ለሠራዊቱ ድል የተቀናጀ የሎጂስቲክ አገልግሎት መቅረቡ የላቀ ሚና እንደነበረው የኅብረት ሎጂስቲክስ ዋና መምሪያ ኃላፊ ሜጀር ጄኔራል አብዱራህማን እስማኤል ተናግረዋል። የተቀናጀና ውጤታማ የውጊያ ድጋፍ አገልግሎት መደረጉ ለድሉ ከፍተኛ አስተዋፆኦ አድርጓል ያሉት ኃላፊው፣ ከተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች ሠራዊቱን አሰባስቦ ለማሰማራትና አስፈላጊውን የውጊያ ቁሳቁስ በተገቢው ሁኔታ ማቅረብ በመቻሉ ድሉ በአፋጣኝ እንዲገኝ አስችሏል ማለታቸው ተሠምቷል። ከሕብረተሰቡ ለሠራዊቱ የተደረገው ድጋፍም ከፍተኛ አቅም እንደፈጠረም ተናግረዋል።

## ማክሰኞ ሕዳር 22/2013

በሰሜን ኢትዮጵያ እየተወሰደ ካለው ወታደራዊ እርምጃ ጋር በተያያዘ ግንኙነት ያለው ኢትዮጵያዊ ሱዳን ውስጥ መያዙ ተሰምቷል። የተያዘው ግለሰብ የትግራይ ሚሊሻ መሪ የነበረና ከፍተኛ ሀብት ይዞ ከነቤተሰቡ ሱዳን ግዛት ውስጥ ሲንቀሳቀስ በሱዳን ወታደሮች ተይዟል። ይኸ ግለሰብ ከትህነግ ወገን ሆኖ ሀገሩን ሲወጋ የነበረ ሲሆን፣ በገዳሪፍ ግዛት ውስጥ አብረውትም በርካታ ወታደር አጃቢዎቹ እንደነበሩም ተነግሯል። ግለሰቡ 5 ቢሊዮን ፓውንድ፣ መጠኑ ያልተጠቀሰ ብዛት ያለው ወርቅና 2 የቅንጦት መኪኖች ጋር ተይዟል።

በሌላ በኩል፣ በመተከል የሚገኙ የትህነግ ርዝራዦች እጅ እንዲሰጡ ማሳሰቢያ ተሰጥቷቸዋል። የቤኒሻንጉል ክልል ርዕሰ መስተዳድር በመተከል ዞን የትህነግን ጥፋት እያስፈፀሙ ያሉ ርዝራዦች ከጥፋታች በመታቀብ በአጭር ቀናት ውስጥ እጃቸውን ለዞኑ ኮማንድ ፖስት እንዲሰጡ አሳስበዋል። በመከላከያ እርምጃ ህልውናው ያከተመው የትህነግ ተልእኮ አስፈፃሚዎች ለዓመታት በክልሉ ባደረጉት ጥፋት ብዛት ያላቸው ንፁሐን ሰዎች እንዲሞቱ፣ እንዲሰደዱና ንብረታቸው እንዲወድም ማድረጋቸውን ርዕሰ መስተዳድሩ አሳውቀዋል። የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ የፀጥታ ኃይሎች ከአጎራባች አማራ ክልልና ፌደራል መንግሥት ጋር በመቀናጀት በርካታ የጥፋት ቡድኑ ተላላኪዎችን መደምሰሳቸውን አሳውቀዋል። እርምጃው እየተወሰደ ቢሆንም፣ ጥፋቱ ግን እንዳልቆመ አቶ አሻድሊ አሳውቀዋል። በየቦታው የቀሩት የጥፋት ቡድኑ አባላት እጅቸውን እንዲሰጡ በቀረበላቸው ጥሪ ተጠቃሚ ይሆናሉ የተባለ ሲሆን፣ ይኽ ካልሆነ ግን እንደ ትህነግ ለአንድ ጊዜና ለመጨረሻ ጊዜ የመደምሰስ እጣ ፋንታ ይገጥማቸዋል ማለታቸው ተሠምቷል።

በእለቱ ከተዘገቡ ክስተቶች ሌላው፣ ሁመራ ስለተገኘው 37 ኩንታል አዳንዛዥ ዕፅ ነው። በከተማው አንድ ሆቴል በተደረገ ድንገተኛ ፍተሻ 37 ኩንታል አደንዛዥ እፅ ተገኝቷል። ብዛት ያለው አደንዛዥ እፅ በከተማው ሲገኝ ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑም ተነግሯል። ከዚህ በተጨማሪ፣ በአንድ ሰው ሥም የተመዘገቡ 11 የቤት ካርታዎች እና ግለሰቡ ከፍተኛ ገንዘብ ያዘዋወረበት ቼክ ተገኝቷል። በርካታ ገጀራዎች፣ መጥረቢያዎችና ሌሎች መሣሪያዎች ከተማዋን እየጠበቀ በሚገኘው የአማራ ልዩ ኃይልና በአማራ ክልል ፖሊስ መገኘቱ ታውቋል።

በሌላ በኩል፣ የሽሬ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር አመራሮች ከእንግዲህ በኃላ በትህነግ ቡድን የነበረው የዝምድና አሠራር አይኖርም ብለዋል። በፊት የነበረው የዝምድና ኔትወርክ ቀርቶ ህዝብን በቅንነት ለማገልገል እንደሚሰሩ አመራሮቹ ተናገረዋል። የጊዜያዊ አስተዳደሩ ከንቲባ ሆነው የተመረጡት መምህር ሐጎስ በርሄ ሲሆኑ፣ ምክትል ከንቲባ የሆኑት ኢንጂነር ጀማል ሙሐመድ፣ የከተማው የአቅም ግንባታ ጽ/ቤት ኃላፊ ሆነው የተመረጡት መምህር ንግስቲ ፋንታሁን መሆናቸው ተሠምቷል። የክልል ጊዜያዊ ዋና ስራ አስፈፃሚ ሆነው የተሾሙት ዶክተር ሙሉ ነጋ በተለያዩ አካባቢዎች እየተንቀሳቀሱ ህዝቡን ማወያየታቸው ተዘግቧል። የሽሬውም ስብሰባ የመሩት እሳቸው ናቸው።

ሕዳር 22 ከተከናወኑ ተግባሮች ሌላው የሚዲያ ባለሙያዎችን የተመለከተ ነው። በምዕራብ ግንባር በአካል ተገኝተው ስለ ዘመቻው ሲዘግቡ የነበሩና የተሰጣቸውን ሀገራዊ ተልእኮ የተወጡ የሚዲያ ባለሙያዎች ዕውቅና የተሰጠበት የምስጋና መርሃ ግብ ተካሄዷል። በምዕራብ ግንባር ከዳንሻ፣ ሁመራ፣ ሽራሮ፣ በሽሬ አድርጎ እስከ አድዋና አክሱም የዘለቀ ስምሪት ለነበራቸው ባለሙያዎች ዕውቅና የተሰጠው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመረጃ ፍሰት ቃል አቀባይ አምባሳደር ሬድዋል ሁሴን በተገኙበት ነው። በመርሃ ግብሩ ላይ ጥሪ የተደረገላቸው የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች የሠራዊቱ ተወካዮችና የተለያዩ ሚዲያ ተወካዮች ተገኝተው ነበር።

የእለቱ መነጋገሪያ የነበረው የቀድሞ የፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የነበሩት የወ/ሮ ኬሪያ ኢብራሂም እጅ መስጠት ነው። ያለመከሰስ መብታቸው ተነስቶ የእስር ማዘዣ ወጥቶባቸው ከነበሩ የትህነግ አመራሮች መካከል አንዷ የሆኑት ወ/ሮ ኬሪያ ኢብራሂም እጃቸውን ለመንግስት መስጠታቸው ታውቋል። የትህነግ ጥቅም ይሻለኛል ብለው ወደ መቀሌ ሸሽተው የነበሩት የእኚህ የቀድሞ ባለስልጣን ሹፌር የመንግስት ንብረት ትቼ አልመለስም ብሎ የሄዱበትን መኪና ይዞ መመለሱ ይታወሳል።

በሌላ በኩል፣ ወቅታዊ የኢትዮጵያ ሁኔታን በተመለከተ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ ደመቀ መኮንን ከተመድ የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ ጋር ተወያይተዋል። የኢትዮጵያ መንግስት በትህነግ ላይ እየወሰደ ያለውን እርምጃ ለማብራራት ባለስልጣናቱ መገናኘታቸው ታውቋል። ንፁሀን ዜጎችን በተመለከተ፣ ስደተኞችን በመመለስ በኩል ስለሚወስድ ጥንቃቄ፣ እንዲሁም ወደፊት ሠላማዊ ኑሮ እንዲመለስ ሊደረግ ስለታቀደ ሁኔታ መወያየታቸው ተነግሯል።


## እሮብ ሕዳር 23/2013

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢትዮጵያ ልዑክ በኒውዮርክና አካባቢው ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ማህበረሰቦች ስለወቅታዊ ሁኔታ ገለፃ አድርገዋል። መንግስት በትግራይ ክልል ስለወሠደው ህግን የማስከበር ዘመቻ ለኒውዮርክ፣ ኒውጀርሲና ኬኔቲኬት አካባቢ ነዋሪዎች ማብራሪያ ተሠጥቷል። የትህነግ ቡድን በመንግስትና በህዝብ ላይ ስለፈፀመው ዘግናኝና አሳፋሪ ወንጀል በመተንተን፣ መንግስት ህግን ለማስከበር እንደተገደደ ገለፃ ተሰጥቷል። በገለፃው ወቅት ተሳታፊ የነበሩት ኢትዮጵያውያን፣ በዘመቻው ምክንያት የተፈናቀሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን መልሶ ለማቋቋምና ቤተሰቦቻቸውን ላጡ ድጋፍ ለማድረግ ቃል መግባታቸው ተነግሯል።

በሌላ በኩል፣ በእለቱ የዳንሻ ከተማ ነዋሪዎች ህዝባዊ የድጋፍ ሠልፍ አካሂድዋል። ባለፈው ሳምንት በራያ የተደረገውና ወደ ትግራይ መመለስ አንፈልግም የሚል ይዘት የነበረውን አይነት ተመሣሣይ ሠልፍ መካሄዱ ተነግሯል። የትህነግ ቡድን የተወገዘበት መልእክት ያለው በርካታ መፈክር ተይዞ የተወጣ ሲሆን፣ በመንግስት በተወሰደው እርምጃ ደስተኛ መሆናቸውን የሚገልጹ የድጋፍ መልእክቶችም ነበሩ። ትህነግን ላባረሩት መከላከያና አማራ ልዩ ኃይል እንዲሁም ሚሊሻ ምስጋና ማቅረባቸውም ታውቋል። በአካባቢው ያሉ የትህነግ አባላት ትጥቃቸውን እንዲፈቱና የማይካድራ ነዋሪዎችን ጨፍጭፈው ወደ ሱዳን የሸሹትም ተይዘው ለፍርድ እንዲቀርቡ ጥያቄ ቀርቧል።

በአዲስ አበባ ቦንብ ፈንድቶ ምንም ጉዳት አለማድረሱን ተነግሯል። ቦሌ ክፍለ ከተማ የጎርጎርዮስ አደባባይ በሚል በሚታወቀው አካባቢ በሚገኝ ቆሻሻ መጣያ ገንዳ ውስጥ ተጥሎ የተገኘው ቦምብ፣ በአካባቢው ህብረተሰብ ጥቆማ ለፖሊስ ተላልፎ ነበር። የፈንጂ አምካኝ ባለሙያዎች በማለዳ ወደ ቦታው በማቅናት ሊያመክኑት ሲሞክሩ ባልታወቀ ምክንያት መፈንዳቱን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን አሳውቋል። በፍንዳታው ፍንጣሪ አንድ ግለሰብ ቆስሎ ህክምና ተደርጎለት ወደ ቤቱ መመለሱ ተነግሯል። በተመሳሳይ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 6 ጉርድ ሾላ ቅዱስ ያሬድ ሆስፒታል አካባቢ ቦንብ ተገኝቶ ፖሊስ ተጠርቶ እንዲመክን መደረጉ ተገልጿል።

በሌላ በኩል፣ በእለቱ በትግራይ ክልል የተከፈቱና እንዳይንቀሳቀሱ ተብለው የነበሩ የባንክ ሒሳቦች ላይ የተጣለው እገዳ በከፊል መነሳቱ ተነግሯል። ትግራይ ክልል ባንክ ሂሳብ የከፈቱና ከትግራይ ውጭ ያሉ ደንበኞች በያሉበት ሂሳባቸውን ማንቀሳቀስ እንዲችሉ ብሄራዊ ባንክ ተነግሯል። በጠቅላይ አቃቤ ህግ በወንጀል ተጠርጥረው ሂሳባቸው እንዳይንቀሳቀስ ከታገደባቸው ውጭ ሌሎች እንዲያንቀሳቅሱ ተፈቅዷል። በትግራይ ክልል የፀጥታ ሁኔታው አመቺ በሆነባቸው ከተሞች ባንኮች ተከፍተው ስራ እንዲጀምሩ እየተሠራ ነው ያለው ባንኩ፣ በሌሎቹ ግን ፀጥታውና ኔትወርኩ እስኪሻሻል ተዘግተው እንዲቆዩ መወሰኑን አሳውቋል።



ሻምበል አስማማው አዳሙ

# ከጄነራሎቹ በሥተጀርባ

## ክፍል ፩

ከቀድሞ ሠራዊት ጄነራሎች መካከል ጥቂቶቹ የብዙኃኑን ዝምታ፣ እንደ አላዋቂነት በመቁጠር፣ ወይም ከኛ ሌላ የታሪክ እማኝ ስለሌለ፣ ነቃሽ የለብንም በሚል ይመስላል በቴሌቪዥን መስኮት ብዙ የተዛቡ ታሪኮችን ሲናገሩ ይደመጣል፡፡ በቅርቡ ደግሞ በእነሱ መልክ የቀረጿቸው ተከታዮቻቸውም በዚያው ቅኝት ውስጥ ገብተው ሲጓዙ ይስተዋላሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ ባልደረቦቻችን፣ እኔ ማን ነኝ? ብለው እራሳቸውን በመጠየቅ ለወደፊቱ በጥንቃቄ እንዲራመዱ ለማሳሰብና በተጨማሪም በእነሱ የተዛባ መረጃ የተሞሉ አድማጭና ተመልካቾችም እውነታውን ይረዱ ዘንድ የምናውቀዉን በጥቂቱ ለማጋራት ይህን መልእክት አስተላልፈናል፡፡

ጉዳዩም እንዲህ ነው በካራማራ 41ኛ ዓመት የመታሰቢያ ዝግጅት ላይ ያልተደረገውን ተደረገ ብለው ክቡር ሜ/ጄነራል መርዳሳ ሌሊሳ ጋዜጠኞችን በማሳሳት ለንባብ ያበቁትን ኃሰተኛ ሪፖርት አስመልክቶ፣ ሁለት ሻለቆች ትችት ሰንዝረውባቸው ማንበባችን ይታወሳል፡፡ በዚያው ሰሞንምአምዱንካነበብነውከተመለከትነውወገኖች መካከል ጥቂቶቻችን፣ እንዴት እርስ በእርሳችን በመተቻቸት ገበናችንን ወደውጭ እናወጣለን? በሚል ቅሬታ ስለተሰማን፣ ትችት አቅራቢዎቹን አንድ ዓመት ሙሉ በነገር ስናልመዘምዛቸው ሰንብተናል፡፡



ይሁን እንጂ ከእለታት አንድ ቀን ከስታዲዮም መልስ በአንድ ሻይ ቤት ተሰብስበን የባጥ የቆጡን ስናወጋ፣ እንደ አጋጣሚ ሜ/ጄነራል መርዳሳን በቴሌቪዥን መስኮት አየናቸው፡፡ ከመካከላችን አንዱ እሳቸውን እያሞጋገሰ፣ ያንኑ የጠነዛ አጀንዳ አንስቶ በፈረደባቸው ሻለቆች ላይ የማጣጣል ወሬውን ሲጀምር፣ አንዱ ጓ ደኛችን ካፉ ነጥቆ፣ "ወንድሞቼ ሻለቆቹኮ ምንም ጥፋት የለባቸውም፡፡ ለምን አለቆቻችን ተተቹ ብሎ የሚቆጭ ካለ አዝናለሁ፡፡ ከዚያ በተረፈ ግን በይሉኝታ ሀቁን ማዳፈኑ አግባብ ሆኖ ስላልታያቸው አድርገውታል፡፡ እናም ትክክል ነበሩ፡፡"...



"በመሠረቱ ሜ/ጄ መርዳሳና ተከታዮቻቸውኮ የብዙኃኑን ሠራዊት ማንነት እያዳፈኑ የራሳቸውን ታዋቂነት ብቻ ሲያንጸባርቁ እያየናቸው አይደለም እንዴ? ዛሬም ድርጊታቸው ትክክል ያለመሆኑን የተረዱ ተቆርቋሪ ወገኖች ብቅ ብለው፣ እረፉ ውሸት አትናገሩ፣ ዛሬ የሀገሪቱ የፌደራል ሠራዊት እንደሚፋለመው ሁሉ፣ እኛምኮ ከወያኔና ሻዕቢያ ጋር ነበር ለሀገር ሉአላዊነትና አንድነት ስንታገል የነበርነው፡፡ ነገር ግን ወያኔም እኛን ለመከፋፈል በነበረው ዓላማ ብቻ፣ ለእናንተ ጡረታና ሕክምና በመፍቀዱ መብታችሁ ቢጠበቅም፣ መላ የሠራዊቱ አባላት ግን ያለጡረታና የሕክምና መብት መበተኑን ታውቃላችሁ፡፡ ይሁን እንጂ እናንተ ከመንግስት ጎን ለመለጠፍ ዲስኩር ከመደስኮር ባለፈ ለዚያ መብቱን ተገፎ ሜዳ ላይ ለቀረው ወገናችሁ አንድ ቃል እንኳ በሚዲያ ተናግራችሁ ታውቃላችሁ? በማለት ስሕተታቸውን ሊነግሯቸው በተገባ ነበር፡፡ ያ ባለመሆኑ ግን ይሄው ዛሬም ድረስ ያለሀፍረት የተለመደ ዲስኩራቸውን እያደመጥን እንገኛለን፡፡ ደሞምኮ ‹ክቡር ጄነራል መርዳሳ ሌሊሳ፣ ራስዎን ያስተካክሉ፣ ከጎንዎ የምታሰልፉትን ሰውም በጥንቃቄ ይምረጡ› በሚል ምክር አዘል የጨዋነት ትችት ሃሳባቸውን ገለጹ እንጂ፣ የእሳቸውን ክብር የሚነካና የሚዘልፍ ቃል አንድም ቦታ ላይ አልሰነዘሩም፡፡ ታዲያ ይሄ ምኑ ከፍቶ ነው የምንቆጭባቸው?" ሲል ሁላችንንም ጸጥ አደረገን፡፡

ከሴኮንዶች ዝምታ በኋላ ሌላው ባልደረባችን፣ የተናገረው ትክክል መሆኑን በመደገፍ፣ "ካነጋገርሕ በጄነራሉ ላይ እንደተበሳጨሕባቸው ያስታውቃል፡፡ እስኪ ቀደም ሲል ከቀረበባቸው ትችት በተጨማሪ ባንተ በኩል ሊያስወቅሳቸው ይችላል የምትለው መረጃ ካለህ ብታካፍለን?" ብሎ ሲጠይቀው፣ "ስሙኝ ወንድሞቼ፣ በሥራ ላይ በቆየንባቸው ዓመታት ስለእያንዳንዳቸው የምናውቀውን እናንሳ ብንል፣ ሁላችሁም ታውቃላችሁ በጣም ደስ የማይሉ ብዙ ነገሮችን መናገር እንችላለን፡፡ እያንዳንዱ ተራራና የግዳጅ ምእራፍ ለሹመትና ለሽልማት ተከፋፍሎ የተቀመጠ ነበር፡፡ እናም ያንን ትተን ዛሬ በወያኔ ኢሕአዴግ ዘመን እራሳቸው ካሳተሙት መጽሐፍና በራሳቸው አንደበት ከተናገሯቸው የተሳሳቱ ሁለትና ሦስት ነጥቦች በመነሳት ግን ጥቂት ማለት እችላለሁ"

"ለምሳሌ ሜ/ጄነራ መርዳሳ ሌሊሳ በመጽሐፋቸው እንደገለጹት፣ ብዙ ጊዜ በጦር ሜዳ ላይ እጃቸውን እንደሚቆስሉ ነው የጻፉት፡፡ ለምን ይሆን? የምሥራቁን ጦር ግንባር እንተወውና በተለይ አምቦ ላይ የታንክ ቱሬት እንዳቆሰላቸውና ፌንት ሆነው እንደወደቁ ግዮን ሆቴል በስብሰባ ላይ ሲናገሩ ሰምቻቸዋለሁ፡፡ ብዙ ዝርዝር ውስጥ መግባት ባያስፈልግም፣ እንደ ወታደራዊ ባለሙያ ግን እንዴት ቱሬት ውስጥ ሊገቡ ወይም ሊጠጉ እንደቻሉ ግምት ውሰዱ፡፡"

"በሌላ በኩልም በ1970 ዓ.ም መግቢያ ላይ ቆስለው ለሕክምና እንደተላኩ በመጽሐፋቸው ገልጸዋል፡፡ ያ ማለት ደግሞ ካራማራ ሲያዝ በቦታው አልነበሩም ማለት ነው፡፡ ታዲያ እሳቸው በቦታው ካልነበሩ፣ በኢሳት ቴሌቪዥን ስለካራማራ መያዝ ያን ያህል ሰፊ ትረካ በድፍረት ያቀረቡት ከምን ተነስተው ነበር?"

እዚህ ላይ እናንተንም ሆነ ሌሎችን ላስገነዝብ የምፈልገው አንድ ዓብይ ነጥብ አለኝ፡፡ ያም ካራማራ በሶማሊያ የማጥቃት ወረራ በተኩስ አልተያዘችም፡፡ በእኛም የመልሶ ማጥቃትና ሀገርን ነጻ የማውጣት እርምጃ እንዲሁ በተኩስ አልተለቀቀችም፡፡ እርግጥ ነው ሶማሊያ አካባቢውን በቁጥጥር ሥር ከማዋሏ በፊት ከመቶ በላይ የሚሆኑ የመድፍ አረሮችን ካራማራ ላይ በማዝነብ በአንድ የመድፍ ሼል ተሳካላትና ራዳሩን ማውደም ቻለች፡፡ ከዚያ በኋላ ካራማራ ተያዘች አልተያዘች ምንም የምትፈይደው ነገር አልነበረም፡፡ በዚህ ረገድ ስሕተት ነው ብሎ የሚሞግት ካለ ከኔ ጋር ብቻ ሳይሆን ከመቶዎች በላይ የሚሆኑ የአይን እማኞች ጋር በቴሌቪዥን መስኮት ፊት ለፊት ቀርቦ ሊሞግት ይችላል፡፡ እሳቸው ግን መጽሐፋቸውን እንዳየሁት ታሪክን በአግባቡ የመግለጽ ችግር ስላለባቸው ለሙግት የሚመጡ አይመስለኝም፡፡"

"ካልሰለቻችሁኝ ሌሎችም አሉ፡፡ ለምሳሌ ከመንግስት የቴሌቪዥን መስኮቶች የማይጠፉት ብ/ጄነራል ካሳዬ ጨመዳንም እስኪ ተመልከቱ፡፡ ታማኝ በየነ ለሠራዊቱ ካለው ፍቅር የተነሳ በአንድ ▶

ወቅት “መ/አ ካሳዬ ጨመዳ ተኩስ አለ ካራማራ ተያዘ” ብሎ በኢሳት ቴሌቪዥን ተናገረ፡፡ ከዚያ ወዲህ ብ/ጄነራል ካሳዬም በሚዲያዎቹ ሁሉ ተጋባዥ ሆኑ፡፡ ይህን ስል ጄነራሉን ለማጣጣል ፈልጌ አይደለም፡፡ ሀቁ ግን በሶማሊያ ወራሪ ጦር ላይ የመልሶ ማጥቃቱ ዘመቻ ሳይጀመር፣ እሳቸው በ1969 ዓ.ም መጨረሻ ወደ ሰሜን እዝ ተዛውረው ነበር፡፡ ምናልባትም በስልታዊ አፈግፋጊነታቸው ስማቸው የሚጠራ ከሆነ ያ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሲጠራ በማጥቃቱ ላይ ግን እንዳልተሳተፉ እርግጠኛ ነኝ፡፡ እኔ ምሥራቅ እዝ ስለነበርኩ ይሄንን አውቃለሁ፡፡ በተጨማሪም ብ/ጄነራል ጥላሁን ክፍሌ በታንክ ብርጌድ መምሪያ ውስጥ ስለነበሩና ብ/ጄ ካሳዬ ጨመዳም በዚያው ብርጌድ ውስጥ የታንክ መቶ መሪ ሆነው የሶማሊያን ማጥቃት በመከላከሉ ላይ አብረው የተሰለፉ በመሆናቸው፣ እሳቸው ስለጉዳዩ በተሻለ ዝርዝሩን ሊናገሩ ይችላሉ፡፡ ታዲያ እውነታው ይሄ ሆኖ ሳለ “የመ/አለቃ ካሳዬ ጨመዳ ተኩስ አለ ካራማራም ተያዘ” የሚለውን ሐረግ በአየር ላይ ለማዋል፣ መጀመሪያውኑ መረጃው ከየት አፈትልኮ ወጣ?

ይሄም ብቻ አይደለም፡፡ ወያኔዎች በቤተ መንግስት ውስጥ በነበሩበት ጊዜ፣ “ግንቦት 20 በእግዚአብሔር ኃይል የተገኘ ድል ነው ቢሉ ይሻላቸዋል” ሲሉ ለሎሚ መጽሔት የሰጡትን ቃል ላስታውሳችሁ እወዳለሁ፡፡ ዛሬ ደግሞ በቴሌቪዥን መስኮት ቃለ መጠይቅ ሲደረግላቸው የመጀመሪያው ተቃዋሚና ጸረ ወያኔ ሆነው እያየናቸው ነው፡፡ ሁኔታው እሰይ፣ ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም፣ ያን አፋቸውን ሞልተው ግንቦት 20ን ከእግዚአብሔር የተገኘ ድል ነው ቢሉነው ቢሉ ይሻላቸዋል ያሉትን፣ ዛሬስ ምን ሊሉት ይሆን? ከእግዚአብሔር የተገኘ ውድቀት? ለሁሉም ጄነራሉ ጋ ሁኔታ ማረጋገጥ ብሎ ነገር የለም፡፡ ንግግራቸው ሁሉ እንደወረደ ነው፡ ፡ ይቻላል፡፡”…

“ለመጨረሻ አንድ ነጥብ ብቻ ልመርቅላችሁና ይበቃኛል፡፡ ያም ሜ/ጄ መርዳሳ ሌሊሳ የክፍለጦር አዛዥ፣ ብ/ጄነራል ካሳዬ ጨመዳ ደግሞ የሳቸው ዘመቻ መኮንን ሆነው የአፋቤትን ኦፐሬሽን እንዲመሩ ኃላፊነት ተጥሎባቸው ነበር፡፡ ብዙ ዝርዝር ውስጥ ሳልገባ በግርድፉ ብቻ የግዳጁን ውጤት ኳድ ሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለ ማሪያም በጉጉት ይጠባበቁት እንደነበር ብቻ እያሰባችሁ መጨረሻውን ጠብቁ፡ ፡ ይሄውም ጦሩ በዝግጅት ላይ ሆኖ ግዳጁን እንዲጠባበቅ ተነግሮ ሳለ፣ በከፍተኛ አመራሮች ቀጥል የሚል መመሪያ ሳይሰጥ፣ ሜ/ጄነራል መርዳሳ በራሳቸው ውሳኔ ሠራዊታቸውን ወደ ማጥቃት እንዲገባ ለነብ/ጄነራል ዋሲሁንና ለሌሎቹ ብርጌድ አዛዦችም ትእዛዝ  ያስተላልፋሉ፡፡ ይሁን እንጂ ውጤቱ በጉጉት ሲጠበቅለት የነበረው ማጥቃት፣ 40 ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ “ተከበናልና ድረሱልን” በሚል ጥያቄ ተቋጨና አረፈው፡፡ ይሄን በሚሰሙበት ሰዓት የጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ ስሜት ምን እንደሚሆን ገምቱ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የዘመቻው ውጤት ያስከተለው ዳፋ ደግሞ በጣም አሳዛኝ ነበር፡፡ ይሄውም በግዳጁ ላይ የነበሩት እንደሚናገሩት፣ በሰዓቱ የነበረው ማፈግፈግ ስልታዊ ስላልነበር፣ በየአሸዋ ውስጥ ተቀርቅሮ የቀረው ታንክ፣ ብረት ለበስና ድጋፍ ሰጪ መሳሪያ በሙሉ፣ ለሻዕቢያ ጦር ወደ ሜካናይዝድነት መሸጋገር ምክንያት ሆኖ  ነበር፡፡ እናም ሻዕቢያ ፊቷን ወደ ምሥራቅ በማዞር በቀላሉ መሰናክሎቿን እያጸዳች እስከ ምጽዋ ድረስ ማጥቃትና ብሎም ለዛሬው መበተናችን ምክንያት መሆን ቻለ፡፡ እዚህ ላይ እንግዲህ አንድ ነገር ልብ በሉ፡፡ ያም ጄነራል ካሳዬ ጨመዳ ማንን ለመውቀስ እንደፈለጉ ግልጽ ባይሆንም፣ በኢትዮጵያ ሆቴል ውስጥ ታማኝ በተገኘበት ስብሰባ ላይ “አለቆቻችን ተሞዳሙደው እንድንሸነፍ አስደረጉን እንጂ እኛ አልተሸነፍንም” በማለት እየጮሁ ሲናገሩ ተደምጠዋል፡ ፡ ታዲያ በሰዓቱ እውን እሳቸውስ አንዱ አለቃችን አልነበሩምን? ከተሞዳሞዱት መካከል አንዱ እኔ ነበርኩ ማለታቸው ካልሆነ በስተቀር፣ የሚያውቁት የተለየ መረጃ ካለ ለምን ይሄነው አላሉም? ወንድሞቼ ብዙ ማለት ቢቻልም እድሉን ልስጣችሁና ያላችሁን ጨምሩበት፡፡”

ሲል ንግግሩን ቋጨ፡፡ ሁላችንም መጨረሻውን በጉጉት ስንጠባበቅ ነበርና ባልተደማመጠ አነጋገር “ጄነራሎቹን ምን ነካቸው?” “ያሰኛል! እውነትም ምን ነካቸው? “ምንነካቸው?” በመባባል አንዱ ከሌላው ጋር እርስ በእርሳችን በመተያየት ተጉመተመትን፡፡ በመጨረሻም ሌላው ጓዳችን የነበረውን ጉርምርምታ ሰብሮ “ትሰሙኛላችሁ? ከጄነራሎቹ በስተጀርባ አንድ የተደበቀ ነገር አለ፡፡ እሱም ዛሬ ላይ ካላጠፉት በስተቀር ቀስ ብለን የምንደርስበት ይሆናል፡፡ ከአንድ ዓመት በፊት አንድ ባልደረባችን የጄነራሎቹንና ተከታይ ጓደኞቻቸውን ድረ ገጽ ከፍቶ ያጋጠመውን አስገራሚ መረጃ አሳይቶኝ ነበር፡፡ እሱን ሌላ ጊዜ እነግራችኋለሁ፡፡ ለዛሬ ግን እስካሁን ከተነገረው የባሰ በቅርብ ጊዜ የፈጸሙት አንድ ድራማ ስላለ ሰዓቱ ሄደ እንጂ ብነግራችሁ እንዴት ደስ ባለኝ ነበር፡፡ ይሄውም ከወራት በፊት “ከኢትዮ ኢንተር ናሽናል ጄነራል መኮንኖች… እድር” በሚል ስያሜ በማሕተም የተደገፈ ደብዳቤ በሜ/ጄነራል መርዳሳ ሌሊሳ ፊርማ ተበትኖ አይቻለሁ፡፡ እናም ምን ይመስላችኋል? ልቀጥል?” ሲል ስለደብዳቤው ሊተርክልን ጥያቄ አቀረበ፡፡ ይሁን እንጂ አነጋገሩ ጉዳዩን ለመስማት ልባችንን ቢያንጠለጥለውም፣ እየመሸ በመሄዱ በሁላችንም ገጽታ ላይ የመቸኮል አዝማሚያ ይታይብን ነበር፡፡ እናም በቁም ነገር ለሳምንት ማንም ሰው እንዳይቀር ቀጠሮ ይዘን መለያየቱ ግድ ሆነና ተሰነባበትን፡፡

የባልደረባችንን መረጃ ካዳመጥን በኋላ በክፍል ሁለት ዝግጅታችን “የጄነራሎቹን ደብዳቤ” ይዘን እንቀርባለን፡፡ ቸር ያገናኘን፡፡

# የጭንቋ ቀን ደራሽ

ምነው በመስከረም በአበባው ወራት
ያንን ሁሉ በጋ ያን ሁሉ ክረምት
አብረን ተሻግረነው ወደ አዲስ ዓመት
እጅግ አሳዘነን የእርሶ መለየት፡፡

ይመጣል ይሄዳል ተፈጥሮ ህጓ ነው
የመስፍኖች መስፍን ተለዩን ምንድነው?
የሠራም ላገሩ ያልሠራም ዳተኛው
ያችቀን አትቀርም ሞትን አይቀይረው፡፡
በቀኝም በግራ የሚሟገቱላት
ፊት ለፊት ተጋፍጠው የሚሰለፉላት
ኢትዮጵያ አባት አጣች እስቲ አስተዛዝኗት
ራሷም ይታበት ወገቧም ይደግለል ለሀዘኗ ፅናት፡፡

ምን ይሆን ብልሃቱ ምሁር አልቆይ አለን
እንደነገሩማ ዘጠና ሞልተዋል አምላክም ይመስገን
በማስተዋል ጠልቆ በእውቀት መምከርን
አስተምረውናል ለባለውለታችን ባለእዳዎች ነን፡፡
ያሁሉ ጋዜጣ ያሁሉ መፅሔት
ከወይን በስተቀር የለም ያልፃፉበት
ከመፅሐፍቶቻቸው እነ አገቱኒ እነ አረምኩሽም አዳፍኔና የከደት ቁልቁለት
ምሁር ሁለት ነው አንደኛው የጓዳ አንደኛው ያደባባይ ሙብራት፡፡

በሚሆነው ሁሉ አያውቁም መሸሽ
በእውቀት ተጋፋጩ የጭንቋ ቀን ደራሽ፡፡
አገር ስትጨነቅ መላው ሲጠፋባት
ማን ነበር የሰማ ማንስ ደረሰላት
ፐ/ር መስፍን የኢትዮጵያ አባት፡፡

አያጎበድዱም ፊት ለፊት ተጋፋጭ
የብእሩ አንበሣ የእውነት እውነት ገላጭ
ለሌሎች እያበሩ እንደ ሻማ ቀላጭ
ታሪክ ምሥክር ነው ጊዜ ሁሉን ገላጭ፡፡

በእስር ቤቱ ዘመን አልቀምስም አልበላም እያሉ
የማይቻለውን ሁሉንም የቻሉ
መስፍን ወ/ማርያም ከእንግዲህ የትአሉ? የትአሉ?
ኢትዮጵያ አባት አጣች ሕዝቧም ልሣኑን
ከእንግዲህ መድረኩ ይዘጋ ቢፈልግ ክፍት ይሁን
ማንደፍሮ ሊናገር ማን ተሟጋች ሊሆን
ተተኪ ለማግኘት ሃምሳ አመት ቢፈጅም እንዲሁ ክፍት ይሁን፡፡
ልጠይቅ ለአገሩ ልናገር ለሕዝቤ ብለው የተነሱ
ለዓይን የሞሉ ለልቡ የደረሱ
ለሰብአዊ መብቶች ማልደው የተነሱ
ፐ/ር መስፍን መቼም አይረሱ፡፡

በብዕር ሮጠዋል ሳይለብሱ ማሊያ
ተሻግረው አጥንተዋል እስከ ሶማሊያ
ይኸው ምሥክሩ ጆግራፊቱ ኢትዮ-ሶማሊያ፡፡
ይሠራ ሐውልታቸው በአደባባዮችሽ
አገሬ እንዳትባይ ውለታ በላሽ
ለሠሩትም ምን ሠራች በመባል እንዳትወቀሽ
ታሪክሽን እንዲወርስ መጪው ትውልድሽ፡፡

ሚዛን ባዶ ሆኖ ፍትህን ፍለጋ በየፍርድ ቤቱ
በህገ አራዊት እንዲያ ሲገላቱ
ባለመልካም ተግባር ግዙፍ ስብዕና
መስፍን ወ/ማርያም ኢትዮጵያዊው ጅግና
ቢሆንም ሲፈጠር ባለመልካም ሥራ
ማለፉ እንደሁ አይቀር በተራ በተራ
መልካም ሥራ ሥራ ማለፍ ስለማይቀር
ሁሌ እንድትነሳ ሥራህ እንዲናገር
ይኸንን የሰው ልጅ አውቆና ተረድቶ
በምታልፈው ሕይወት ኗሪ ሥራ ሠርቶ
ማለፍ ተገቢ ነው ለታሪክ አምድ ትቶ፡፡

በሉ እንግዲህ ፈጣሪ ነፍስዎን በገነት ያኑረው
ሀዘኑ ከባድ ነው መሪር ነው
ስለተፈጠሩ ለወገን ደራሽ
ሳይመራቸው ቀርቶ አይደለም በጭራሽ
ፐ/ር መስፍን የጭንቋ ቀን ደራሽ፡፡

**መዝገበ ከበደ ባይሞት ኖሮ**

ማክሰኞ መስከረም ፳፯ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም/2013 ኮተቤ ካራ
አዲስ አበባ፡፡

፩



“በኢትዮ-ኢራን መካከል ያለውን ሁለንተናዊ ግንኙነት ማሳደግ ተችሏል”

ዶ/ር ሳልማን ሩስታሚ (የኢራን የባህል ማእከል ኃላፊ)

26

## የአዘጋጁ መልዕክት

# እየተዘነጋ ያለው የኮሮና ወረርሽኝ አሁንም ትኩረትን ይሻል!

ከአንድ ሚሊዮን በላይ ለሚኾኑ የሰው ልጆች ሞት ምክንያት ኾኗል፡፡ ከስድሳ ሚሊዮን በላይ የሚኾትንም አጥቅቷል፡፡ በዓለማችን ያላካለለው መሬት፣ ያልደረሰበት ሀገር የለም፡፡ የሰው ልጆችን የሕይወት ዘይቤ በእጅጉ ፈትኖ ለአዳዲስ ችግሮች ተጋላጭ አድርጓል፡፡ የኮሮና ወረርሽኝ ፤ ኮቪድ 19፡፡ ልክ እንደሌላው ክፍለ ዓለም ሁሉ ወረርሽኙ የኢትዮጵያችንን ደጅ ካንኳኳ ዐሥር ወራት እያስቆጠረ ነው፡፡ በእነዚህ ወራት ከመቶ ሺህ የሚልቅ ቁጥር ያለው ዜጋ በወረርሽኙ ተጠቅቷል፡፡ አንድ ሺህ ሰባት መቶ በላይ ሞትም ተመዝግቧል፡፡ ይኽ ኢትዮጵያ ካላት የሕዝብ ቁጥር አንጻር ቀላል ሊመስል ይችላል፡፡ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች እየተቀዛቀዘ ከመጣው ምርመራ አንጻር አስደንጋጭ ሪፖርት ነው፡፡ መንግሥት ወረርሽኙ ወደኢትዮጵያ መግባቱን ተከትሎ የማኅበረሰቡ ግንዛቤ እንዲያድግና በሽታው እንዳይስፋፋ ያግዝ ዘንድ መጠነ ሰፊ ሥራ ሰርቷል፡፡

አሁን አሁን ግን ወረርሽኙን ተከትሎ በተለያዩ የመገናኛ አውታሮች የነበረው የጥንቃቄ ዘመቻ ጋብ ማለቱን ተከትሎ ማኅበረሰባችን ስለበሽታው ያለው ግንዛቤ እክል ሲገጥመው እየታዘብን ነው፡፡ ቀድመው የነበሩ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጆች መነሳትንና እንቅስቃሴዎችም ወደ መደበኛ መልካቸው መመለስ ሕብረተሰቡ ነገሮችን ካቆመበት እንዲቀጥል የይለፍ ካርድ የተሰጠው አስመስሎበታል፡፡ ወረርሽኙን አስመልክቶ የተፈጠረው መነቃቃት ዜጎች ለጥንቃቄ የሚያስፈልጉ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብሎች ብሎም የእጅ ንጽሕና መጠበቂያ ቁሶችን እንዲጠቀሙ አስችሏል፡፡

ኾኖም አሁን ላይ ከጤና ሚኒስቴር የሚወጡት ዕለታዊ የወረርሽኙ የስርጭት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በበሽታው እየተለከፈ ያለውም ኾነ እየሞተ ያለው ዜጋ ቁጥር እየጨመረ መኾኑን ነው፡፡ በተለያዩ የዓለማችን ሀገራት “ተቆጣጠርነው” ያሉት ይኽ ወረርሽኝ ዳግም የመስፋፋት ዕድል አግኝቶ ለብዙ ምስቅልቅል ሲዳርግ ተመልክተናል፡፡ በኢትዮጵያም መሠል ክስተት እንዳይከሰት እጅጉን ያሰጋል፡፡ በዚህ ረገድ ሀገራችን በየወቅቱ የሚያጋጥሟት ፖለቲካዊ ችግሮች የማኅበረሰባችን ትኩረት ከወረርሽኙ እንዲናጠብ አንድ ምክንያት ኾኗል ማለት ይቻላል፡፡ የኾነው ኾኖ ግን እየተዘነጋ ያለው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ አሁንም ትኩረትን በእጅጉ ይሻል ስንል ለማስታወስ እንወዳለን፡፡

ቅምሻ
24

«ኢንቲጮ»
ከሆስፒታል የጠፋው ወታደር
ሠሎሞን ለማ ገመቹ.
25

ቢዝነስ ዜና
28

## ከብርሀን ፍጥነት በላይ ለምን መጓዝ አይቻልም?

አልበርት አንስታይን በአንፃራዊ እይታ ጥናቱ ላይ የብርሀን ፍጥነት የአፅናፋ አለም የብርሀን ወሰን እንደሆነ አብራርቷል። ከብርሀን ፍጥነት በላይ መጓዝ የማይታሰብና የፊዚክስ ህግንና ሌሎች መሰረታዊ ህጎችን የሚጥስ ነው። ከብርሀን ፍጥነት በላይ መጓዝ ማለት ሽጉጥን ሳንተኩስ ጥይቱ ኢላማውን መታ እንደማለትም ነው። ብርሀን በሰከንድ 300 ሺህ ኪሎሜትር ፍጥነት ይጓዛል።

በጠፈር ውስጥ የሚገኝ ቁስ አካል "Higgs field" በተሰኘ ሚስጢራዊ ሂደት ውስጥ ይንቀሳቀሳል። የተለያዩ ቁስ አካላት ከ "Higgs field"በሚያደርጉት ጥምረት የተነሳ ክብደታቸውን "mass" የገኛሉ። ከ "Higgs field" ጋር በተለያየ የጥንካሬ ደረጃና መጠን የሚፈጥሩት ጥምረት ቁሶች የተለያየ አይነት ክብደት እንዲኖራቸው የደርጋል። ብርሀን ግን ፎቶን "photon" ከሚባሉ ቅንጣቶች "Particles" ስለተፈጠረ ክብደት "mass" የለውም።

ክብደት ያላቸው ቁስ አካላት ሁሉ ምንም አይነት ፍጥነት እንዲያገኙ የሆነ ልዩ ሀይል ያስፈልጋቸዋል። የአንድን አካል ፍጥነት ወደ ብርሀን ፍጥነት እንዲቀርብ ለማድረግ ደግሞ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ሀይል መስጠት ያስፈልጋል። ምክንያቱም ፍጥነት በጨመረ ቁጥር የአንድ ቁስ ክብደትም ስለሚጨምር ነው። ይህ ከፍጥነት የተነሳ የሚፈጠር ክብደት መጨመር አስገራሚ እውነታ፤ አንድ እጅግ ኢምንት የሆነችና ለአይን እንኳን የማትታይ ቁስን በብርሀን ፍጥነት ለማስኬድ ልክ የለሽ ሀይል እንዲያስፈልግ ያስገድዳል። ምክንያቱም ይህች እጅግ ትንሽ የሆነች ነገር በዚህ ፍጥነት ለመሄድ ስትሻ ክብደቷ ገዝፎ ያልተወሰነ እና በጣም ትልቅ ስለሚሆን ነው። በዚህ አፅናፈ ዓለም ላይ አንድን ኢምንት ቁስ እንኳን በብርሀን ፍጥነት እንድትጓዝ ማድረግ ከባድ ከሆነ ሌላ የገዘፈ ነገርን በዚህ ፍጥነት እንዲጓዝ ማድረግ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ማሰብ ይቻላል።

## ኒውክሊያር ቦንብ

የኒውክሊየር ሀይል አመነጫጨት ሂደት የተመሰረተው የአቶሚክ ቦንብን ለመስራት መሰረት ጣይ በሆነው የአልበርት አንስታይን የ "E=mc^2" ቀመር ላይ ነው። አንስታይን ክብደት ወደ ሀይል ወይንም ሀይል ወደ ክብደት የሚቀየርበትን ቀመር ቢፈጥርም ይህን ቀመር ተጠቅመው የኒውክሊየር ሀይል አፈጣጠር ለዓለም ያስተዋወቁት ሁለት ጀርመናውያን ሳይንቲስቶች ናቸው። የኒውክሊየር አብላዩች (nuclear reactor) ነክሊየር ፊዥን (nuclear fission)በሚባል ሂደት የአተሞችን መሰንጠቅ (spliting of atoms) ፈጥረው በክስተቱ እጅግ ከፍተኛ መጠን ያለው ሀይል እንዲለቀቅ ማድረግ ያስችላሉ።

## የኒውክሊያር ቦንብ የሚሰራው እንዴት ነው?

ይህን ለማወቅ ስለ አቶሚክ ቦንብና ሀይድሮጂን ቦንብ መረዳት ያስፈልጋል።

ዩራኒየም -235 ወይንም ፕሉቶኒየም -239 ኒውክሊየስ በኒውትሮን እንዲመታ በሚደረግበት ግዜ ሁለት ነገሮች ይሆናሉ።የኬሚካል ንጥረ ነገሮቹ ኒውክሊየሶች ወደ ሁለት ትናንሽ ኒኩላይ ይከፈላሉ። እነዚህ ኒውክላዩች ራዲዩአክቲቭ ናቸው። ራዲዩአክቲቭ ማለት በአጭሩ ኒውክሊየሶች ወደ ሁለት ትናንሽ ኒውክላይ ሲከፈሉ በሂደቱ የሚለቀቁ አልፋ"alpha" ጋማ"gamma" እና ቤታ"beta" የተሰኑ አደገኛ ጨረሮች ናቸው። በመቀጠልም ከመጀመሪያው የመሰንጠቅ ክስተት ሁለት ወይም ሶስት ኒውክሊየሶች ሲፈጠሩ ከፍተኛ መጠን ያለው ሀይል ይለቀቃል። ኒውክሊየስ የአተም መካከለኛ ክፍል ሲሆን በውስጡ ፕሩቶን እና ኒውትሮን የሚባሉ የአተም ቅንጥብጣቢዎች (subatomic particles) አሉት። ፕሩቶን ፖዘቲቭ የኤሌክትሪክ ንዝረት (positive electric charge) ሲኖረው ኒውትሮን ደግሞ ዜሮ የኤሌክትሪክ ቻርጅ (zero electric charge) አለው።

በኒውክሊየሶቹ መሰንጠቅ የተነሳ የተፈጠረው ሀይል መለቀቅ "radioactive decay" ይባላል። ይሄ ሀይል የሚለቀቀው በዩራኒየምና በፕሉቲንየም ውስጥ ያሉትን ኒኩላይ እርስ በእርሳቸው አጣብቀና አንድ ኒውክሊየስ አድርጎ የሚይዛቸው በቂ ሀይል ስለሌለ አርፈው የማይቀመጥና የመዋለል(unstable) ይዘት ስላላቸው ነው።ይህ የኒውኪየሶች የመሰንጠቅ ሂደት ራሱን እየደጋገመ መጠኑን በሶስት እጥፍ እየጨመረ ይቀጥላል። የሂደቱ ስም ቼይን ሪአክሽን(chain reaction) ይባላል። ቅጥልጥሎሽ እንደማለት ነው። ቼይን ሪአክሽን በኒውክሊየር ማብላያዎች (nuclear reactor) ማሽኖች ውስጥ በከፍተኛ ቁጥጥር ስር መጠበቅ አለበት። አለበለዚያ ከቁጥጥር ውጪ ሆኖ ከፍተኛ መጠን ያለው ፍንዳታን ያስከትላል።

የአቶሚክ ቦንብ ፍንዳታ እንዲፈጠር የሚደረገው ቼይን ሪአክሽኑ ላይ የሚደረገው ቁጥጥር ሲቋረጥ ነው።

## የቢልጌትስ አስገራሚ እውነታዎች

1. ቢልጌትስ በየሰከንዱ 250 ዶላር፣በየቀኑ 2 ሚሊዮን ዶላር፣በአመት ደግሞ 7.8 ቢሊዮን ዶላር ያገኛል።

2. አንድ ሺ ዶላር መሬት ላይ ቢወድቅበት ዞር ብሎ እንኳን ለማየት ግድ አይኖረውም ይባላል።ምክንያቱም የወደቀበትን ገንዘብ ለማንሳት የሚያጎነብስበት አራት ሰከንድ ጊዜው ውስጥ አንድ ሺ ዶላር ስለሚያገኝ ነው።

3. የአሜሪካ ብሄራዊ እዳ 5.62 ትሪሊየን ይደርሳል። ቢል ጌትስ ይህን እዳ ለብቻዬ ልክፈል ብሎ ቢነሳ ከ1000 አመት ያነሰ ጊዜ ይፈጅበታል።

4. ቢል ጌትስ በአለም ላይ ለሚኖር ለእያንዳንዱ ሰው 15 ዶላር ቢሰጥ በእጁ ላይ 5 ሚሊየን ዶላር ይቀረዋል።

5. በአሜሪካ የአትሌት ክፍያ ታሪክ ከፍተኛ ተከፋይ የነበረው ማይክል ጆርዳን ሳይበላና ሳይጠጣ በአመት የሚያገኛትን 30 ሚሊዮን ዶላር እያንዳንዷን ሳንቲም ቢያስቀምጥ የቢል ጌትስን የመሰለ ሃብት ለማጠራቀም 277 አመታትን ይፈጅበታል ተብሏል።

6. ቢል ጌትስ ሀገር ቢሆን ኖሮ የአለማችን 37ኛ ሃብታም ሃገር ሊሆን ይችል ነበር።

7. ቢልጌትስ ያለውን ገንዘብ በሙሉ በባለ 1 ዶላር ኖት ቢመነዝረው፣ከምድር እስከ ጨረቃ የሚደርስ 14 መስመር የደርሶ መልስ መንገድ መስራት ይችላል። ነገር ግን ገንዘቡን በማመላለስ ይህን መንገድ ለመገንባት 1400 አመታት እና 713 ቦይንግ 747 አውሮፕላኖች ያስፈልጋሉ።

8. ቢል ጌትስ እስከ 75 አመት ድረስ ለመኖር ቢታደልና ገንዘቡን በሙሉ ከዕለተ ሞቱ በፊት ተጠቅሞ ይጨርሰው ቢባል በየቀኑ 6.78 ሚሊዮን ዶላር ማውጣት ይኖርበት ነበር።



# ‹‹ኢንቲጬ›› ከሆስፒታል የጠፋው ወታደር

ሠሎሞን ለማ ገመቹ.

1972 ዓ.ም ሕዳር 22 ቀን፡፡ ከከፋ ክፍለ ሃገር ጊሚራ አውራጃ፣ አማን ከተማ ወደ ሸዋ ከመጡት ሃምሳ ምልምል ወታደሮች መሀል አንደኛው የነበረው የቤንቹ የጦር አለቃ ልጅ፤ በሰልጣኙ የ18ኛው ተራራ ክፍለ ጦር ምድብ ውስጥ ተካተተ፡፡ በታጠቅ የጀመረው የክፍለ ጦሩ ሥልጠና በሁርሶ ሲጠናቀቅ፤ ጉዞ ወደ ትግራይ ሆነ፡፡ በምልመላው ጊዜ ሻለቃ መገርሣ ቀበታ ‹‹የነብር ግልገል›› ያሉትን አፍለኛ ወጣት፤ ሥልጠናው ይበልጥ ንቁ፣ ቀልጠፋና ቅብጥብጥ አደረገው፡፡ ‹‹ለእናት ሃገር ኢትዮጵያ ክብርና አንድነት አንድ የሚያኮራ የጀግንነት ተግባር ፈፅም!›› የሚለው ስሜትም ውስጡን ናጠው፡፡ ያኔ… ጓንዴ ይዘው እዛም እዚም የሚተኩሱትን፣ ገና በማቆጥቆጥ ላይ የነበሩትን ወንበዴዎች፣ በሁለት ሺኅ አሥራ ሦስት ጃጅተውም ሳሉ ፈርያናዊ ትዕቢታቸው ልባቸውን ያደነደነውን የእናት ጡት ነካሾች፤ ለማርበድበድና ልክ ለማስገባት ተቁነጠነጠ፡፡

አፍለኛው ወጣት ወታደር በመንፈስም፣ በአካልም ለግዳጅ ዝግጁ ሆኖ የሚገኝበትን የ18ኛ ተራራው ክፍለ ጦር፣ የ35ኛ ተራራ ብርጌድ፣ 351ኛ ነብሮ ተራራ ሻለቃ፤ ማይ-ነብሪ ከሚባለው ቦታ ወንበዴዎች የደፈጣ ጥቃት ሰነዘሩበት፡፡ ሥፍራው ለአጥቂው ኃይል የሚመች፣የተከላካዩን ጦር የውጊያ ንቅናቄ የሚገድብ ነበር፡፡ የመጀመሪያቸው ከነበረው አደገኛ ውጊያ ጋር የተጋፈጡት የ351ኛ ተራራ ሻለቃ ልጆች፤ እየሞቱ! እየቆሰሉ በፍልሚያው ቀጠሉ፡፡ የሻለቃው አካል የሆኑት የተራራ ሻምበሎች ጥቂት የማይባሉ ተዋጊዎች በውጊያው ሜዳ ወደቁ፡፡ እንዲያም ሆኖ የደፈጣ ጥቃት የሰነዘረባቸውን የወንበዴ ቡድን ማስለቀቅ ቻሉ፡፡

የነብሩ ግልገል የሚገኝበት 351ኛ ተራራ ሻለቃ፤ ሌሎች ውጊያዎችን በነበለት፣ በአላአሳና በሌሎችም ሥፍራዎች አካሄደ፡፡ አንድ ቀን ደግሞ የቅርብ አለቃው ኢንቲጬ በምትባል ሥፍራ በሚገኝ አንድ ኮረብታ ላይ ጎድበው ጓንዴ የሚተኩሱ ወንበዴዎችን አደብ እንዲያሲይዝ ለቤንቹ ዓርበኛ ልጅ ቀጭን ትዕዛዝ ሰጠው፡፡ ትዕዛዙን የተቀበለው የነብሩ ግልገል፤ በኃዱ ሥር ያሉትን ወታደሮች እየመራ ወደ ተባለው ኮረብታ ተነቃነቀ፡፡ ወንበዴዎቹን ደምስሶ፣ ታጥቀውት የነበረውን ጓንዴና ሌሎች ጠመንጃዎች ከባልደረቦቹ ጋር ይዞ ‹‹አ! አሃ! ሳንጃ ወደረ ኮርሚ!…›› እያለ ተመለሰ፡፡ አለቃውም ‹‹ኢንቲጬ›› የሚለውን ስም አወጣለት፡፡ ያም ስም በጦር ሜዳ ታዋቂ መጠሪያው ሆነ፡፡

በየካቲት ወር 1973 ዓ.ም በአፀርጋ በተካሄደው ከፍተኛ ፍልሚያም ኢንቲጬ ተሳተፈ፡፡ የፍልሚያው ወረዳ ጠላት ወደመሸገበት አካባቢ ለመነቃነቃነቅም ይሁን ታላሚዎችን ለመመልከት አመቺ አልነበረም፡፡ በዚያ ላይ ወንበዴው በነበረው ሰንበሌጥና የዕጣን ዛፍ እሳት ሲለቅበት፤ ምድር የነደደች መሰለች፡፡ የ18ኛ ክ/ጦር 35ኛ ተራራ ብርጌድ፣ የ351ኛ ተራራ ሻለቃ፣ የ3ኛ ሻምበል ልጆች የማይበገሩ ሆኑ፡፡ በውጊያው የሦስተኛው ሻምበል ሦስተኛው የመቶ አዛዥ የመቶ አለቃ አወቀ ብርሃኑ ተሰዋ፡፡ ወዲያውም ከአጠገቡ የነበረው ‹‹ኢንቲጬ›› የመታኮሻ ቦታውን ለወጠ፡፡ የመቶ መሪውን ተኩሶ በጣለው የጠላት ተዋጊ ላይ አነጣጠረ፡፡ ዒላማው በዓላሚው ዕይታ ውስጥ ገባ፡፡ ግልገሉ ነብር ምላጩን ሳበ፡፡ ጥይቷ ታላሚውን አገኘች፡፡ ነብሩ የተሰዋውን አለቃ ተክቶ የመቶውን ጦር ያስተባብር ጀመር፡፡ እየተዋጋ በማዋጋቱ ተግባር ተጠመደ፡፡ በግንባሩ የነበሩት የ351ኛ ተራራ ሻለቃ ሻምበሎች ጨበጣ እንዲሰነዝሩ ትዕዛዝ ተሰጣቸው፡፡ የሕወሓት ወንበዴ እግሩን ነቀለ፡፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት በአፀርጋ ፍልሚያ ድል ተጎናፀፈ፡፡

‹‹በትግራይ የሚገኙ ወንበዴዎች አለቀላቸው…›› በተባለበት አጋጣሚ፤ 18ኛ ተራራ ክፍለ ጦር ትግራይን ለቆ ወደ ኤርትራ እንዲሻገር ትዕዛዝ ደረሰው፡፡ ኢንቲጬ ከብርጌዱ፣ ከሻለቃውና ከሻምበሉ ጋር ወደ ኤርትራ ተነቃነቀ፡፡ 351ኛ ተራራ ሻለቃ ነፋሲት በምትባለው ሥፍራ ቦታ ያዘ፡፡ ከቀናት ቆይታ በኋላ ብዙ ዝግጅት የተካሄደበትና እጅግ ብዙም የተባለለት የቀይ ኮከብ ሁለ-ገብ ዘመቻ የመጀመሩ ዜና ተሰማ፡፡ ቀን ተቆርጦ ሠራዊታችን ከነገ ዛሬ ነጎድጓዳዊ ጥቃት ይሰነዝራል ተብሎ ሲጠበቅ፤ የነበሩትን ነገሮች ሁሉ እንዳልነበሩ የሚያደርግ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡

ሻዕቢያ አልጌና በሚገኘውና በጄነራል አበራ አበበ በሚመራው ውቃው ዕዝ ላይ የካቲት 5 ቀን ውጊያ ከፈተ፡፡ በሰነዘረው ተከታታይና ማዕበላዊ ማጥቃትም ‹‹ካታር›› ከሚባለው ከፍተኛ ኮረብታ ላይ የሠፈረውን 19ኛ ተራራ ክ/ጦር አወረደው፡፡ ይህ ሁኔታ እንደተሰማ ኢንቲጬ የሚገኝበት 351ኛ ነብሮ ተራራ ሻለቃ፤ ከነፋሲት በአውሮፕላን በአስቸኳይ ተጓጉዞ አልጌና ግንባር እንዲገኝ ተደረገ፡፡ አልጌና እንደደረሰም 19ኛ ተራራ ክፍለ ጦር የለቀቀውን ኮረብታና ወደ ኮረብታውም የሚያቃርቡትን ወታደራዊ መሬቶች መልሶ ለመያዝ ወደሚያስችለው ውጊያ ገባ፡፡ ከሻለቃው መነሻ መስመር በስተጀርባ ቀይ-ባሕር ነው፡፡ ከፊት ለፊት ወደ ካታር ኮረብታና ወደ ሌሎች ከፍተኛ ቦታዎች ፈጣን ንቅናቄ ለማድረግ የማያስችልና እግር የሚያስር አሸዋ አለ፡፡ በዚያ ላይ ጊዜያዊው ድል ያሰከረው የሻዕቢያ ተዋጊ ልዩ የመፋለም ብቃት አለው፡፡

በነብሩ ግልገል ኢንቲጬና በሌሎች መሰል ወጣት ነብሮች የተዋቀረው 351ኛ ተራራ ሻለቃ፤ በመረራ ደረቅ ወንዝ፣ በቀጭኔ፣ በመሐመድ ኮረብታዎች ላይ ተዓምረኛ ውጊያ አካሄደ፡፡ ጠላት ከወገን ተቀላቀለ፡፡ መራር በነበረው ፍልሚያ ሬዲዮናቸው በመመታቱ ከሻለቃው ጋር የነበራቸውን ግንኙት ያቋረጡት የሁለተኛ ተራራ ሻምበል ወታደሮች ተጎዱ፡፡ ጨበጣ በተሰነዘረበት የውጊያ ቦታ ከሻዕቢያ ተዋጊዎች ጋር በቴስታ ጭምር ሲመታቱ የነበሩትን ጨምሮ፤ የደብረ ታቦሩ ልጅ ብርሃኑ ጀንበሬ፣ የሰሜን ሸዋ ይሁን የጎጃም ልጅ የነበረው ጫኔ ወደቁ፡፡… ኢንቲጬም በተፋፋመው ውጊያ መሀል ተመታና በአልጌና አሸዋ ላይ ተዘረረ፡፡ ሌሎች የ18ኛ ተራራው ክፍለ ጦር አምባሳደር የሆነው የ351ኛ ተራራ ሻለቃ ልጆች ውጊያውን አፋፋሙት፡፡ የሻዕቢያን ተዋጊዎች አስጨንቀውና መላወሻ አሳጥተው ሲያበቁም፤19ኛ ተራራ ክፍለ ጦርን አስለቅቀውት በነበረው ካታር ኮረብታ ላይ መልሰው ሰቀሏቸው፡፡

የካቲት 12 ቀን 1974፡፡ ጦርነቱ ጋብ አለ፡፡ አንድ ዙ-23 በተጠመደባት ካሚዮን የመጡ ወታደሮች ኢንቲጬንና ሌሎች ቁስለኞችን አነሱ፡፡ ከሰዓታት በኋላ ወደ አሥመራ ተወሰዱ፡፡ ኢንቲጬ ገጀረት ሆስፒታል ደርሶ አስቸኳይ ሕክምና ተደረገለት፡፡ ቀጣይ ሕክምናውንም በኤክስፖ ማገገሚያ ጣቢያ ሆኖ እንዲከታተል ተደረገ፡፡ ከቅርብ ርቀት አንገቱ ሥር አካባቢ የተመታ በመሆኑ ቁስሉ በቀላሉ አልድን አለ፡፡ በዚያ ሁኔታ ላይ ሆኖ ሌሎች ወታደሮች በፍጥነት እያገገሙ ወደ ግንባር ሲመለሱ ተመለከተ፡፡ ሐኪሞች ‹‹ከፍተኛ ሕክምና ያስፈልግሃል…›› ያሉት ቢሆንም ‹‹እንደዚህ ሆኜ እስከመቼ እቆያለሁ? ወደ ግንባር ተመልሼ የሠራዊታችን አጠቃላይ ድል ተቋዳሽ መሆን አለብኝ…›› የሚለው ሐሣብ አላስቀምጥ አላስተኛ አለው፡፡ ስለሚጠዘጥዘውና ስለሚያመረቅዘው ቁስሉ ለማሰብ ጊዜ አጣ፡፡

በአንደኛው ቀን በሐኪሞች ቃል ወደ ጦር ግንባር መመለስ እንደሚችሉ የተነገራቸው የእናት ኢትዮጵያ ወታደሮች በልዩ የሃገር ፍቅር ስሜት በየመኪናዎቹ ላይ ሲሳፈሩ፤ኢንቲጬም በአንደኛው መኪና ላይ ወጥቶ ቦታ ያዘ፡፡ ጉዞ ከአሥመራ ወደ ምፅዋ፡፡ ከምፅዋ በመርከብ ወደ አልጌና፡፡ መርከቢቱ ቀይ-ባሕርን እየቀዘፈች መርሳ-ጉልጉብ ደረሰች፡፡ ከገጀረት ሆስፒታል የማገገሚያ ቦታ የጠፋው ኢንቲጬ ከመርከብ ወርዶ የጦር ክፍሉን ተቀላቀለ፡፡ ግን በአልጌና የውጊያው ፍፃሜ መሆኑን የሚያመለክት አንዳች ነገር አልነበረም፡፡

ከቀናት በኋላ ለኢንቲጬ ተዋጊ ሻለቃ ከአልጌና ወደ ናቅፋ እንዲያመራ የንቅናቄ ትዕዛዝ ደረሰው፡፡ ከክፍሉና ከ29ኛ ሜካናይዝድ ብርጌድ መድፈኛ ሻለቃ ባልደረቦች ጋር በእግር ተጉዞ ተስፋዬ በር ደረሰ፡፡ የ351ኛ ተራራ ሻለቃ አባሎችን እያቀፉ የክፍለ ጦሩ ዋና አዛዥ ኮሎኔል መርዳሣ ሌሊሣ ተቀበሏቸው፡፡ ከዚያም ሻለቃዋ በናቅፋ ግንባር በከፍታ ነጥብ 1702 ላይ ለተወሰነ ጊዜ ቆየች፡፡ ‹‹የቀይ ኮከብ ዘመቻ ምዕራፍ ሁለት፤ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ…›› በተባለ ጊዜም ሻለቃዋ ከብርጌዷ ጋር ወደ ምዕራባዊ ቆላ ተንቀሳቀሰች፡፡ ‹‹ላባ›› በሚባለው ልዩ ቦታም የመከላከያ ወረዳ ያዘች፡፡

1975 ዓ.ም ወርሃ መጋቢት፡፡ ሻዕቢያ ‹‹ላባ›› በሚገኘው 351ኛ ተራራ ሻለቃ ላይ ከበስተጀርባው ማጥቃት ሰነዘረ፡፡ ወገን ደርሶ የሻለቃውን ጦር ከውጊያ እስኪያላቅቀው ድረስ፤ ምድር ቁና ሆነች፡፡ ኢንቲጬ እግሩ ላይ ተመታ፡፡ ምቱ ከፍተኛ በመሆኑ ከነበረበት ሥፍራ መነቃነቅ አልሆነለትም፡፡ እሱን ለማንሳት የተንቀሳቀሰው የአዲ-ጓደዱ ልጅ ደስታ ሐጎስ ተሰዋ፡፡ ውጊያው ጋብ ሲል የነብሩን ግልገል! በርከክ ብሎ ደሙን ከሚያዘራበት ቦታ ባልደረቦቹ አንስተው ወደ አፋ-ቤት ናደው ዕዝ መምሪያ ወሰዱት፡፡ ከዚያም ወደ አሥመራ ገጀረት ሆስፒታል፡፡ ከሆስፒታሉም ወደማገገሚያ ማዕከል፡፡ የቁስለኛው ማኅደር ወጥቶ ሲታይ፤ ኢንቲጬ ከአልጌና ግንባር ቆስሎ የመጣና ከማገገሚያው የጠፋው ወታደር መሆኑን መሰከረ፡፡ እነ ዶክተር ጄነራል ጋጋ ኦልጆ ‹‹ይሄ ወታደር በየት በኩል ወደ ግንባር ሄዶ ተመልሶ ቆስሎ መጣ?!›› እያሉ አግራሞታቸውን ገለጹ፡፡ /ለብርሃኑ ወልደሰንበት (ሻለቃ)-አሜሪካ ላስቬጋስ./

# “በኢትዮ-ኢራን መካከል ያለውን ሁለንተናዊ ግንኙነት ማሳደግ ተችሏል”

**ዶ/ር ሳልማን ሩስታሚ (የኢራን የባህል ማእከል ኃላፊ)**



እንደ ሀገር የረጅም ዘመናት ታሪክ ካላቸው አራቱ የዓለም ሀገራት መካከል ኢራንና ኢትዮጵያ በገናናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ቻይናና ግሪክ ከኢትዮጵያ በመልከዐምድር በመራቃቸው ምክንያት ያላቸው ግንኙነትም ያን ያህል የጎላ አልነበረም፡፡ ኢትዮጵያና ኢራን ግን በእድሜ ጠገብ ታሪካቸው ግንኙነታቸውም የቆየ እንደሆነ ይነገራል፡፡ በዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክም ኢራን ከግማሽ ክፍለዘመን የተሸገረ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ከኢትዮጵያ ጋር ፈጥራለች፡፡ እስካለንበት ዘመን ድረስም በጠላትነት ሳይተያዩ በወንድማማችነት ጸንተው መቆየት ችለዋል፡ ፡ ስለ ኢትዮ-ኢራን ግንኙነት ታሪክና የሕዝብ ለሕዝብ ወዳጅነት ምን እየተሰራ ነው ሲል የግዮን መጽሔት ዝግጅት ክፍል የኢራን የኢራን የባህል ማእከል ኃላፊከሆኑት ዶ/ር ሳልማን ሩስታሚ ጋር የሚከተለውን ቆይታ አድርጓል፡፡

**ግዮን፡- ስለ ኢራን ሕዝብና ባህል ትንሽ ይንገሩን?**

ዶ/ር ሩስታሚ፡- ኢራን በምዕራብ እስያ የምትገኝ ካስፒያን ባህር፣ የፋርስ ባህር ሰላጤ የሚዋሰኗት ሀገር ናት፡፡ አራቱም ወቅቶች የሚፈራረቁባት ደማቅ የታሪክ ሀብት ያላት ሀገር ናት፡፡ ለቁጥር የሚታክት ቅርስ ያላት ምርጥ ምግብና መስተንግዶን የታደለች ሀገር ናት፡፡ ኢራን እድሜ ጠገብ ሥልጣኔ ካላቸው ሀገር በቀዳሚነት ተርታ የምትሰለፍ ናት፡፡ ውስብስብ የሆነና በሥነሀሳብ የበለፀገ ሥልጣኔዋም ከጥንት ጀምሮ ያልተቋረጠ ነው፡፡ ከኢራን ሥልጣኔ ውጤቶች ውስጥ አንዳንዶቹ የዓለም ሕዝብ በሙሉ ተጠቅሞባቸዋል ማለት ይቻላል፡፡

የኢራን ዋና ከተማ ቴሂራን የሀገሪቱ ዋናና ብዙ ሕዝብ የያዘው ከተማ ነው፡፡ ኢስፋሀን፣ ሺራዝ፣ ታብሪዝ፣ ማሻድ የተሰኙ ትልልቅ ከተሞችም አሏት፡፡ ፋርስ ወይም ፐርሺያን የተሰኘው የሀገሪቱ የሥራ ቋንቋ በስፋት ይነገራል፡፡ ቱርክሜን,ኩርድ,አረብኛ፣የተሰኙ ቋንቋዎችንም የሚናገሩ በርካታ ዜጎች አሉ፡ በተጨማሪም ባሉቺ፣ ጊላኪ፣ ማዛንዳራኒ ዘዬዎች ይነገራሉ፡

ኢራን የበርካታ ሥርወ መንግሥታት መናኸሪያም ነበረች፡ ፡ ሳይንሳዊ ማስረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከድንጋይ ዘመን አንስቶ የተለያዩ ሥልጣኔዎች እንደተፈራረቁ ይታወቃል፡፡ ሕዝቡ በረጅም ታሪክ የዳበረ ባህል ስላለው በቀላሉ ከሰው የሚወዳጅ፣ ሥርዓት ያለው እና ክብር የሚሰጥ ሕዝብ ነው፡፡ የኢራን ባህል ከጥንት ጀምሮ በነበሩ የታወቁ ምልክቶች የሚታወቅ ነው፡፡ ኢራንን ከሌሎች ሀገራት የሚለያት ከመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት የፀሐይ ካላንደርን የምትጠቀም ብቸኛ ሀገር መሆኗ ነው፡፡ ፀደይ ሲጀምር አዲስ አመት መጀመሯም ከዓለም ሃገራት የተለየች ያደርጋታል፡፡ ኢራን የተለያዩ ባህሎች፣ ዜጎች፣ ብሔሮች፣ ቋንቋዎች እና ኃይማኖቶች የሚገኙባትም ናት፡፡ ይኽ ልዩነቶችን ለማስተናገድ የተመቻቸው ሁኔታ ብዙ ዓይነት ባህሎች ለረጅም ዘመናት ተጠብቀው እንዲቆዩ አስችሏል፡፡ የኢራንን የበለፀገ ባህል አሁን ካላት በርካታ የሚታይ ቅርስ ለይቶ መመልከት አይቻልም፡ ፡

**ግዮን፡- የጥንቷ ኢራን ኃያላን ከሚባሉ ጥቂት ሀገራት ተርታ የምትሰለፍ እንደመሆኗ ከኢትዮጵያ ጋር የሚያመሳስላት ባሕል ምንድነው ይላሉ?**

ዶ/ር ሩስታሚ ፡- ኢራንና ኢትዮጵያ ቢያንስ 2 ሺህ ዓመት የሚያስቆጥር የሁለትዮሽ ግንኙነት አላቸው፡፡ ይኽ ግንኙነት በባህል ልውውጥ የታጀበ ነበር፡፡ አንዱ የአንዱን ባህል በግንኙነቱ ሳቢያ ሲቀባበል ነው የኖረው፡፡ ይኽን የባህል ልውውጥ ለማስረዳት ቋንቋውን ማየት እንችላለን፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ከኢራን ቋንቋ በውሰት የተገኙ ቃላቶች አሉ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የኖሩ ኢራናውያን በጣም ጥቂት የነበሩ ቢሆንም፣ ኢትዮጵያውያን ግን ቃላቶቹን አሁንም በቋንቋቸው ውስጥ እየተጠቀሙባቸው ይገኛሉ ለምሳሌ የሚከተሉትን ማየት እንችላለን፡፡

ከቋንቋ ባሻገር፣ ከባህል አኳያ ካየነው በሥነ ሕንፃና በግንባታ ዘርፍ የሚያመሳስሉ ነገሮች አሉ፡፡ ድሬዳዋና ሐረር በ17ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ የተገነቡ ቤቶች የኢራንን ባህላዊ የግንባታ ምህንድስና የተከተሉ ናቸው፡፡ በተለይ ሐረር ያለ መስጊድ አሠራር፣ በወቅቱ ኢራን ውስጥ ይገነቡ ከነበሩት ጋር በጣም ይመሳሰላል፡፡

**ግዮን፡- አሁን ያለው የኢራንና የኢትዮጵያ ግንኙነት ምን ይመስላል?**

ዶ/ር ሩስታሚ ፡- የኢትዮ-ኢራን ግንኙነት አሁን በከፍተኛ መነቃቃት ላይ ይገኛል፡፡ በተለይ በኢኮኖሚና ማህበራዊ መስኮች ያለውን ግንኙነት ሁለቱም ሀገራት እየተጠቀሙበት ነው፡፡ በወዳጅነት ላይ የተመሠረተው ግንኙነት በባህል በኩል የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት እንዲኖር መደረጉ አዎንታዊ ውጤት እያመጣ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ለኢራን ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ሀገራት ምቹ ናት፡፡ በተለይ ባህላዊ ትስስርን ለመፍጠር በሯ ክፍት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የኢራን እስላማዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ በባህል ተቋሙ አማካኝነት የጀመረውን እንቅስቃሴ እያጠናከረ ይገኛል፡፡ በፈረንጆቹ 1992 የባህል ተቋሙ በኤንባሲው በይፋ ሥራውን ጀምሮ ነበር፡፡ በ2004 በተደረሰው አጠቃላይ ስምምነት፣ በሁለቱ ሀገራት መካከል በተለይ በትምህርት መስክ ያለውን ግንኙነት ለማሳደግ ተችሏል፡፡ አዲስ አበባ የተፈረመው

| Amharic | English pronunciation of Amharic words | Persian | English pronunciation of Persian words |
|---|---|---|---|
| አናናስ | Ananas | آناناس | Ananas |
| ሙዝ | Mooz/Muzi | موز | Moz |
| ዝንጅብል | Zinjibli | زنجبیل | Zanjebil |
| ባቄላ | Bakela | باقاله | Baghale |
| ሱካር | Sikuar | شکر | Shekar |
| ውቅያኖስ | Wuqiyanos | اقیانوس | Oqiyanos |
| ቁልፍ | k'ulife | قفل | Ghofl |
| ክብሪት | kibirite | کبریت | Kebrit |

ይህ የመግባቢያ ሰነድ በትምህርትና በባህል መስክ በትብብር ለመስራት የሚያስችል ነው። ይህ የመግባቢያ ሰነድ የፕሮፌሰርና የተማሪዎችን ልውውጥ ለማካሄድ፣ እንዲሁም ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በትምህርት አሠጣጡ ላይ እገዛ ለማድረግና ግንኙነቱን ለማሻሻል የሚስችል ነው፡ ፡ በዚህ ስምምነት መነሻ በ2008 ላይ ለአዲስ አበባ ቤተመጻሕፍት ድጋፍ ለማድረግ በተደረገ ስምምነት ሁለቱ ሀገራት ያላቸውን ግንኙነት በባህላዊ ቅርስ ዙሪያም እንዲያሳድጉ አስችሏል።

**ግዮን፡- የኢራን ኤምባሲ የባህል ተቋም ሥራዎች ምን ምን ናቸው?**

ዶ/ር ሩስታሚ ፡- በኢትዮ-ኢራን ስምምነት መሠረት የባህል ማዕከሉ በርካታ ሥራዎችን ይሠራል። ከተግባሮቹ መካከል ኢትዮጵያውያንን ፐርሺያን ቋንቋ ማስተማር አንዱ ነው። በዚህም ተግባር በርካታ ኢትዮጵያውያንን ተሳታፊ ሆነዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ኢራኖሎጂ ትምህርት ለ3 ወራት ይሠጣል። ይህ ትምህርት የኢራንን ረጅም ታሪክና የኢትዮ-ኢራን ግንኙነትን ለማሳወቅ የሚሠጥ ነው። ከመደበኛ ትምህርት ሌላ ተቋሙ ሴሚናሮችን ያዘጋጃል፡ ፡ በነዚህ ፕሮግራሞች ላይ ማህበራዊና ባህላዊ መስቦች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ይቀርባሉ። በነዚህ ዝግጅቶች በርካቶች እንዲገኙ እየተደረገ ኢትዮጵያውያንና ኢራናውያን እንዲወያዩ ይደረጋል። ይህም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱን ያጠናክረዋል። የባህል ማዕከሉ ኢማም ሆሚኒ የተሰኘ ቤተመጻሕፍ ያለው ሲሆን ስለኢራንም ሆነ ስለ ኢትዮ-ኢራን ግንኙነት ለማወቅ ለሚፈልጉ በሩ ክፍት ነው። ለኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ማጥኛ የሚሆን ምቹ ሁኔታን የፈጠረም ነው። በቤተ መጻሕፍቱ ውስጥ ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ከሚሆኑ መፃህፍት ጀምሮ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የሚሆኑ የተለያዩ መጻሕፍት ይገኛሉ። በማዕከሉ መገልገል የሚቻለው ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ከጠዋቱ 2:30 እስከ ቀኑ11 ሰዓት በተጨማሪም ቅዳሜ ከጠዋቱ 2:30 እስከ ቀኑ 6:00 ነው።

**ግዮን፡- "ኢራኖሎጂ" ስለተባለው ትምህርት የበለጠ ሊነግሩን ይችላሉ? ትምህርቱ በኢትዮ-ኢራን ግንኙነት ውስጥ ያለው ጠቀሜታስ ምንድ ነው?**

ዶ/ር ሩስታሚ ፡- ኢራኖሎጂ የፋርስ(ኢራን) ታሪክን እንዲሁም የኢትዮ-ኢራንን ግንኙነት የሚያጠና ነው። ይህ ትምህርት በሳምንት አንድ ጊዜ ለ2 ሰዓታት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመጡ መምህር ይሰጣል። በቅርቡ የባህል ማዕከሉ 15ኛ ዙር የኮርሱ ተማሪዎችን አስመርቋል።

ኮርሱ የኢራንን እውነተኛ ገጽታ ለኢትዮጵያውያን ለማስረዳት ጠቃሚ ነው፡ ፡ በተጨማሪም በሥነ-ጥበብ ፣ በሥነ-ጽሑፍ ፣ በኢኮኖሚ ፣ እና በፖለቲካ ጉዳዮች ዙሪያ ያለውን ታሪክ በጥልቀት ለማወቅ በጣም አስፈላጊ ኮርስ ነው።

የትምህርቱ አጠቃላይ ዓላማ የኢራንን በተለይም ደግሞ የመካከለኛው ምሥራቅን ታሪክ፣ ፖለቲካ፣ ጂኦግራፊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኀበራዊ፣ ባህላዊ እሴቶች እና ቅርሶች ለተማሪዎቹ ማሳወቅ ነው። በተጨማሪም የቆየውን የኢትዮ-ኢራን ግንኙነት ለመገምገም የሚያስችል ነው። በይበልጥ ደግሞ የሁለቱ ሉዓላዊ አገራት ማለትም የኢትዮጵያ እና የኢራን የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ለማጠናከር ይረዳል።

**ግዮን፡- የኢትዮ-ኢራን የባህል ግንኑነትን ከማጠናከር አንጻር የያዛችሁት ዕቅድ ምን ይመስላል?**

ሮስታሚ፡- እኛ በሁለቱ ሀገሮች የባህልም ኾነ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ለማጠናከር የተለያዩ ዕቅዶች አሉን። የተወሰኑትን መጥቀስ እችላለሁ።

1. በሀገራቱ መካከል ባህላዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ትምህርታዊ እና ጥበባዊ ግንኙነቶችን ማስፋፋት፡ ፡

2. የኢራንን ባህልና ሥልጣኔ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማስተዋወቅ።

3. በሁለቱ ሀገሮች መካከል ወንድማማችነትን፣ አንድነትን እና የፍቅር ትስስርን ማጠናከር።

4. የሁለቱን ሀገራት ሳይንሳዊ እና ባህላዊ ተቋማት በዩኒቨርሲቲዎችም በኩል ማስፋት እና ማጠናከር።

5. የኢራንን ቋንቋ እና ሥነ ጽሑፍ ማስተዋወቅ።

6. በሁለቱ ሀገራት ያሉ ታዋቂ የባህል እና የሥነ-ጽሁፍ ከያኒያንን ፣ ገጣሚያንንና ደራሲያንን ማስተዋወቅ።

7. በተለያዩ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት መስኮች የፕሮፌሰሮች፣ የምሁራንና የተማሪዎች የልምድ ልውውጥ ማድረግ።

8. ምሁራዊ፣ ትምህርታዊ እና ሥነ ጽሑፋዊ መጻሕፍትን ማሳተም።

9. ተፈጥሮአዊ ስፍራዎችን፣ ታሪካዊ ሐውልቶችን እና የሁለቱን ሀገራት የተቀደሱ ቦታዎች ለቱሪስት መስህብነት ማስተዋወቅ።

10. ባህላዊና ትምህርታዊ ጉባኤዎችን እንዲሁም ሴሚናሮችን ማካሄድ።

ግዮን፡- ከተቀረው አፍሪካስ ጋር ያላችሁ ግንኙነት ምን ይመስላል?

ዶ/ር ሩስታሚ0፡- ኢራን ከአፍሪካ ሀገራት ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች መሥርታለች፡ ፡ በርካታ የትብብር ስምምነቶችን በመፍጠርም ከአፍሪካ ሀገራት ጋር የባህል፣ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ግንኙነቷን ለማሳደግ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች ነው። በተጨማሪም አሁን ላይ ኢራን በአፍሪካ ሕብረት እንደ አጋር ሀገር የምትቆጠር ነች። በዳበረ ወዳጅነት ውስጥ የኢራንን ባህልና ታሪክ የማስተዋወቅ ከፍተኛ ፍላጎት አለን።

**ግዮን፡- ከኢትዮጵያም ኾነ ከተቀረው ዓለም ጋር ወዳጅነቶችን ለማሳለጥ እንቅፋቶች ኾነዋል የሚሏቸው ጉዳዮች ምንድናቸው?**

ዶ/ር ሩስታሚ ፡- ኢትዮጵያን ጨምሮ በወዳጅ ሀገሮች መካከል ያለው የሁለትዮሽ ግንኙነት በከፍተኛ ሁኔታ ተስፋፍቷል። ነገር ግን ኢራን ውስጥ ኢትዮጵያ ኤምባሲ የሌላት ሀገር በመኾኗ ግንኙነታችንን ይበልጥ ለማጠናከር በምናደርገው ጥረት አንድ መሰናክል ኾኖብናል። በዚህ አጋጣሚ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣናት በቴህራን ኤምባሲ ስለማቋቋም አስፈላጊነት ዳግም ሊያስቡበት ይገባል። የኢትዮጵያ መንግሥት በቴህራን የሚገኘውን ኤምባሲ በ1998 በበጀት ምክንያት ነበር የዘጋው።

ኢራን ኤምባሲዋን በአዲስ አበባ ከከፈተች 70 ዓመት ኾኗታል። ከካይሮ ቀጥሎ በአፍሪካ ሁለተኛው የኢራን ኤምባሲ የሚገኘው እዚህ ነው፡ ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሁለቱ ሀገራት አስተማማኝ እና መልካም ግንኙነት በመፍጠራቸው በኢራን እና በኢትዮጵያ የነበሩትን አገዛዞች መለዋወጥ እንኳን የሀገራቱን ወንድማማችነት ሊያበላሽ አልቻለም። ሁለቱ ሀገሮች በቀጣዮቹ ዓመታትም የትብብር ዘርፎችን በመለየት ጠንካራ ግንኙነታቸው እያደገ እንደሚሄድ ሙሉ እምነት አለኝ።

**ግዮን፡- የኢትዮጵያን ባህል እንዴት አገኙት? ኢራናውያንስ ስለ ኢትዮጵያስ ምን ያውቃሉ?**

ዶ/ር ሩስታሚ ፡- ወደ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ስመጣ ብዙ ተመሳሳይ ነገሮች ስላጋጠሙኝ ኢትዮጵያን እንደ ሁለተኛ ቤቴ ሆና ነው ያገኘኋት። ኢራንና ኢትዮጵያ ታሪካዊ ሀገራት በመኾናቸው የተሳሰሩባቸው ብዙ የጋራ ጉዳዮች አሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደስ የሚል፣ እንግዳ ተቀባይ እና ሀገሩን ሲያስተዋውቅ ኩራት የሚሰማው ሕዝብ ነው። ኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች ልዩ ልዩ እና አስገራሚ የአኗኗር ባሕል ያላቸው ከ80 በላይ ብሔረሰቦች መኖሪያ ናት። የአውሮፓውያንን ቅኝ ግዛት በተሳካ ሁኔታ የመከተች ብቸኛ ሀገር በመሆኗም ከሌሎቹ የአፍሪካ አገራት የተለየች ያደርጋታል።

በኢትዮጵያ የኢራንን ባሕል ለማስተዋወቅ ከምናደርገው እንቅስቃሴ በተጨማሪ ስለ ኢትዮጵያ የተለያየ ባሕል፣ ዕድሜ ጠገብ ታሪክ እንዲሁም አስደናቂ ብዝኃ-ሕይወት ለኢራን ሕዝብ አስተዋውቀናል። ለምሳሌ፣ ኢትዮጵያ በነበርኩበት አንድ ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ ፣ ከ65 በላይ አርቲክሎችን በፐርሺያ ቋንቋ ጽፌ በተለያዩ ሚዲያዎች ለኢራናውያን ስለኢትዮጵያ በማስተዋወቄ አያሌ ቁጥር ያላቸው ኢራናውያን ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ፍላጎት አሳይተዋል። ከሁለት ዓመት በፊት የኢራን ባህላዊ የሙዚቃ ቡድን በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራውን በዩኒቨርሲቲዎች እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር አቅርቧል። አሁን ደግሞ የኢትዮጵያን ባህላዊ የሙዚቃ ቡድን ወደተለያዩ የኢራን የዩኒቨርሲቲዎች እና ከተሞች በመላክ ዝግጅቶችን የማቅረብ ፍላጎቱ አለን።

## በሩሲያ ኢትዮጵያን የተመለከተ የቢዝነስ ፎረም ተካሄደ

በሩሲያ ኢትዮጵያን የተመለከተ የቢዝነስ ፎረም ተካሄደ። በቪዲዮ ኮንፈረንስ የተካሄደውን ፎረም በሩሲያ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ያዘጋጀው ነው። ፎረሙ በኢትዮጵያ ያሉ መልካም የኢንቨስትመንት አማራጮችን ለማስተዋወቅ ያለመ ነው ተብሏል። ከዚህ ባለፈም ከአካባቢው ሃገራት በተለይም ከሩሲያና ቤላሩስ ጋር ኢንቨስትመንት እና ንግድን በመሳብ የሃገራቱን የቢዝነስ ግንኙነት ለማጠናከር ያለመ መሆኑም ተገልጿል። በሩሲያ የኢትዮጵያ አምባሳደር አለማየሁ ተገኑ ለፎረሙ ተሳታፊዎች በኢትዮጵያ ስላሉ ምቹ የኢንቨስትመንት አማራጮች ገለጻ አድርገዋል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ጽዮን ተክሉ በበኩላቸው በኢትዮጵያ የሚገኙ የንግድ ኢንቨስትመንቶችን በተመለተ ገለጻ ማድረጋቸውን በሩሲያ የኢትዮጵያ ኤምባሲ መረጃ ያመላክታል።

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ የዐሥር ዓመት ምርጥ የአፍሪካ አየር መንገድ ሽልማትን አሸነፈ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአስር ዓመት ውስጥ የአፍርካ ምርጥ አየር መንገድ ሽልማት አሸናፊ መሆኑ ተገለጸ። ለአቪዬሽን ኢንዱስትሪው አስቸጋሪ በሆነው የአፍሪካ ቀጣና እና ፈታኝ በሆነ ወቅት ባስመዘገበው ድንቅ ስኬት መሸለሙም ታውቋል። እንዲሁም የኢትዮጵያ አየር መንገድ እውነተኛው የፓን አፍሪካኒዝም ምሳሌ በመባል አድናቆት ተቸሮታል። አየር መንገዱ በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ያስመዘገበው ትርፍም የስኬት መንገዱን ያሳየ መሆኑ ነው የተገለጸው። ከዚህ በተጨማሪም አየር መንገዱ እንደ ቻይናና ዱባይ ባሉ ከፍተኛ የንግድ፣ የቱሪዝምና የኢንቨስትመንት መዳረሻዎች ላይ የሚሰጠው አገልግሎት ተመራጭ እንዳደረገውም ተጠቁሟል። በአየር መንገዱ እየተካሄደ ያለው የማስፋፊያ ፕሮጀክትና በምቾት አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙት ዘመናዊ አውሮፕላኖቹ አየር መንገዱን ከአፍሪካ አልፎ በአለም አቀፍ ደረጃ ተመራጭ እንዳደረገውም ፍላይት ግሎባል መረጃ ያመለክታል።

## የከተሞች ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮጀክት በ83 ከተሞች ሊተገበር ነው

የከተሞች ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮጀክት በቀጣይ ተጨማሪ 72 ከተሞችን በማቀፍ በጠቅላላ በ83 ከተሞች እንደሚተገበር የኮንስትራክሽን ሚኒስትርና የፕሮጀክቱ ስትሪንግ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኢ/ር አይሻ መሐመድ አስታወቁ። ኢ/ር አይሻ መሐመድ ባለፉት 5 ዓመታት ከ600 ሺህ በላይ ዜጎችን የዕለት ጉርስ ማሟላት እና ሕይወታቸውን ማስቀጠል መቻሉንም ገልፀዋል። የስትሪንግ ኮሚቴው በ2012 ሪፖርት እና በ2013 ዕቅድ ላይ ተወያይቷል። ፕሮጀክቱ በተተገበረባቸው ከተሞች ለከተሞች ፅዱነት እና አረንጓዴነት አስተዋፅኦ አድርጓል ብለዋል ኢ/ር አይሻ። የደሴ ከተማ ደግሞ በአርዓያነት በተነሳበት ውይይቱ ፕሮጀክቱ በቀጣይ ተጨማሪ 72 ከተሞችን በማቀፍ በጠቅላላ በ83 ከተሞች ይተገበራል ተብሏል። በፕሮጀክቱ የሥራ ዕድል ፈጠራን ለማካተት እና የስደተኞች የሥራ ዕድል ፈጠራም ለመተግበር በዝግጅት ላይ ነውም ተብሏል።




## ክብርት ዶ/ር ሂሩት ካሳው የእውቅና ሽልማት ተበረከተላቸው

የኢፌዴሪ የባህል፣ ቱሪዝም እና ስፖርት ሚኒስትር ዶ/ር ኂሩት ካሳው የ2019 እጅግ ምርጧ የአፍሪካ ቱሪዝም መሪ (WOMEN IN AFRICA TOURISM 2019 MOST ENERGETIC AND PASSIONATED AFRICAN TOURISM LEADER AWARD) አሸናፊ ሆነው መመረጣቸውን በጋና የሚገኘው ስትሪት ኦፍ ጎልድ ፋውንዴሽን የተሰኘው ድርጅት አስታውቋል፡፡ ተቋሙ ለሚኒስትሯ አሸናፊ ኾኖ መመረጥ ምክንያት አድርጎ ካስቀመጣቸው ምክንያቶች መካከል ተቋማዊ ሪፎርም ለማምጣትና ይኽንንም ለማስፈፀም ያሳዩት ቁርጠኝነትና ተነሳሽነት፣ በዘርፉ የሥራ ዕድል ፈጠራ እንዲኖር ለሰጡት ከፍተኛ ትኩረት እና የቱሪስቶች ቁጥርና የቱሪዝም ገቢ መጠን እንዲጨምር ላደረጉት ጥረት መኾኑን ገልጹዋል፡፡ ሽልማቱ ከቀናት በኋላ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 12/2020 አዲስ አበባ በሚገኘው ስካይላይት ሆቴል የሚደረግ መሆኑን የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር አስታውቋል፡፡

## በሩብ የበጀት ዓመቱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ያቀዱትን አልተገበሩም ተባለ

በአገልግሎት ዘርፍ የተካተቱት የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን፣ የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅት፣ አዲስ አበባ ሒልተን፣ ፍል ውኃ አገልግሎት ድርጅትና የጊዮን ሆቴሎች ድርጅት ሲሆኑ፣ የ2013 የመጀመርያ ሩብ ዓመት የ1.3 ቢሊዮን ብር የሽያጭ አፈጻጸማቸው ከዕቅዳቸው አንፃር 55 በመቶ ብቻ ማሳካታቸው ተገለጸ፡፡ ይህም በሩብ ዓመቱ ያገኙት ገቢ ከዕቅዳቸው ከ700 ሚሊዮን ብር በላይ ያነሰ መሆኑን ነው፡፡ ባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ግን ሒልተን ሆቴልን ሳይጨምር አራቱ የንግድ የአገልግሎት ዘርፍ ድርጅቶች አግኝተውት የነበረው ገቢ 1.73 ቢሊዮን ብር ነበር፡፡ ዘንድሮ በአንድ ድርጅት የጨመረው ዘርፉ ያገኘው የትርፍ መጠን ግን 1.3 ቢሊዮን ብር መሆኑ የትርፍ ምጣኔው ከቀዳሚው ዓመት አንፃር ሲታይ ከ430 ሚሊዮን ብር በላይ ያነሰ መሆኑን ያመለክታል፡፡

የእነዚህ አምስት ድርጅቶች ገቢ ከዕቅድ አንፃር ሲታይ በ55 በመቶ ቅናሽ ማሳየቱ በሩብ ዓመቱ ሊገኝ ይችላል የተባለውንም የትርፍ መጠን እንዲቀንስ አድርጎታል፡፡ በመረጃው መሠረት አምስቱ የንግድና የአገልግሎት ዘርፍ ድርጅቶች በ2013 የመጀመርያ ሩብ ዓመት ከታክስ በፊት ያገኛሉ ተብሎ የታቀደው 90 ሚሊዮን ብር ቢሆንም አፈጻማቸው ግን 64 ሚሊዮን ብር ሆኗል፡፡ ይህም የትርፍ አፈጻጸም ከዕቅዳቸው አንፃር ሲታይ 71 በመቶ እንደሆነም ታውቋል፡፡ የ2013 የመጀመርያ ሩብ ዓመት የትርፍ አፈጻጸማቸው ከቀዳሚ ዓመት የትርፍ ግኝት ጋር ሲነፃፀር ከ13.6 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያንስ ነው፡፡

## ጥረት ኮርፖሬት የስያሜ ለውጥ አደረገ

“ጥረት ኮርፖሬት” የተሰኘው የአማራ ክልል የአደራ (ኢንዶውመንት) ኩባንያ የስያሜ ለውጥ ማድረጉ ታውቋል፡፡ አዲሱ ስያሜው “ንጋት ኮርፖሬት” የተባለ ሲሆን፣ ተቋሙ ከስያሜውና መለዮው (ሎጎ) ጀምሮ አጠቃላይ የአሠራር ማሻሻያ እያደረገ መሆኑን ከድርጅቱ መረጃ ማግኘቱን ገልጾ ሲራራ ጋዜጣ ዘግቧል፡፡ ጥረት ኮርፖሬት ከ26 በላይ ኩባንያዎችን በስሩ ያቀፈ ግዙፍ ተቋም መሆኑ ይታወቃል፡፡

## አዋሽ ባንክ በትርፉና በሀብቱ ቀዳሚ የግል ባንክ መሆኑ ተገለጸ

ቀዳሚ ከሆኑት ኢትዮጵያ የግል ባንኮች አንዱ የሆነው አዋሽ ባንክ፣ በ2012 የሒሳብ ዓመት ያልተጣራ የትርፍ መጠኑን ከ4.2 ቢሊዮን ብር በላይ በማድረስ የሒሳብ ዓመቱን ማጠናቀቁን ገልጿል፡፡ ከታክስና ሌሎች ተቀናሾች ተደርገው 2.6 ቢሊዮን ብር ትርፍ ማግኘቱንም አመልክቷል፡፡ ይህም ከቀዳሚው ዓመት የሰባት በመቶ ብልጫ ያሳየ መሆኑን ቅዳሜ ኅዳር 19 ቀን 2013 ዓ.ም ባካሄዱው ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ይፋ አድርጓል፡፡

በ2012 የሒሳብ ዓመት ያስመዘገበው ትርፍ መጠን በ25 ዓመት በባንክ ኢንዱስትሪ ታሪክ እስካሁን ያልተመዘገበ ከፍተኛ ትርፍ መሆኑም ተገልጿል፡፡ ከትርፍ ባሻገር በሒሳብ ዓመቱ የባንኩን አፈጻጸም የሚያሳዩ አኃዛዊ መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ የባንኩ 2012 የሒሳብ ዓመት ያስመዘገበው ትርፍ የተገኘው በተለያዩ አፈጻጸሞቹ ባስገኘለት አመርቂ ውጤት መሆኑን የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር ዲባባ አብደታ (አምባሳደር ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡

ከዓመታዊ መረጃው መገንዘብ እንደተቻለውም፣ አዋሽ ባንክ በ2012 የሒሳብ ዓመት ማጠናቀቂያ ላይ በተቀማጭ ገንዘብ ረገድ የ19 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ 74.3 ቢሊዮን ብር ደርሷል፡፡ በብድር አሰጣጥ ረገድም በሒሳብ ዓመቱ የብድር መጠኑን በ21 በመቶ በማሳደግ፣ ለተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች የተሰጠውን ብድር መጠን 57.4 ቢሊዮን አድርሷል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ የባንኩ የተበላሸ ብድር ምጣኔ 1.7 በመቶ መሆኑም ባንኩ በብድር አመላለስ ላይ ያሳየው አፈጻጸም ውጤታማ እንደሆነ የሚያሳይ ነው መባሉን ሪፖርተር ጋዜጣ ዘገቧል፡፡

ኢትዮ ሐበሻ ህትመትና ማስታወቂያ ኃ.የተ.የግ.ማህበር

# ግዮን መፅሔት ለ2013

በአዲስ አደረጃጀትና አቀራረብ

- በWebsite: http://ghion-meg.com
- በYouTube: Ghion-Meg Tube ግዮን መጽሔት
- በTwiter: Ghion Megazine
- በTelegram: Ghion Megazine
- በFacebook: Ghion-Meg ግዮን መጽሔት
- በInstagram: Ghion Meg

ለአንባቢያን

እንደምርጫው ለመድረስ በዝግጅት ላይ ነን ድርጅታችሁን በማስተዋወቅ ለአገራችን እውነተኛ መረጃ ለመስጠት የምናደርገው ጥረት እንድትደግፉና እንድታበረታቱን እንጋብዛለን፡፡

## መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን !




የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ

ስልክ ፡ +251 911 227661 +251 912 165606

+251 118 12 2333

ኢ-ሜይል: enqu2013@ gmail.com

Ghion2011meg@gmail.com